# የአስተምህሮተ ሥላሴ
## መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት



ከተስፋዬ ሮበሌ

የአስተምህሮተ ሥላሴ
መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት



# የአስተምህሮተ ሥላሴ
## መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት




**የመልእክት ሣጥን ቁጥር 23045፤ ኮድ 1000**
**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ**

- ርእስ - የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት
- ጸሓፊ - ተስፋዬ ሮበሌ
- አሳታሚ - ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
- መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው 1998 ዓ.ም
- ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማራባት/ማባዛት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃ ለመውሰድ ከተፈለገ፣ በትክክል ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ፣ በግርጌ ማስታወሻ ሊመላከት ይገባዋል።
- ልዩ መግለጫ ካልቀረበ በስተቀር፣ የተከተልነው የጎርጎሮሳውያኑን የዘመን አቈጣጠር ሲሆን፣ ጥቅሶቹ የተወሰዱት የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1954 ዓ.ም ያሳተመውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ነው።
- ቀደምት ወይም ደኅርት የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ስም በተመለከተ፣ በአማርኛ የተጻፉ ጥንታዊ የብራና ጽሑፎችን ስያሜ ተከትለናል።
- ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሒስ ካልዎ ለጸሓፊው በሚከተለው አድራሻ ይጻፉ:-

**ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር**
**የመልእክት ሣጥን ቁጥር** 23045፤ **ኮድ** 1000
**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ**

- Title – The Biblical Basis of the Trinity
- Author - Tesfaye Robele
- Publisher - The Evangelical Society For Apologetics (TESFA)
- Copyright 2005 - **T**he **E**vangelical **S**ociety **F**or **A**pologetics (TESFA)
- All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means-electronic, mechanical, photocopying, or other wise-without the prior written permission of the publisher and copyright owner.

*The Evangelical Society For Apologetics (TESFA)*
*Post Office Box 23045, Code 1000*
*Addis Ababa, Ethiopia.*
**E-mail:** apologetics@ethionet.et

tesfa_apologetics@yahoo.com
tesfaye_robele@yahoo.com

- Comments, questions, and criticisms of this book are welcome. Please address all correspondence to the above address.

# ማውጫ


- መግቢያ፡ እግዚአብሔር ምን ይመስላል? 1
- ሥላሴ የሚለው ቃል ምን ትርጒም ይወክላል? 2
- ትምህርተ ሥላሴን ለማብራራት የምንጠቀብማቸው ምሳሌዎች 10
- ትምህርተ ሥላሴ በዓለም ሃይማኖቶችና በመናፍቃን እይታ 11
- ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ስለሥላሴ ምን ይላሉ? 15
- የቅዱሳት መጻፍት የአፈታት ጥበብና ትምህርተ ሥላሴ 20
- የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት—ተዋፅኦአዊ ጥናት 23

I. እግዚአብሔር አንድ ነው (አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ)
II. ይህ አንዱ አምላክ በብሉይ ኪዳን ያህዌ በሚል ስም ይታወቅ ነበር
III. እግዚአብሔር ፍጹም ልዩና የሰዎች አእምሮ ከሚረዳው በላይ ምጡቅ ነው
IV. እግዚአብሔር አንድ አካል ነውን?
V. የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር አብ ነው
VI. ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው
VII. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው
VIII. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት ናቸው።
IX. ማጠቃለያ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ያስተምራል
X. አስተምህሮተ ሥላሴ በእምነት አስተምህሮ ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?

- አባሪ 1
- አባሪ 2
- አባሪ 3
- አባሪ 4


# የመጽሐፉ መታሰቢያነት

## በወንጌል ሥራ እጅግ ትጉህ ለነበረውና በቅርቡ ወደ ጌታ ለሄደው ለወንድም አሕመድ መሐመድና ለባለቤቱ ርግበ ብርሃነ

"ክርስቶስን ተስፋ ያደረግነው ለዚህች ሕይወት ብቻ ከሆነ፣ ከሰው ሁሉ ይልቅ የምናሳዝን/ምስኪኖች ነን። ነገር ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኩራት ሆኖ በእርግጥ ከሙታን ተነሥቶአል"

(1 ቆሮንቶስ 15÷19-20)

"የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የተከበረ ነው"

(መዝሙር 116÷16)

# ምስጋና

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ውድ ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ፣ ረቂቁን በማንበብ ጠቃሚ አስተያየት የሰጡኝን እንዲሁም ከበርካታ ስሕተት የታደጉኝን ሰዎች ማመስገን እወዳለሁ። እንዲያም ሆኖ በመጽሐፉ ላይ ስሕተት ቢገኝ፣ የስሕተቱ ተወቃሽ እኔው ጸሓፊው እንጂ እነዚህ ሰዎች አይደሉም—አስተያየቶችን ሁሉ አላካተትሁምና።

ቀሲስ ሙሉጌታ ታደሰ፣ አቶ ንጉሤ ቡልቻ፣ አቶ ማሞ ገበረ መስቀል፣ መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን፣ አቶ ምኒልክ አስፋው፣ አቶ ካሱ በላቸው።

እግዚአብሔር ያክብርልኝ፤ ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ።

# የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት—*ተዋፅኦአዊ ጥናት*

## *መግቢያ*

### እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

በተለያየ ቦታና ጊዜ ሰዎች የራሳቸውን አምላክ ሲፈጥሩና ለፈጠሯቸውም አማልክት ሲሰግዱ ይታያል፡፡ ታዲያ የእነዚህን አማልክት ቅርጽ የሚወስነው እነዚህን ጣዖታት የሚያበጀው ቀራጺ ወይም አንጥረኛ ወይም ደግሞ ጠራቢ ነው፡፡ በልቡና በአእምሮው እንዳሰበው አድርጎ “አምላክ” የሚለውን ይቀርጸዋል፡፡ ይህም “አምላክ” የቀራጺውን፣ የአንጥረኛውን ወይም የጠራቢውን ልብና አስተሳሰብ በመወከል ሲመለክና ሲወደስ ይኖራል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር በምንማረው ትምህርት፣ እግዚአብሔርን ፍጹም ልንረዳውም ሆነ ልንጨብጠው (እንዲህ ወይም እንዲያ ነው ብለን ልንገምተው) አለመቻላችንን ነው፡፡ በተለይ አዲስ ኪዳን ስለ አብ፣ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረው ትምህርት ከግንዛቤያችን ፍጹም የላቀ የመሆኑ ጉዳይ፣ እግዚአብሔርን በተመለከተ የምንሰጠው መልስ መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ማእከል ያደረገ እንዲሆን ግድ ይላል፡፡ በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር የምንነጋገረው ብሉያትና ሐዲሳት የእግዚአብሔርን ማንነት በገለጡልን መጠን ብቻ እንዲሁም ሐሳብንና ፈቃድን ለአምላክ ቃል ባስገዛና ቅዱሳት መጻሕፍት በጉዳዩ ላይ ምን ይላሉ በሚል ትሑት መንፈስ ሊሆን ይገባል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው ተዋፅኦአዊ[1] ጥናት፣ ትምህርተ ሥላሴን በአሰሳ መልክ የሚቃኝ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ላይ የቀረቡትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች በተመለከተ፣ ሰፊ ማብራሪያ አልተሰጠም፤ ይህ እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት፣ አስተምህሮውን አስመልክቶ የሚቀርቡትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች በብዛት ለማቅረብ ስለ ተፈለገ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ከሰባት መቶ በላይ የሚሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአስረጅነት የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህም እማኞች ከሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል፣ ከሃያ ስድስቱ መጻሕፍት የተወሰዱ ናቸው፡፡ ይህን ተዋፅኦአዊ ጥናት ከመጀመራችን በፊት ለጥናታችን ጥሩ መደላድል እንዲሆነን፣ ከርእሰ ጉዳዮ ጋር ተዛማጅ የሆኑና ተዘውትረው የሚነሡትን ጥያቄዎች እንመልከት፡፡

---

[1] **ተዋፅኦአዊ፣** አስተዋፅኦ/አስተዋፃኢ ከሚለው የግእዝ ቃል የተወሰደ ነው፡፡ ቃሉ ግሥ ወይም ቅጽል በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ የአንድን ትምህርት ወይም ሙግት ወይም ደግሞ ሀሳብ መንደርደሪያና ድምዳሜ መሠረታዊ ውቅር ምን እንደሚመስል የሚገልጽ አጭር ጽሑፍ ተዋፅኦ ይባላል፡፡ በዚህ ትርጉሙ መሠረት Outline ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራል፡፡ **ተዋፅኦአዊ ጥናት** የሚለው ሐረግ outline study የሚሉትን የእንግሊዝኛ ቃላት በሚወክል መልኩ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ “**የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ መሠረት**” በሚል ርእስ ወደ 350 ገጽ ያለው መጽሐፍ በማዘጋጀት ላይ ሲሆን፣ በዚህ መጽሐፍ የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ መሠረት ሰፊ ቦታ ተሰጥቶታል፡፡

## ሥላሴ የሚለው ቃል ምን ትርጒም ይወክላል?

ክርስትና አሐዱ አምላክ ብሎ የሚያምን ሃይማኖት (monotheism) ነው:: በዚህም ከይሁዲና ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ተመሳሳይ አቋም ይጋራል፤ ነገር ግን የክርስትና አሐደ አምላክ እምነት፣ ከእነዚህ ሃይማኖቶች የሚለይበት ነጥብ አለው:: በክርስትና እምነት እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ሦስት አካላት ግን አሉት፤ እነርሱም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው::

የሥላሴ አስተምህሮ የተቀዳው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም፣ አስተምህሮው ሙያዊ ቃላት ተበጅተውለት ደርዝ ባለው መልክ የቀረበው፣ ከብዙ ዓመት በኋላ ነው:: "**ትሪያስ**" የሚለውን የግሪክ ቃል 168-183 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ቴዎፍሎስ (Theophilus) የተባለው የቤተ ክርስቲያን አባት ሲሆን፣ 220 ዓ.ም ላይ "**ትሪኒታስ**" የሚለውን የላቲን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ደግሞ ጠርጡልያን (Tertullian) ነው:: ሥላሴ ለሚለው ቃል የእንግሊዝኛው አቻ ቃል "Trinity" የሚለው ሲሆን፣ ቃሉ "tri" ወይም "ሦስት" እና "unity" ወይም "ኅብረት/አንድነት" ከሚሉት ሁለት የላቲን ቃላት የመጣና አንድ ቃል ሆኖ በተገናኝ የሚነበብ ("tri" + "unity") ነው::

እንዳንድ ሰዎች "ሥላሴ" የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለማይገኝ፣ የ"ሥላሴ" አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ይላሉ:: ይህ ስሕተት ነው:: "ሥላሴ" የሚለው ሙያዊ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለመገኘቱ ሁላችንንም ሙሉ ለሙሉ የሚያስማማ ጉዳይ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብ፣ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰፊ ትምህርት እስካለው ድረስ፣ "ሥላሴ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብ፣ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት የለውም" ማለት አይቻልም:: ይህን መሰሉን የሙግት ነጥብ በመያዝ፣ "ግብረ ሰዶም"፣ "ውርጃ"፣ "ጫት መቃም"፣ "የወሲብ ሥዕሎችን መመልከት"፣ "አደንዛዥ ዕፆችን መጠቀም" ወዘተ የሚሉት ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለማይገኙ፣ ቃለ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች አልኰነነም ወይም በእነዚህ ነገሮች ላይ የሥነ ምግባር ትምህርት የለውም ማለት በፍጹም አይቻልም:: ክርስቲያን ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው ወይም በየትኛውም "ቤተ ክርስቲያን" ጥላ ሥር የተጠለለ ሰው፣ እነዚህ ነገሮች በቃለ እግዚአብሔር የተኰነኑ ናቸው የሚል የጸና አቋም አለው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚህ ርእሰ ጉዳዮች የማያወላዳ መመሪያ እንዳለው ያውቃልና ነው::

ከላይ የጠቀስናቸውን ቃላት ጨምሮ ትምህርተ ክርስቶስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ነገረ ፍጻሜ፣ አምላከ ገዝ (theocracy) ወዘተ የሚሉት ቃላት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደማይገኙ ሁሉ፣ "ሥላሴ" የሚለውም ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም:: እነዚህ ቃላት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈው አይገኙም ማለት ደግሞ፣ እነዚህ ቃላት የወከሏቸው ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም ማለት አይደለም:: በቃለ እግዚአብሔር ተፈትሸው እስካልወደቁ ድረስ:: አንድ ሰው እነዚህን ሙያዊ ቃላት አለመቀበል ይችላል፤ ሙያዊ ቃላቱን እስካልተቀበልሁ ድረስ ቃላቱ የወከሏቸውን ትምህርቶችም አልቀበልም ማለት ግን ስሕተት ነው:: ሥላሴ የሚለው ቃል የሚወክለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ክዶ የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ወይም የዘላለም ሕይወት አለኝ የሚል አስተሳሰብ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ የለውም:: ጠርቱሊያን "ሥላሴ" እንዲሁም "አካል" የሚለውን ቃል በሥራ ላይ ሲያውል፣ ቃሉ የሚወክለው ትርጒም እንደሚከተለው ነው:: ሥላሴ ማለት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት በአምላክነት ወይም በባሕርይ አንድ መሆናቸውን የምንገልጽበት ቃል ነው:: የቃሉ አገባብ አንድነትንም ሦስትነትንም በአንድ ጊዜ ማስረዳቱ ነው::

በክርስቲያናዊ አስተምህሮ በተለይ ደግሞ በሥላሴ አስተምህሮ ውስጥ "አካል" ማለት የስሜት፣ የፈቃድና የዕውቀት መኖር ስለሆነ ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት የሌለውን አካል ማለት አንችልም:: መላእክት አካል አላቸው የሚባለው፣ ባይዳሰሱና ባይታዩም (ረቂቃን ፍጥረታት ቢሆኑም) እንኳ ይህን መስፈርት ስለሚያሟሉ ነው:: እግዚአብሔር አብ አካል አለው ወይም መንፈስ ቅዱስ አካል አለው ሲባል ይዳሰሳል/ይጨበጣል ወይም ይታያል ማለት ሳይሆን፣ የራሱ የሆነ ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት አለው ማለት ነው:: ሰው

አካል አለው የሚባለው ቊሳዊ ባሕርይ ኖሮት ስለሚታይና ስለሚዳሰስ ሳይሆን፣ የአካል መስፈርት የሆኑትን ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት ገንዘቡ ስላደረጋቸው ነው።

ሥላሴ የሚለው ቃል ከቋንቋ ረገድ (በአማርኛ) ያለውን ትርጒምና በነገረ መለኮት ትምህርት ውስጥ ያለውን ፍቺ ወደ መቃኘቱ እንዝለቅ።

## ቋንቋዊ ፍቺው

ሥላሴ የሚለው ቃል የነገረ መለኮት ቃል እንደ መሆኑ መጠን፣ ቃሉ በአብዛኛው መጤን ያለበት ከቋንቋ አኳያ ሳይሆን ከነገረ መለኮት አኳያ ነው። በተለይ የሥላሴ አማንያን ቃሉን እንዴት ይመለከቱታል የሚለው ጒዳይ መሠረታዊ ይሆናል። ይህ እንዳለ ሆኖ የቋንቋ ምሁራንስ ቃሉን እንዴት ተረድተውት ነበር የሚለውን ጒዳይ መመልከት ቢያንስ ቃሉ መፈታት ያለበት በነገረ መለኮት ትርጒሙ ነው የሚለውን አቋም ያጸናልናል።

ስመ ጥር የሆኑት የአማርኛ መዝገበ "ቃላት" ሥላሴ የሚለውን ቃል በሚከተለው መልኩ ይፈቱታል፡-

**ሥላሴ፤** እግዚአብሔር በአካል፣ በስም፣ በግብር፣ የሦስትነቱ መገለጫ ስም[2]።

**ሥሉስ፤** በአካሉ ሦስት የሆነ አምላክ[3]።

**ሠለሰ፤** ሥላሴ የሚባሉ አብን፣ ወልድን፣ መንፈስ ቅዱስን በሦስት አካል ከፍሎ በመለኮት፣ በባሕርይ፣ በመንግሥት፣ በፈቃድ አንድ አድርጎ አዋሐደ። ሦስት አካላትን አመነ[4]።

[2] *አማርኛ መዝገበ ቃላት፤* የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1993፤ አዲስ አበባ። ገጽ 106።

[3] ደስታ ተክለ ወልድ፤ *ዐዲስ አማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1962፤ አዲስ አበባ። ገጽ 886።

**ሥሉስ ቅዱስ፤** በሦስትነት ያለ ቅዱስ አካላት የማይለያይ ባሕርየ ሥላሴ። ቅዱሳን ባሕርያት አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ[5]።

በአማርኛ ቋንቋ ሊቃውንት ዘንድ መልካም ስም ያላቸው እነዚህ መዝገበ ቃላት፣ ሥላሴ የሚለውን ቃል የፈቱት በነገረ መለኮት ካለው አጠቃቀም ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደ ሆነ እንመለከታለን።

## ነገረ መለኮታዊ አገባቡ

የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶችን አስተምህሮ የያዘውና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ "ሃይማኖተ አበው" በሚል ርእስ ያሳተመችው ስመ ጥር መጽሐፍ፣ ትምህርተ ሥላሴን በዚህ መንገድ ይገልጸዋል፤

> "በምስጢረ ሥላሴ እግዚአብሔር በስም፣ በግብር፣ በአካል ሦስት፤ በባሕርይ፣ በመለኮት፣ በህልውና አንድ መሆኑን እየገለጠ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ መሆኑን እየሰበከ አንድ ገጽ የሚሉ አይሁድንና ሰባልዮስን፣ እስማኤላውያንን ወልድ ፍጡር የሚል አርዮስን፣ መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ የሚል መቅዶንዮስን ሌሎችንም መናፍቃንን ከነወገኖቻቸው ይቃወማል"[6]።

ከዚህ ገለጻ ልብ ልናደርገው የሚገባን ቊም ነገር፣ "**ሦስት**" የሚለው ቃል ስምን[7]፣ ግብርን[8]ና አካልን[9] የሚያመለክት ሲሆን፣ "**አንድ**" የሚለው ቃል ደግሞ ባሕርይን፣ መለኮትንና ህልውናን ያመለክታል።

[4] ተሰማ ግጸው፤ *ከሣቴ ብርሃን የዐማርኛ በዝገበ ቃላት፤* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1962፤ አዲስ አበባ። ገጽ 175።

[5] ዝኒ ከማሁ።

[6] *ሃይማኖተ አበው፤*

[7] አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተብሎ እንደማይጠራው ሁሉ፣ ኢየሱስ ክርስቶስም አብና መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም። መንፈስ ቅዱስም ወልድና/ኢየሱስ ክርስቶስና አብ ተብሎ አይጠራም ማለት ነው።

[8] የሥላሴ አካላት የተለያየ ግብር/ሥራ አላቸው:: እግዚአብሔር አብ የሚከተሉትን ሥራዎች ይሠራል/ሠርቶአል:- 1) ዓለማትን መፍጠር (1ቆሮንቶስ 8÷6፤ ራእይ 4÷11)፤ 2) መለኮታዊ መገለጥ መስጠት (ራእይ 1÷1)፤ 3) ድኅነት/ድነት መስጠት (ዮሐንስ 3÷16-17)፤ እንዲሁም 4) ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሠራቸው ሥራዎች ውስጥ ተካፋይ መሆን (ዮሐንስ 5÷17፤ 14÷10):: እግዚአብሔር አብ የእነዚህ ሥራዎች **ቀዳማይ አመንጪ** (initiater) ነው::

አብ የሚሠራቸውን ሥራዎች የሠራው በኢየሱስ ክርስቶስ **አማካይነት** ነው:- 1) ዓለማትን መፍጠርና ዓለማትን ደግፎ መያዝ (1ቆሮንቶስ 8÷6፤ ዮሐንስ 1÷3፤ ቈላስይስ 1÷16-17)፤ 2) መለኮታዊ መገለጥ መስጠት (ዮሐንስ 1÷1፤ ማቴዎስ 11÷27፤ ዮሐንስ 16÷12-15፤ ራእይ 1÷1)፤ እንዲሁም 3) ድኅነት/ድነት መስጠት (2ቆሮንቶስ 5÷19፤ ማቴዎስ 1÷21፤ ዮሐንስ 4÷42):: ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ **ወኪል** (agent) ነው የሚባልበት ምክንያት፣ እግዚአብሔር አብ እነዚህን ሥራዎች የሠራው በኢየሱስ ክርስቶስ **አማካይነት** ስለሆነ ነው::

እግዚአብሔር አብ የሚከተሉትን ሥራዎች የሠራው በመንፈስ ቅዱስ **ኀይል** ነው:- 1) ዓለማትን መፍጠርና ዓለማትን ደግፎ መያዝ (ዘፍጥረት 1÷2፤ ዮሐንስ 26÷13፤ መዝሙር 104÷30)፤ 2) መለኮታዊ መገለጥ መስጠት (ዮሐንስ 16÷12-15፤ ኤፌሶን 3÷5፤ 2ጴጥሮስ 1÷21)፤ **3)** ድኅነት/ድነት መስጠት (ዮሐንስ 3÷6፤ ቲቶ 3÷5፤ 1ጴጥሮስ 1÷2)፤ እንዲሁም 4) በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ውስጥ ተካፋይ መሆን (ኢሳይያስ 61÷1፤ ሐዋርያት ሥራ 10÷38)::

በሁሉ ቦታ መገኘት፣ ሁሉን ማወቅ፣ ሁሉን መቻል፣ ፈጣሪነት ወዘተ የሚሉት መለኮታዊ ባሕርያት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በእኩል የሚጋሩት ባሕርያት ናቸው:: ይህ ባሕርይ እንዳለ ሆኖ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሥራ ክፍፍል አላቸው:: "አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ነው" የሚባለውም በሥላሴ አካላት መካከል የተለያየ ግብር/ሥራ እንዳለ ለማሳየት ነው:: [አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ ነው ሲባል፣ በአብና በወልድ መካከል ዘላለማዊ **ግንኙነት** እንዳለ ለማሳየት እንጂ፣ አብ የነበረበት ወልድ ግን ያልነበረበት ዘመን/ጊዜ ነበር ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል:: አብና ወልድን በተመለከተ ያለው "አባትነት"ና "ልጅነት"፣ ጊዜን ሳይሆን ግንኙነትን እንደሚያመለክት መዘንጋት የለበትም]:: አብ ዓለምን ስለወደደ አንዲያ ልጁን ሰጠን፤ ወልድ ዓለምን ስለወደደ የኀጢአታችንን ዕዳ





አንድ ነገር በተወሰነ ትርጒሙ፣ ሁኔታና ጊዜ አንድና ሦስት መሆን አይችልም:: ስለዚህ "**አንድ**" እንዲሁም "**ሦስት**" የሚሉት ቊልፍ ቃላት የተለያየ ትርጒምን የሚወክሉ ስለሆነ፣ ትምህርተ ሥላሴ ውስጥ የአመክንዮ መጣረስ/ግጭት ሊኖር አይችልም:: ብዙ ሰዎች ይህን ጒዳይ በወል ማስተዋል ሲያቅታቸው፣ በትምህርተ ሥላሴ ውስጥ ተቃርኖ አለ ብለው ያስባሉ::
የሥላሴ አስተምህሮ በሚከተሉት አምስት መሠረታዊ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ነው::

1. መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር አንድ ብቻ እንደ ሆነ ያስተምራል (**ዘዳግም** 4÷35፤ 39፤ 32÷39፤ 2**ሳሙኤል** 22÷32፤ **ኢሳይያስ** 37÷20: 43÷10፤ 44÷6-8፤ 45÷5፤ 14፤ 21-22፤ 46÷9፤ **ዮሐንስ** 5÷44፤ **ሮሜ** 3÷30፤ 16÷27፤ 1**ቆሮንቶስ** 8÷4-6፤ **ገላትያ** 3÷20፤ **ኤፌሶን** 4÷6፤ 1**ጢሞቴዎስ** 1÷17፤ 2÷5፤ **ይሁዳ** 25)::
2. መጽሐፍ ቅዱስ፣ አብ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል (ዮሐንስ 17÷3፤ 1**ቆሮንቶስ** 8÷6፤ 2**ቆሮንቶስ** 1÷3፤ **ኤፌ**1÷3፤ 1**ጴጥሮስ** 1÷3)::

በመክፈል የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን አደረገ፤ መንፈስ ቅዱስ፣ ክርስቶስ ወደ ፈጸመው ወጀዊ ሥራ አመጣን፤ በኀጢአታችን እንድንናዘዝ፣ ክርስቲያነዊ ኑሮን እንድንኖር፣ መንፈሳዊ ፍሬዎችን እንድናፈራ፣ ሕይወታችንን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንድናስተዳድር ወዘተ የሚያስችለን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው:: የኀጢአታችንን ዕዳ ለመክፈል በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስ ሕይወቱን የሰጠን አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን **ወልድ** ነው:: ድኅነትን/ድነትን መስጠት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አብ በመስቀል ላይ ሞቶልናል ማለት ግን ትልቅ ስሕተት ነው:: በሥላሴ መካከል ያለውን የግብር/የሥራ ልዩነት ስለሚያዛባ:: "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚጠራው መናፍቃዊ ድርጅት "አብ፣ ኢየሱስ የሚባለውን ሰው ሥጋ በመልበስ፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሏል" ይላል:: ይህ አብ ለኀጢአታችን ተሠቃየ "**ፓትሮፓሽኒዝም**" ["ፓቲር" (አባት) እና "ፓሽን" (መከራ፣ ሥቃይ) ከሚሉት ሁለት የግሪክ ቃላት የተገኘ ነው] የሚለው የሰባልዮስ ኑፋቄ ነው:: ይህ ኑፋቄ በጉባኤ ኒቂያ ተወግዞአል፣ "ውጉዝ ከመሰባልዮስ"::
[9] አካል ማለት የስሜት፣ የፈቃድና የዕውቀት መኖር እንጂ፣ የመጨበጥ/የመዳሰስ ወይም የመታየት ጒዳይ እንዳልሆነ ልብ ይሏል::

3. መጽሐፍ ቅዱስ፣ ወልድ/ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል (ኢሳይያስ 9÷6፤ ዮሐንስ 1÷1፤ ዮሐንስ 1÷18፤ 20÷28፤ የሐዋርያት ሥራ 20÷28፤ ሮሜ 20÷28፤ ቲቶ 2÷13፤ ዕብራውያን 1÷8፤ 1ጴጥሮስ 1÷1፤ 1ዮሐንስ 5÷20)::
4. መጽሐፍ ቅዱስ፣ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል (ሐዋርያት ሥራ 5÷3-4፤ 2ቆሮንቶስ 3÷17-18)::
5. መጽሐፍ ቅዱስ:- አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያየ አካል እንዳላቸው ያስተምራል:: ይህ ማለት:-
   ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ አይደለም ወይም እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም (ሮሜ 1÷7፤ ዮሐንስ 5÷31-32፤ 8÷16-18፤ 3÷16-17፤ ገላትያ 4÷4፤ ዮሐንስ 3÷35፤ 5÷20፤ 14÷31፤ 15÷9፤ 17÷23-26፤ 11÷41-42፤ 12÷28፤ 17÷1-26፤ ማቴዎስ 11÷27፤ ሉቃስ 10÷22፤ ዮሐንስ 7÷29፤ 8÷55፤ 10÷15፤ 1ዮሐንስ 2÷1)::
   ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ አይደለም ወይም መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም (ዮሐንስ 14÷16፤ 1ዮሐንስ 2÷1፤ ዮሐንስ 15÷26፤ 16÷7፤ 16÷13-14፤ ማቴዎስ 28÷19፤ ሉቃስ 3÷22)::
   ሐ. እግዚአብሔር አብ መንፈስ ቅዱስ አይደለም ወይም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ አይደለም (ዮሐንስ 14÷15፤ 15÷26፤ ሮሜ 8÷26-27፤ 28÷19)::

አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሚሉት ስሞች እግዚአብሔር በአካል ሦስት መሆኑን የሚያመለክቱ ሲሆን፣ "እግዚአብሔር" የሚለው ስም ደግሞ ባሕርይን (መለኮትን) ያመለክታል:: ሦስትነቱ አካልን የሚያመለክት ሲሆን፣ አንድነቱ ደግሞ አምላክነትን የሚያመለክት ነው:: እግዚአብሔር **አንድ** ነው ስንል፣ ሦስቱም አካላት የአምላክነት **ባሕርይ** አላቸው ማለታችን ሲሆን፣ ሦስት **አካላት** ናቸው ስንል ደግሞ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የራሳቸው የሆነ **ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት** አላቸው ማለታችን ነው:: ስለዚህ "አንድ" እና "ሦስት" የሚሉትን ቃላት የምንጠቀመው በተለያየ መንገድ ነው:: **አንድነት** አምላክነትን የሚያሳይ ሲሆን፣ **ሦስትነት** ደግሞ አካልን ያመለክታል::

በሌላ አገላለጽ፣ አንድነቱ "ምን" ("what") የሚለውን ሲያመለክት፣ ሦስትነቱን ደግሞ "ማን" ("who") የሚለውን ያሳያል:: ማን ስንል አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያየ አካል እንዳላቸው ያሳያል:: ምን ስንል ደግሞ፣ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ገንዘባቸው ያደረጓቸውን አምላካዊ ባሕርያት (essence) የሚያመለክት ነው::

ልብ ልናደርጋቸው የሚገቡ መሠረታዊ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:-

1. እግዚአብሔር ቊስ አካላዊ ተፈጥሮ (በዐይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ ግዘፍ አካል) የለውም:: አካል የሚለውን ቃል የምንጠቀመው እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት እንዳለው ለማሳየት ብቻ ነው:: መላእክት አካል አላቸው ስንል ይታያሉ፣ ይዳሰሳሉ ወዘተ ማለታችን አይደለም[10]:: መላእክት መናፍስት ናቸው::

---

[10] መላእክት መንፈስ ወይም መንፈሳዊ ፍጥረታት ስለሆኑ (ዕብራውያን 1÷14) ቊሳዊ አካል የላቸውም (ሉቃስ 24÷39):: ከዚህ የተነሣም ብዙውን ጊዜ ለሰው ልጆች አይታዩም:: እግዚአብሔር ፈቃዱን ለሰው ልጆች እንዲያሳውቁ በሚበልግ ጊዜ፣ በቊሳዊ አካል እንዲቀለጡ ልዩ ችሎታ ይሰጣቸዋል፤ በዚህ ጊዜ በሚታይና በሚዳሰስ ቊሳዊ አካል ለሰዎች ይገለጣሉ (ዘኍልቊ 22÷31፤ 2ነገሥት 6÷17፤ ሉቃስ 3÷13፤ ማቴዎስ 28÷5፤ ዕብራውያን 13÷2):: በሚታይና በሚዳሰስ ቊሳዊ አካል ተገለጡ ማለት ግን ቊሳዊ አካል አላቸው ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል:: በነገረ መለኮቱ ዓለም፣ መላእክት ቊሳዊ በሆነ አካል መገለጣቸው "**አንትሮፖሞርፊዝም**" በመባል ይታወቃል:: "**አንትሮፖሞርፊዝም**" የግሪክ ቃል ሲሆን፣ "**አንትሮፖስ**" ማለትም **ሰው** እንዲሁም "**ሞርፌ**" ማለት ደግሞ **መልክ** ማለት ነው::

እግዚአብሔርን እንደ ሰው አድርገን ስንገልጸው [ለምሳሌ:- **ዐይን** (መዝሙር 11÷4፤ ዕብራውያን 4÷13)፣ **ጆሮ** (መዝሙር 55÷1፤ ኢሳይያስ 59÷1)፣ **አፍ** (ዘዳግም 8÷3)፣ **አፍንጫ** (ዘዳግም 33÷10)፣ **ክንፈር** (ኢዮብ 11÷5)፣ **ምላስ** (ኢሳይያስ 30÷27)፣ እጅ

ነገር ግን የራሳቸው የሆነ ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት ስላላቸው አካል አላቸው እንላለን፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ማንነት የሚገለጠው በባሕርይው እንጂ ቊሳዊ በሆነ አካል አይደለም፡፡

2. እግዚአብሔር በቦታ፣ በጊዜና በሁኔታ አይወሰንም፡፡ የእግዚአብሔር ባሕርይ እግዚአብሔርን እንዳንወስነው ያደርገናል፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚገኝ አምላክ ስለሆነ፣ እዚህ ነው ወይም እዚያ ነው ልንለው አንችልም፡፡ በጊዜም ረገድ እርሱ ያልነበረበት ጊዜ የለም፤ የማይኖርበትም ጊዜ የለም፡፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ በአምላክነቱ ጸንቶ ይኖራል፡፡ አንድ አምላካዊ ባሕርይ ብቻም ነው ያለው፡፡

## ትምህርተ ሥላሴን ለማብራራት የምንጠቀምባቸው ምሳሌዎች ትክክል ናቸውን?

---

(ዘፀአት 15÷16)፣ **ጣት** (ዘፀአት 8÷19)፣ **ልብ** (ዘፍጥረት 6÷6)፣ **እግር** (ኢሳይያስ 66÷1) ወዘተ እንዳለው] ወይም በሰባውያን ቋንቋ ስናቀርበው **"አንትሮፖሞርፊክ ቋንቋ"** ይባላል፡፡ እግዚአብሔር ራሱን በዚህ መንገድ የገለጠበት ምክንያት፣ እርሱን በደንብ እንድናውቀው/እንድንረዳው ስለፈለገ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን በሰው አምሳል በመግለጽ ለሰዎች የታየበት ሁኔታ አለ፡፡ ልክ እንደ መላእክቱ ይህ ጊዜያዊ እንጂ፣ እግዚአብሔር ቊሳዊ አካል አለው ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል፡፡ በነገረ መለኮት እግዚአብሔር በሰው መልክ ራሱን መግለጡ፣ **"ቴዎፋኒ"** ይባላል፡፡ **"ቴዎፋኒ"** የሚባለው ይህ የነገረ መለኮት ቃል **"ቴዎስ"** እንዲሁም **"ፋኔሮ"** ከሚሉት ሁለት የግሪክ ቃላት የተገኘ ነው፤ **"ቴዎስ"** ማለት **እግዚአብሔር** ማለት ሲሆን፣ **"ፋኔሮ"** ማለት ደግሞ **መገለጥ** ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ወደዚህች ከመጣ በኋላ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ ሆኖአል፤ እስካሁን ድርስም ሰውና አምላክ ሆኖ አለ (የሐዋርያት ሥራ 17÷31፤ 1ቆሮንቶስ 15÷47 1ጢሞቴዎስ 2÷5)፡፡ አብና መንፈስ ቅዱስ ግን ቊሳዊ አካል የላቸውም፡፡

ትምህርተ ሥላሴን ለማብራራት ይቅርና ለመረዳትም አስቸጋሪ የሚያደርገው እግዚአብሔር ከሰዎች መረዳት እጅግ ስለሚልቅ ነው፤ "የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ ዕውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፤ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም፡፡ የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር?" (ሮሜ 11÷33-34)፡፡ ይህ ማለት ግን ቃለ እግዚአብሔር አስተምህሮውን የገለጠልንን ያህል አናውቅም ማለት አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ይህን አስተምህሮ ለማጥናት የተነሣነው፡፡

በተለምዶ ትምህርተ ሥላሴን ለማብራራት ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ምሳሌዎች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው የሚያመዝን ይመስላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች አስተምህሮውን ለማብራራት በዕንቊላል ምሳሌ ይጠቀማሉ፡፡ ዕንቊላል ሦስት ክፍሎች አሉት እነርሱም ከላይ ያለው ቅርፊት፣ ከውስጥ ያለው ነጭ ፈሳሽና በዕንቊላሉ ማዕከል የሚገኘው አስኳል ናቸው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት አካላት አሉት ይላሉ፡፡ ይህ ገለጻ ትምህርተ ሥላሴን በትክክል አይወክልም፡፡ ምክንያቱም ሦስቱም የአንድ ዕንቊላል ክፍሎች እንጂ፣ በራሳቸው ዕንቊላል አይደሉም፡፡ የሦስቱ ጥምረት ግን ዕንቊላልን ዕንቊላል ያሰኘዋል፡፡ ይህ ግን ሥላሴን በተመለከተ ትክክል አይደለም፡፡ የሥላሴ አካላት በራሳቸው ፍጹም አምላክ ናቸውና፡፡

ሌላው የውሃ ምሳሌ ነው፡፡ የውሃ ምሳሌ ከላይ ከተመለከትነው የዕንቊላል ምሳሌ የተሻለ ቢሆንም፣ ትምህርተ ሥላሴን ለማብራራት ዐቅም ያንሰዋል፡፡ ውሃ ፈሳሽ ሲሆን፣ ስናፈላው ይተናል ስናቀዘቅዘው ደግሞ በረዶ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሦስቱም የውሃ ክፍሎች ናቸው የሚል ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች የለዋወጣቸው የሁኔታው/የአየሩ ጠባይ መቀያየር ነው፡፡ በረዶውን በተወሰነ መጠን ብናሞቀው ውሃ እንዲሁም ብናፈላው ወደ ትነት ይቀየራል፡፡ ይህ ማለት አንዱ ውሃ በሁኔታዎች መቀያየር ራሱን እንደ ቀያየረ እንመለከታልን፡፡ ይህ ገለጻ ሰባልዮሳውያን ስለ ሥላሴ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያሳይ እንጂ፣ ርቱዕ/ትክክልኛ የሆነው ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ሥላሴን የሚያብራራበት መንገድ አይደለም፡፡ በመናፍቁ በሰባልዮስ አስተምህሮ መሠረት፣ የብሉይ ኪዳኑ አብ በሐዲስ ኪዳን ወልድ በበዓለ ኀምሳ ቀን ደግሞ

መንፈስ ቅዱስ ሆኖ ወረደ ብሎ ስለሚያስተምር ይህ ምሳሌ የሰባልዮስን የኑፋቄ ትምህርት የሚያሳይ ነው:: በዛሬ ጊዜ ከዚህ አስተምህሮ ጋር ተቀራራቢ ትምህርት ያለው፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በሚል ስያሜ የሚጠራው ሃይማኖታዊ ድርጅት ነው::

## ትምህርተ ሥላሴ በዓለም ሃይማኖቶችና በመናፍቃን እንዴት ይታያል?

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነውን የሚለው ጉዳይ በስፋት ሲያነጋግር የነበረው በአራተኛው፣ በአምስተኛውና በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው:: በዚህም ምክንያት በርካታ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ተካሂደዋል፤ በተለይ በ325 ዓ.ም የተካሄደው ጉባኤ ኒቂያ፣ በ381 ዓ.ም የተካሄደው ጉባኤ ቈስጠንጥኒያ፣ በ431 ዓ.ም የተካሄደው ጉባኤ ኤፌሶን እንዲሁም በ451 ዓ.ም የተካሄደው ጉባኤ ከልቄዶን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው:: የእነዚህም ከጉባኤዎች አቋም በካቶሊክ፣ በኦርቶዶክስና በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው::

ትምህርተ ሥላሴ የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ክርስትና ከዓለም ሃይማኖቶች ጋርም ሆነ ከመናፍቃን ጋር የሚለያይበት ዳር ድንበር ነው ማለት ይቻላል:: የይሁዲ እምነትና እስልምና እንዲሁም ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ነገር ግን፣ ይህን መሠረተ እምነት የማይቀበሉ በርካታ የሃይማኖት ድርጅቶች አሉ:: እንዲያውም አንዳንዶቹ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ትምህርተ ሥላሴ ከጥንት አረማውያን አስተሳሰብ የተቀዳ ነው የሚል አቋም ሲኖራቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ አስተምህሮውን እንቀበላለን እያሉ ትምህርቱን የሚያብራሩበት መንገድ ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ፈጽሞ የተለየ ነው::

**የይሁዲ ሃይማኖት** የሥላሴን አስተምህሮ አይቀበልም:: በአዲስ ኪዳን ንባባት አይሁዶች ኢየሱስ ራሱን እንደ አምላክ አድርጎ የማቅረቡን ጉዳይ፣ አምላክን እንደ መጻረፍ/መሳደብ አድርገው ነበር የቈጠሩት:: ለምሳሌ በማርቆስ ወንጌል፣ ኢየሱስ የሰውየውን ኀጢአት ይቅር ማለቱ አንዳንድ የአይሁድ የሕግ መምህራንን፣ "ይህ ሰው ስለ ምን እንደዚህ ያለ ስድብ ይናገራል? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኀጢአት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ብለው አሰቡ" (ማርቆስ 2÷7):: በዮሐንስ ወንጌል አንዳንድ አይሁድ ኢየሱስን በድንጋይ ለመውገር የተነሡበትን ምክንያት ሲያብራሩ፣ "ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድርግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት" (ዮሐንስ 10÷33) ይለናል::

**የእስልምና ሃይማኖት** መመሪያ የሆነው ቁርዓን፣ የሥላሴን አስተምህሮ እንደማይቀበል በግልጽ አስፍሮአል:: የሚገርመው ግን ክርስቲያኖች ሥላሴ የሚሉት አብን፣ ኢየሱስንና ማርያምን ነው የሚለው ትምህርቱ ነው፤

> "በትንሣኤ ቀን አላህ እንዲህ ይላል:- የማርያም ልጅ ኢሳ ሆይ! ከአላህ በስተቀር እኔንና እናቴን እንደ ሁለት አምላክ አምልኩ ብለህ ነበርን? እርሱም እንዲህ ሲል ይመልስለታል:- 'ክብር ሁሉ ለአንተ ይሁን! ይህንን ለማለት መብቱ የእኔ አይደለም'" (ቁራን 5÷116-117)::

የአርዮስን[11] ትምህርት በመከተላቸው በርካታ ሰዎች አርዮሳውያን በማለት የሚጠሯቸው፣ ራሳቸውን **የይሖዋ ምስክሮች** ብለው የሚጠሩ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ድርጅት አባላት:-

> ይሖዋ አምላክ በአንድ አካል ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ሥላሴ አይደለም:: በክርስትና እምነት ሃይማኖት አንቀጽ ላይ እንደ ሰፈረው "በእግዚአብሔር አካላት" ውስጥ [ግጻዌ[12] መለኮት ውስጥ] ሦስት እኩል የሆኑ

---

[11] በጉባኤ ኒቂያ ክፉኛ የተወገዘ መናፍቅ ነው:: "ውጉዝ ከመአሪዮስ"ን ልብ ይሏል::

[12] "ግጻዌ መለኮት" በእንግሊዝኛው Godhead የሚለውን ሙያዊ ቃል እንዲወክል ጥቅም ላይ የዋለ (የተቀመረ) ነው:: አንዳንድ ምሁራን ከቋንቋው ትርጉም በመነሣት "ግጻዌ መለኮት" የሚለው የግእዝ ቃል Godhead የሚለውን ሊወክል አይችልም ባይ ናቸው:: "የእግዚአብሔር አካላት" ተብሎ መተርጐሙን ግን አብዛኞቹ

> አካላት የሉም። ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ሳይሆን በይሖዋ አምላክ የተፈጠረ ብቸኛ ፍጡር ነው። እንዲያውም ሊቀ መላእክት ሚካኤል ነው። መንፈስ ቅዱስ አካል የሌለው የአምላክ ፈጣን ኀይል ነው። በእግዚብሔር አካላት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚባለ ሦስተኛ አካል የለም[13]።

ድርጅቱ ትምህርተ ሥላሴን አለመቀበሉ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች በአስተምህሮው ላይ የተሳሳተ ግንዛቤና ጥላቻ እንዲያድርባቸው እንዲሁም አስተምህሮውን አንዲያወግዙት በኅብረ ቀለማት የተዋቡ በርካታ ጽሑፎችን በተለያዩ ቋንቋዎች በከፍተኛ ቍጥር ዐትሞ በብዙ ቦታዎች በማሠራጨት ከፍተኛ ቅስቀሳ ያካሂዳል። የሚገርመው ግን ድርጅቱ የሥላሴ አማኒያን እምነት ነው ብሎ የሚያሠራጫቸው መረጃዎች በአብዛኛው፣ የሥላሴ አማኒያን ከሚያምኑት የሥላሴ መሠረተ ትምህርት ጋር የማይጣጣም መሆኑ ነው[14]።

---

ይስማሙበታል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንበት፣ "የእግዚአብሔር አካላት" የሚለውን ሙያዊ ቃል ነው።

[13] *በሥላሴ ማመን ይገባሃል?* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1993). እንዲሁም *ከቅዱስን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1994), 197-198, 212-221, 403-427 የሚሉትን የድርጅቱን መጻሕፍት ይመለከቷል።

[14] በዚህ ረገድ ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ በግርጌ ባስታወሻው ቍጥር 12 ላይ የተጠቀሱትን የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር መጻሕፍት እንዲሁም ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤* ራዕይ አሳታሚ ድርጅት፤ 1991 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ በሚል ርእስ የታተመውን መጽሐፍ ይመለከቷል። በተለይ ገጽ 74-91። የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር *በሥላሴ ማመን ይገባሃል?* በሚል ርእስ ላሳተመው መጽሐፍ ምላሽ ይሆን ዘንድ Robert M. Bownam, Jr. *Why You Should Believe In The Trinity* በሚል ርእስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ምላሽ ሰጥቶአል። ይህን የRobert M. Bownam, Jr. መጽሐፍ አቶ ካሱ በላቸው *በሥላሴ ማመን አይገባህምን?* በሚል ርእስ ወደ አማርኛ ቋንቋ መልሶታል። ድርጅቱ ትምህርተ ሥላሴን አስመልክቶ የሚያሠራጨውን የተዛባ አመለካከት በቃለ እግዚአብሔር፣ በታሪክና በሥነ አመክንዮ በማረቅ/በማስተካከል ረገድ ይህ መጽሐፍ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው።





የሰባልዮስ[15] መንፈሳዊ ልጆች ነን የሚሉት[16] እንዲሁም፣ **"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"** በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት ተከታዮች ደግሞ፣ ስለ ሥላሴ እንዲህ የሚል አስተምህሮ አላቸው፦

> "መለኮት ከዘላለም በአካል፣ በባሕርይ፣ በስም፣ በግብር አንድ እንጂ ሁለት ወይም ሦስት አልነበረም። በሦስት መንገድ ግን ራሱን ለሕዝቡ ገልጾአል። በሦስት መንገድ የተገለጸበትም ምስጢር በአብነት በሥጋ ዐይን ሳይታይ፣ በወልድነት በሥጋ እየታየ፣ በመንፈስ ቅዱስነት እስትንፋሱን በሕዝቡ ልብ ውስጥ በማሳደሩ ተገልጦአል"[17]። "ከጥንት ከዘላለም እግዚአብሔር ወይም መለኮት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በመባል በሦስት አካላት ተከፋፍሎ አይጠራም ነበር"[18]። "[ኢየሱስ] የመለኮት አካል እንዲሆን የተዘጋጀ ሰው ነው"[19]። "ይህ ሕፃን ሆኖ የተገለጠው አብም ወልድም ነው። ሙሉ አምላክና ሙሉ ሰውም ነው...አብ ሰው ሆነ ማለት ሳይሆን አብ በሥጋ ተገለጠ ማለት ነው"[20]።

---

[15] ሰባልዮስ (Sabellius) በፊት በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ (ከአሪዮስ በፊት ማለት ነው) በተሳሳተ ትምህርቱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን መናፍቅ ብላ ያወገዘችው ሰው ነው።

[16] በኢትዮጵያ፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀውን ሃይማኖታዊ ድርጅት የመሠረተውና የድርጅቱ የበላይ ተጠሪ የሆነው ተክለማርያም ገዛኽኝ፣ "*ኢየሱስን ማን ይሉታል?*" በሚል ርእስ በታተመው መጽሐፉ (ገጽ 4 ላይ) እርሱም ሆነ እርሱ በበላይነት የሚያስተዳድረው ሃይማኖታዊ ድርጅት፣ የሰባልዮስን አስተምህሮ እየተከተለ እንዳለ ይፋ አድርጎአል።

[17] ተክለማርያም ገዛኽኝ፤ *ኢየሱስን ማን ይሉታል?* (1978 ዓ.ም) ገጽ 4።

[18] ዝኒ ከማሁ ገጽ 10። ድርጅቱ "አካል" የሚለውን ሙያዊ ቃል የሚያብራራው ቍስ አካልን በሚያመለክት መልኩ ነው። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን በዚህ መልኩ እንደማትጠቀምበት ልብ ይሏል።

[19] ዝኒ ከማሁ ገጽ 19፤ በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።

[20] ዝኒ ከማሁ ገጽ 40።

በአጠቃላይ ይህ የሃይማኖት ድርጅት በሥላሴ ላይ ያለው አስተምህሮ የሚከተለውን ይመስላል፤

> "እግዚአብሔር አምላክ በዐይነ ሥጋ ሳይታይ መንፈስ ሆኖ ይኖር ነበር። ኋላ ግን ቃሉን ሥጋ ማለትም ኢየሱስ በማድረግ ኢየሱስ በተባለው ሥጋ ውስጥ ዐደረ። ኢየሱስ በተባለው ሰው ውስጥ ካደረው አምላክ የሚወጣው እስትንፋስ ደግሞ ቅዱስ መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ ይባላል። ስለዚህ አብ ማለት፣ ኢየሱስ በተባለው ሥጋ ውስጥ ያደረው አምላክ ሲሆን፣ ወልድ ደግሞ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ነው። የአብ እስትንፋስ ወይም ትንፋሽ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው"[21]።

**የ"ሞርሞን" እምነት ወይም "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ዘመን ቅዱሳን"** በሚል ስያሜ፣ ወርኀ ሚያዝያ 1830 ዓ.ም በአሜሪካን አገር የተጀመረውን ሃይማኖት የመሠረተው ጆሴፍ ስሚዝም ሆነ ተከታዮቹ፣ የሥላሴን አስተምህሮ እንቀበላለን ይበሉ እንጂ፣ ስለ ሥላሴ ያላቸው አስተምህሮ ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር የሚቃረን ነው። ለምሳሌ:- "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦች እንደሆኑት ሰብአዊ ፍጡራን፣ የተለያዩ አካላት ናቸው"[22]። ድርጅቱ በሥላሴ አካላት መካከል ያለው አንድነት የዐላማና የስምምነት ብቻ እንደ ሆነ ይገልጻል[23]።

ልክ እንደነዚሁ ሁሉ፣ ሜሪ በከር ኤዲ በምትባል አሜሪካዊት ሴት የተመሠረተውና "ክርስቲያን ሳይንስ" በሚል ስያሜ የሚታወቀው የሃይማኖት ድርጅት፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ እንዳስተማረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው"[24]። ይህቺ ሴት ትምህርት፣ ኢየሱስ "የእግዚአብሔር ልጅ" መሆኑ ከአብ ጋር እኩል አያደርገውም የሚለውን አስተሳሰብ ታሳቢ እንዳደረገ ልብ ይሏል።

## ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ስለ ሥላሴ ምን ይላሉ?

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከውልደቷ ጀምሮ በዚህ ምድር በኖረችባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ ህልውናዋን የሚፈታተኑ በርካታ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች ገጥመዋታል። በአንጻራዊነት ሲታይ፣ አንዳንዶቹ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ሲያገኙ፣ አንዳንዶቹ ግን በየትኛውም የታሪክ ዘመን ሳያጨቃጭቁ ያለፉበት ጊዜ የለም ማለት ይቻላል። ከእነዚህ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች ውስጥ ትምህርተ ሥላሴ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል ቢባል እብለት አይሆንም። በየዘመናቱ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ የተረዱት አስተምህሮ ነውና።

የትምህርተ ሥላሴ ቀዳማይ አመንጪ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም፣ በሐዋርያት እግር ሥር የተማሩ ቀደምትም ሆኑ ደኅርት[25] የቤተ ክርስቲያን አበው ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ ምን አሉ የሚለውን ጉዳይ መቃኘት፣ የተዛባ የታሪክ መረጃ ያላቸውን ሰዎች ለማቅናት ጠቀሜታ ስላለው፣ ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን በአማኝነት እናቀርባለን።

---

[21] ተስፋዬ ሮበሌ፤ *ዐበይት መናፍቃን*፤ ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን: ብራና ማተሚያ ድርጅት፤ 1993 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ። ገጽ 143።

[22] Alan W. Gomes, *Unmasking the Cults* (Grand Rapids: Michigan, 1995), 25 ከ James Talmage, *A Study of Articles of Faith* (Salt Lake City: The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1976), አንቀጽ 1 ገጽ 29-51 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[23] ዝኒ ከማሁ።

[24] Gomes, 26 ከMary Baker Eddy, *Science and Health with Key to the Scriptures* (Boston Trustees Under the Will Mary Baker G. Eddy, 1934), 361 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[25] ደኅርት ማለት ኋለኛ፣ የኋላ፣ ታናሽ፣ ተከታይ ወዘተ ማለት ነው።

ትምህርተ ሥላሴን እንደ አርዮስ ካሉ የመናፍቃን ጥቃት በመጠበቁ ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ የነበረው አትናቴዎስ (Athanasius) ቢሆንም፣ ርእሰ ጉዳዩን በጠለለና በዳበረ መልኩ ያቀረቡት ቀጰዶቃውያን አበው[26] ናቸው::

በርካታ ሰዎች በተለይ መናፍቃን፣ ትምህርተ ሥላሴ ከቃለ እግዚአብሔር የተቀዳ ሳይሆን፣ ከጉባኤ ኒቂያ በኋላ[27] የመጣ ባዕድ አስተምህሮ ነው የሚል አመለካከት አላቸው:: ጉባኤ ኒቂያ በሮማው ቄሳር ቈስጠንጢኖስ[28] ተጠርቶ፣ የአንድ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበረው አርዮስ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር በሁሉ ነገር ትክክል አይደለም" የሚለውን ትምህርቱን ለመመርመር የተቀመጠ ጉባኤ ነው::

ጉባኤው አርዮስን አውግዞና ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው የሚለውን መሠረተ እምነት አጽንቶ ያለፈ ጉባኤ ቢሆንም፣ አንዳንድ ሰዎች ትምህርተ ሥላሴ ከኒቂያ ጉባኤ በፊት አልነበረም የሚል የተሳሳተ ግንዛቤና ሙግት አላቸው:: ጉባኤ ኒቂያ ብሉያትንና ሐዲሳትን እያጣቀሰ አስተምህሮውን ደርዝ ባለው መልክ ያብራራ ጉባኤ እንጂ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተቀመጠውን ትምህርት ያስተላለፈ ጉባኤ ላለመሆኑ ታሪክን በመጥቀስ እማኝ በማፈላለግ ይህን የተሳሳተ የታሪክ ግንዛቤ፣ የታሪክ እማኝ በማቅረብ ስሕተቱን ማጋለጥ አግባብ ስለሚሆን፣ ከጉባኤ ኒቂያ በፊት የነበሩትን የቤተ ክርስቲያን አበው በርእሰ ጉዳዩ ላይ ምን ብለው ዐለፉ የሚለውን ጉዳይ በአስረጅነት ለማቅረብ እሞክራለሁ:: ይህ ጽሑፍ ዳሰሳዊ ጥናት ስለሆነ፣ የሁሉንም አበው እማኝነትና ትምህርት በስፋት ማቅረብ ስለማይቻል፣ የጥቂቶቹን ብቻ በናሙናነት ቈንጥረን በመውሰድ እናቀርባለን:: ይህን የምናደርገውም የእነዚህን አበው ጽሑፍ በቀጥታ በመተርጐም ነው::

**ፖሊቃርጶስ** (Polycarp) በ70 ዓ.ም ተወልዶ በ155 ዓ.ም ወይም ደግሞ 160 ዓ.ም የሞተ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረ እንዲሁም የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት የነበረ ሰው ነው:: ይህ ሰው ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ እንዲህ ብሏል:-

- "ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ሆይ…ዘላለማዊና ሰማያዊ በሆነው ሊቀ ካህናት በምትወደውና ባከበርኸው ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለአንተና ለእርሱም እንዲሁም ለመንፈስ ቅዱስ ለአሁንም ሆነ ለዘላለም ክብር ይሁን" (n. 14, ed. Funk; PG 5.1040).

**ዮስጦስ ሰማዕት** (Justin Martyr)፣ የቤተ ክርስቲያን ዐቃቤ እምነት[29] የነበረና የሰማዕትነትን ክብር የተቀዳጀው ይህ አባት በ100 ዓ.ም ተወልዶ 165 ዓ.ም

[26] ቀጰዶቃውያን አበው (Cappadocian Fathers) የሚባሉት፣ የቂሳርያው ትልቁ አባት ባስልዮስ (Basil The Great)፣ ጐርጐርዮስ ዘእንዚናዙ (Gregory of Nazianzus) እንዲሁም ጐርጐርዮስ ዘኑሲስ (Gregory Nyssa) ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ስም የምንጠቅሰው፣ የጥንት ብራና መጻሕፍት በሚጠቀሙበት መንገድ ነው:: የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዐውዳዊ ነገረ መለኮት (contextualize theology) የሚለውን ጉዳይ ትኩረት የሚሰጡበት እስከ ሆነ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ስያሜ በተመለከተ ትልቅ ትኩረት ሊሰጡበት የሚገባ ይመስለኛል::

[27] ጉባኤ ኒቂያ በጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 325 ዓ.ም በጁሊያን የዘመን አቈጣጠር 318 ዓ.ም የተካሄደ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው::

[28] በወቅቱ የአገረ ሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረ::

[29] ዐቃቤ እምነት/ክርስትና የሚለው ስያሜ (Apologetics) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚወክል ነው:: በግእዝ ዐቃቢ ማለት የሚጠብቅ፣ ጠባቂ፣ ተመልካች፣ ከልካይ ማለት ነው:: ዐቃቤ ክርስትና የሚባሉት የክርስትናን መሠረተ እምነት ከመናፍቃን እንዲሁም ክርስቲያናዊ ካልሆኑ የተለያዩ የስሕተት ትምህርቶች/ሒሶች የሚጠብቁ ሰዎች ናቸው::

"አፖሎጂቲክስ" (apologetics) ይሚለው የእንግሊዝኛ ስያሜ የተወሰደው "አፖሎጂያ" ወይም "አፖሎጂዮ" ከሚለው የግሪክ ቃል ነው:: አፖሎጂያ የሚለው ቃል በ1ጴጥሮስ 3÷15 ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ሁሉም የአማርኛ ትርጉሞች (የ1954፣ የ1980 እንዲሁም የአዲሱ መደበኛ ትርጉም) "መልስ መስጠት" ብለው ተርጉመውታል:: በአብዛኛው ይህ ክፍል ለዐቃቤ ክርስትና መሪ ጥቅስ ተደርጎ ይወሰዳል:: የዐቃቤ ክርስትና ዐቢይ ዐላማ፣ ክርስቲያናዊ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ምክንያታዊ/ምክንዩአዊ ለመሆኑ

እንደ ሞተ ይገመታል። ይህ አባት ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ እንዲህ ብሏል:-

- *“የዓለማት ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር በስመ አብ፣ በመድኀኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ በውሃ መታጠብን ያገኛሉ”* (First Apol., LXI).

**አግናጢዮስ ዘአንጾኪያ** (Ignatius of Antioch) የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት የነበረና በ98 ዓ.ም ወይም በ117 ዓ.ም እንደ ሞተ የሚገመት ክርስትናን ከመናፍቃን በመከላከሉ ዙሪያ ብዙ የጻፈ ዐቃቤ ክርስትና ነው:-

- *“ጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ፣ ለእርሱና በእርሱ በኩልም ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ክብርና ኀይል ለዘላለም ዓለም ይሁን”* (n. 7; PG 5.988)።

**ጠርጡሊያኖስ ወይም ተርቱሊያኖስ** (Tertullian 160-215) አፍሪካዊ ዐቃቤ ክርስትና እንዲሁም የነገረ መለኮት ሊቅ ነው። ክርስትናን ከመናፍቃንና ከሌሎች ሐያስያን ለመከላከል ብዙ ጽፎአል።

- *“አብና ወልድ ሁለት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ደግሞ ሦስት መሆናቸውን እንገልጻለን። የቀጥሩም ቅደም ተከተል ከድኅነት/ድነት አንጻር ነው. . .ይህም አንድነትንና ሦስትነትን መሠረት አድርጎ ሦስቱንም ማዕከል ያደረገ ነው፤ እነርሱም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ። [አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ] ሦስት ናቸው. . .ነገር ግን በባሕርይ ሳይሆን በገጽ፤ በኀይል ሳይሆን ነገር ግን በዐይነት። በባሕርይና* (substance) *በኀይል አንድ ናቸው፤ ምክንያቱም አንድ አምላክ ብቻ ስላለና ይህም ባሕርይ፣ ገጽና ዐይነት በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ዙሪያ ያለ በመሆኑ”* (Adv. Prax. 23; PL 2.156-7፣ *የመጀመሪያውን ቅንፍ አይጨምርም*)

**አርጌንስ** (Origen 185-254) የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁር ነው። አርጌንስ ክርስትናን ከተለዩ ሐያስያን የተከላከለና ክርስትናን በተመለከተ ብዙ የጻፈ ሰው ነው።

- *“የእግዚአብሔር ቃል ወይም የእግዚአብሔር ጥበብ ጅማሬ አለው የሚል ማንኛውም ሰው፣ ቢያንስ እግዚአብሔርን መናቁ እንደ ሆነ ልብ ሊለው ይገባል. . .ምክንያቱም እግዚአብሔር ባለፉት ዓመታትም ሆነ ዘመናት ወይም ከዚህ ውጪ ሊገመት በሚችልበት ጊዜ ሁሉ፣ እግዚአብሔር የጥበብ ባለቤት ነውና . . . ይህ እውነት ለእግዚአብሔር አብ እንደ ሆነው ሁሉ ለወልድም ነው”* (De Princ. 1.2.; PG 11.132)።
- *“እውነታው ይህ ከሆነ [መንፈስ ቅዱስ አሁን እንደ ሆነው ሁሉ ዘላለማዊ ካልሆነ፣ በዘመናት ውስጥ ዕውቀትን ገብይቶ መንፈስ ቅዱስ መሆን ከቻለ] መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ዓለም መንፈስ ቅዱስ መሆን ካልቻለ፣ እንደማይለወጠው አብና እንደ ልጁ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ አንዱ አካል ነው ማለት አይቻልም”*[30]
- *“የመለኮት ምንጭ ብቻ ሁሉን ነገር በቃሉና በምክንዩው የሚይዝ ከሆነ፣ በሥላሴ አካላት ውስጥ መበላለጥ ወይም መተናነስ የለም”*[31]

**ሔሬኔዎስ** (Irenaeus) በ115 ዓ.ም ተወልዶ 190 ዓ.ም የሞተ፣ በልጅነቱ የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ከነበረው ከፖሊካርጶስ የተማረ እንዲሁም የልዮን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት የነበረ ሰው ነው:-

---

ማስረጃ ማቅረብ ነው። አፖሎጂያ የሚለው የግሪክ ቃል በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥም ተጠቅሶ ይገኛል (ሐዋርያት ሥራ 22÷1፣ 25÷16፣ 1ቆሮንቶስ 9÷3፣ 2ቆሮንቶስ 7÷11፣ ፊልጵስዩስ 1÷7:16፣ 2ጢሞቴዎስ 4÷16)።

[30] Alexander Roberts and James Donaldson, eds., *The Ante-Nicene Fathers,* Grand Rapids: Eerdmans, 1975 rpt., Vol. 4, p. 253, de Principiis, 1.111.4

[31] Roberts and Donaldson, *Ante-Nicene Fathers,* Vol. 4, p. 255, de Principii., I. iii. 7

- “ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ እንዲሁም እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ብትበተንም፣ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያትና ከእነርሱ ደቀ መዛሙርት የተቀበለችው የሚከተለውን መሠረተ እምነት ነው፡- ሁሉን ቻይ የሆነና ሰማይንና ምድርን እንዲሁም ባሕርን በእነዚህም ውስጥ የሚኖሩትን ሁሉ የፈጠረ አንድ እግዚአብሔር፤ በእግዚአብሔር ልጅ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ ለድነታችን ሲል ትስብእት የሆነ፤ በመንፈስ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔርን ዘመን በነቢያቱ ያበሠረ እንዲሁም የተወዳጁ ጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት፣ ከድንግል መወለድ፣ ሕማም፣ ከሙታን መነሣት፣ በአካለ ሥጋ ወደ ሰማይ ማረግ፣ ‘ሁሉን አንድ አድርጎ ለመሰብሰብ’ በአብ ክብር ከሰማይ መገለጥ፣ የሰው ልጆችን ሁሉ በአዲስ አካል ከሙታን ማስነሣት፣ ይኸውም ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታችንና አምላካችን እንዲሁም አዳኛችንና ንጉሣችን መሆኑን፣ በማይታየው አብ ፈቃድ ‘በሰማይና በምድር ከምድርም በታች’ ያለ ጉልበት ሁሉ እንዲንበረከክለት፣ ምላስም ሁሉ ለሁሉ ኀጢአት ብሎ እንደ ተሰዋ እንዲመሰክርለት ነው. . .” (Against Heresies X.l)፡፡

ከጉባኤ ኒቂያ በፊት የነበሩት እነዚህ የእምነት አባቶች እንዲህ ዐይነት እምነት ያላቸው ከሆነ፣ የአስተምህሮው ቀዳማይ አመንጪ ጉባኤ ኒቂያ ሳይሆን ቃለ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው፡፡ የሥላሴ አስተምህሮ ጠንሳሽ የኒቅያ ጉባኤ ቢሆን ኖሮ፣ ክርስቲያኑ ማኀበረሰብ ከቀድሞው አስተምህሮ ጋር የማይጣጣም ነው በሚል ተቃውሞውን ለምን አላቀረበም? እንዲህ ዐይነቱ ተቃውሞስ በታሪክ ለምን አልተዘገበም?

## ለትምህርተ ሥላሴ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብን እንጠቀም?

የትምህርተ ሥላሴን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ለመመርመር፣ ትክክለኛ የሆነውን የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ዘዴ[32] በትክክል ማወቅ እንዲሁም ይህን ዘዴ በትክክል ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የምናያቸውን መርሖች በሚገባ ልናውቃቸውና ቃለ እግዚአብሔርን በምናጠናበት ጊዜ ሁሉ ልንጠቀምባቸው የሚገቡ ናቸው፡፡ እነዚህን መርሖች ማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ እንዳንተረጉም፣ ራሳችንን ከመናፍቃን እንቅስቃሴ እንድንጠብቅ እንዲሁም በተሳሳተ እምነት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት እንድናመጣቸው ታላቅ ዕገዛ አለው፤ በተለይ ደግሞ ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ፡፡ እነዚህ መርሖች ዘመናዊው ሥልጣኔ የወለዳቸው ወይም ዘመን አመጣሽ አይደሉም፡፡ ዘመንኛው ዓለም እነዚህን መርሖች በተፍታታና አእምሮ በሚጨብጠው መንገድ ይግለጻቸው እንጂ፣ መርሖቹ መጽሐፍ ቅዱስ በነበረበት ዘመን ሁሉ የነበሩ፣ የጥንት የቤተ ክርስቲያን አበው በጽሑፎቻቸውም ሆነ በትምህርታቸው ወቅት የተጠቀሙባቸው መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ ለምሳሌ ሔሬኔዎስ (Irenaeus)

---

[32] የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ዘዴ/ጥበብ (Hermeneutics)፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሓፍያን ለቀዳማይ ተደራስያኑ ያስተላለፉት መልእክት ምን ነበረ እንዲሁም ተደራስያኑ መልእክቱን የተረዱት እንዴት ነበረ የሚለውን ጉዳይ በመመርመር፣ የመልእክቱን ትክክለኛ ትምህርት ነቅሰን የምናወጣበት የጥናት ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ክፍል አንኳር አንኳር የሚባሉትንና የምንነጋገርበትን ርእሰ ጉዳይ በትክክል እንድንመረምረው ይጠቅሙናል ያልኋቸውን የአፈታት መርሖች በአጭሩ አቀርባለሁ፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልጉ ከሆነ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ አባሪ 4 “ሥነ አፈታትን አስመልክቶ ተዘውትረው የሚታዩ ችግሮች” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ፡፡ እንዲሁም ተስፋዬ ሮበሌ *የሥነ ምግባር መርሖ* በሚል ርእስ ካዘጋጀው መጽሐፍ ገጽ 127-142 ያለውን ክፍል ይመለከቷል፡፡ ወይም Gordon D. Fee & Douglas Stuart, *How to Read the Bible For All Its Worth: A Guide to Understanding the Bible* (Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1993) የተባለው መጽሐፍ በዚህ ረገድ ለጀማሪ አንባብያን ታላቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህ የ Fee እና Stuart መጽሐፍ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞአል፡፡

ኖስቲሲስምንና ሌሎች ስሕተት ትምህርቶችን በተመለከተ “**ኑፋቄን መከላከል**” በሚል ርእስ በጻፈው መጽሐፍ እነዚህን መርሖች ተጠቅሞባቸዋል::

### 1. የአገባብ መርሖ

አንድን የተወሰነ ቃል ወይም ሐረግ መፍታት የሚኖርብን፣ መልእክቱ በተጻፈበት **ወቅት** በሚሰጠው ትርጒም በተለይ ደግሞ በዚያ **ማኅበረሰብ** ውስጥ ምን ትርጒም በመወከል ያገለግል ነበር በሚለው መሠረታዊ ነጥብ ነው::

### 2. የዐውድ መርሖ

ቃላትን ከሚገኙበት **ዐውድ** አላቄ/ገንጥሎ መተርጐም ስሕተት ነው:: ዐውድ የቃልን ትርጒም ይወስናልና:: መጽሐፍ ቅዱስ የተለያየ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ያላቸው መጻሕፍት መድበል መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህ መጻሕፍት እንደማንኛውም የታሪክ ወይም የልብ ወለድ መጻሕፍት ዐውዳቸውን ጠብቀው የተሰተሩ/የተደረደሩ ጽሑፎች መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም::

### 3. የታሪካዊ ዳራ መርሖ

አንድን ቃል ወይም ሐረግ ከ**ታሪካዊ** ግኝት/እውነታ አፋቶ መተርጐም ስሕተት ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍትን መተርጐም የሚኖርብን፣ የታሪክ ጥናት በማያሻማ መልኩ ግልጥ ያደረገልንንና መልእክቱ በተጻፈበት ጊዜ የነበረውን እውነታ ታሳቢ ባደረገ መንገድ ነው::

### 4. የነባር አገባብ መርሖ

ቃላትን መተርጐም ያለብን ከዚህ በፊት ይሠራበት ከነበረውና ተቀባይነት ካገኘው ትርጒም አንጻር እንጂ፣ **ስውር** የሆነን ትርጒም/ፍቺ በማፈላለግ መሆን የለበትም:: በተለይ የሚከተሉት ሁለት መርሖች ለጥናታችን ትልቅ ዕገዛ ስላላቸው በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርገን እንመለከታቸዋለን::

### 5. ጠንካራ ምንባባትን ከግልጥ ምንባባት አንጻር የመተርጐም መርሖ

ስውር ከመሆናቸው የተነሣ ለመፍታት አስቸጋሪ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት፣ ግልጽና ለፍቺ ቀና የሆኑት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሚያስተምሩት ትምህርት አንጻር መመልከት/ማብራራት አስፈላጊ ነው:: ግልጽና ለመፍታት ቀና ናቸው የምንላቸው እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ያላቸው አስተምህሮ መሠረታዊ እንዲሁም የማያሻማ ትምህርት ያላቸው ሲሆኑ፣ ከምንነጋገርበት ርእሰ ጒዳይ ጋር በቀጥታም ባይሆን ተዘዋዋሪ በሆነ መልኩ ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው:: ለምሳሌ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂ አምላክ እንደ ሆነ በማያሻማ መንገድ ያስተምራሉ፤ ይኸውም እግዚአብሔር የሰዎችን አስተሳሰብ፣ መጪውን ዘመን እንዲሁም ማናቸውንም ነገሮች ከመሆናቸው በፊት አስቀድሞ ያውቃል (1ሳሙ. 16÷7፤ 1ዜና. 28÷9፡ 17፤ ኢዮ. 37÷16፤ መዝ. 139÷1-4፤ ኢሳ. 41÷22-23፤ 42÷9፤ 44÷7፤ ኤር. 17÷10):: ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ እግዚአብሔር የማያውቃቸው ነገሮች አሉ (ለምሳሌ፡- ዘፍ. 3÷9-13፤ 4÷9፤ 18÷9፡ 20-21) የሚሉ ከሚመስሉ ክፍሎች ላይ በበላይነት መታየት አለባቸው::

### 6. የሥነ አመክንዮ (Logic) መርሖ

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች የምናብራራው የሥነ አመክንዮ ሕግጋትን በመከተል ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍትን በምንተረጒምበት ውቅት፣ በርካታ የሥነ አምክንዮ መርሖችን መጠቀም የሚኖርብን ሲሆን፣ በተለይ የሚከተሉት ሁለት ነጥቦች መሠረታዊ ናቸው:- **ሀ)** የተወሰኑ ቃላት ወይም ሐረጐች መተርጐም የሚኖርባቸው፣ ከአብዛኞቹ እውነታዎች ጋር **መጣጣም** በሚችሉበት መንገድ ብቻ ነው፤ ቃለ እግዚአብሔር እርስ በርሱ አይጣረስምና/አይጋጭምና:: **ለ)** አንድን ሙግት ወይም አስተምህሮ ማዋቀር ያለብን፣ በፊት ከሚታወቀውና **እውነትነቱ ከተረጋገጠው** ወይም ደግሞ ምክንያታዊ የሆነ እንድምታ ካለው እውነት በመነሣት ነው::

ከላይ የተመለከትነውን ማስረጃ በዚህም ቦታ ላይ በመጠቀም ነገሩን ግልጽ ለማድረግ እንሞክር፤ እግዚአብሔር አንድ ነገር ከመከሠቱ በፊት አስቀድሞ ስለዚያ ነገር ጠንቅቆ የሚያውቅ ከሆነ፣ አዳምና ሔዋን በኀጢአት እንደሚወድቁ ያውቃል ማለት ነው:: እግዚአብሔር ጒዳዩን አስቀድሞ የሚያውቅ ከሆነ፣ “ሰዎች በኀጢአታቸው ምክንያት ሊጠየቁ ይገባል?” የሚል ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል:: “ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ሁሉን በማወቅ ችሎታው ተጠቅሞ ችግር ውስጥ እንዳይገቡ ለምን አላደረጋቸውም” የሚል ጥያቄ ሊያመጣ ይችላል:: እግዚአብሔር በኀጢአት እንደሚወድቁ አስቀድሞ ያውቃል፤ ነገር ግን በኀጢአት እንዳይወድቁ ለምን አላደረገም የሚለው ጥያቄ እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ከሚለው እውነት ጋር በሥነ አመክንዮ ሕግ

የሚጋጭ አይደለም:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ ትምህርተ ሥላሴ ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንጻር መታየት ይኖርበታል::



# የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ
## ቅዱሳዊ መሠረት—ተዋዕአአዊ[33] ጥናት[34]



## I. እግዚአብሔር አንድ ነው (አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ)

### ሀ. እግዚአብሔር አንድ ነው

1. ብሉያት፡- ዘዳ. 4÷35፤ 39፤ 32÷39፤ 2ሳሙ. 22÷32፤ ኢሳ. 37÷20፡ 43÷10፤ 44÷6-8፤ 45÷5፤ 14፤ 21-22፤ 46÷9::

2. ሐዲሳት፡- ዮሐ. 5÷44፤ ሮሜ 3÷30፤ 16÷27፤ 1ቆሮ. 8÷4-6፤ ገላ. 3÷20፤ ኤፌ. 4÷6፤ 1ጢሞ 1÷17፤ 2÷5፤ ያዕ. 2-19፤ ይሁዳ 25::

### ለ. እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም (በማንነት/በባሕርይ [በጥንተ ባሕርይው በአኗኗሩ])

1. ግልጽ የሆኑ ዐረፍተ ነገሮች፡- ዮሐ. 8÷10፤ ሮሜ 9÷14፤ 15÷11፤ 2ሳሙ. 7÷22፤ 1ነገሥ. 8÷23፤ 1ዜና 17÷20፤ መዝ 86÷8፤ ኢሳ 40÷18:25፤ 44÷7፤ 46÷5:9፤ ኤር. 10÷6-7፤ ሚክ 7÷18::

2. "እንደ እግዚአብሔር መሆን" ማለት የሐሰት አበት ከሆነው ከሰይጣን ዲያብሎስ የተገኘ ውሸት ነው፡- ዘፍ. 3÷5፤ ኢሳ. 14÷14፤ ዮሐ. 8÷44::

3. "እንደ እግዚአብሔር እሆናለሁ" ሲል ወደ ላይ የተንጠራራው ሰው፣ በራሱ ላይ ያመጣው "ክፉና ደጉን ማወቅን እንጂ" እግዚአብሔርን መሆን አልነበረም፡- ዘፍ 3÷22::

**ሐ. አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ አለ፡- 2ዜና 15÷3፤ ኤር. 10÷10፤ ዮሐ. 17÷3፤ 1ተሰ. 1÷9፤ 1ዮሐ. 5÷20-21::**

**መ. አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ ካለ "አማልክት"[35] የተባሉት ሁሉ እውነተኛ አማልክት አይደሉም፡- ዘዳ. 32÷21፤ 1ሳሙ. 12÷21፤ መዝ. 96÷5፤ ኢሳ. 37÷19፤ 41÷23-24:29፤ ኤር. 2÷11፤ 5÷7፤ 16÷20፤ 1ቆሮ. 8÷4፤ 10÷19-20::**

**ሠ. ስለዚህ "አማልክት" የተባሉት ሁሉ ከሐሰተኛ አምልኮዎች ጀርባ የሚሠሩ አጋንንት ናቸው እንጂ አምላክ አይደሉም፡- ዘዳ. 32÷17፤ መዝ. 106÷37፤ 1ቆሮ. 10÷20፤ ገላ. 4÷8::**

### ረ. ሰዎች "እግዚአብሔርን የሚመስሉት" እንዴት ነው?፡-

1. ሰዎች "እግዚአብሔርን ይመስላሉ" ወይም "አምሳለ መለኮት ናቸው" ሲባል፣ የእግዚአብሔርን ግብረገባዊ ባሕርይ ተካፋዮች ናቸው ማለት እንጂ፣ አምላካዊ የሆነ የእግዚአብሔር ባሕርይ አላቸው ማለት አይደለም፡- ዘፍ. 1÷26-27፤ 5÷1፤ 1ቆሮ. 11÷7፤ ኤፌ. 4÷24፤ ቈላ. 3÷10::

---

[33] የግርጌ ማስታወሻ 1 ይመለከቷል::

[34] ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው፣ Robert M. Bownam, Jr. በባዮላ ዩኒቨርስቲ ሲያስተምሩ ለተማሪዎቻቸው ከሰጡት ጽሑፍ ነው:: Robert ጽሑፉን በዚህ መጽሐፍ እንድጠቀምበት ስለፈቀደልኝ ምስጋናዬ ትልቅ ነው:: ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ Rob:: በአገልግሎትህ ብዙ እየተጠቀምን ስለሆነ፣ እግዚአብሔር አገልግሎትህን ይባርክ::

[35] "አምላክ" የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ስለሆነ፣ የግእዙን ሰዋስው ተከትለን ስናረባው አማልክት ይሆናል:: አምላኮች የሚለው ግን ጸያፍ አረባብ ነው (እንደ ቀደምቶቹ የአማርኛ ቋንቋ ምሁራን ማለቴ ነው):: ግእዝን በአማርኛው የቃላት አረባብ መንገድ አርብተነዋልና::

2. "ክርስቶስን መምሰል" ማለት የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች የሚያሳይ እንጂ፣ እንደ እርሱ አምላክ መሆን ይቻላል የሚል ትምህርት የለውም:-

ሀ) የግብረገባዊ ባሕርይው ተካፋይ መሆን:- 1ዮሐ. 3÷2፤ ሮሜ. 8÷29::

ለ) ልክ እንደ እርሱ በክበረና በማይሞት የትንሣኤ አካል ከሙታን መነሣት ማለት ነው:- ፊልጵ. 3÷21፤ 1ቆሮ. 15÷49::

3. "የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆን" ማለት ግብረገባዊ ባሕርይን የሚያመለክት ነው ("ከክፉ ምኞት የተነሣ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል"):- 2ጴጥ. 1÷4 እንዲሁም የሚከተሉትን ክፉሎች ይመለከቷል ዕብ. 12÷10 "ተካፋዮች" የሚለውን ቃል ትርጉም ለማወቅ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ክፍሎች ይመለከቷል 1ቆሮ. 10÷18: 20፤ 2ቆሮ. 1÷17፤ 1ጴጥ. 5÷1::

### ሰ. ታላላቅ ወይም እጅግ ከፍ ያሉ ሰዎች አማልክት ናቸውን?

1. ቃለ እግዚአብሔር ሰዎች አማልክት ናቸው አይልም::
2. ታላቅ ወይም እጅግ ከፍ ያሉ ሰዎች አማልክት አይደሉም:- ሕዝ. 28÷2: 9፤ ኢሳ. 31÷3፤ 2ተሰሎ. 2÷4::
3. ሰዎችና እግዚአብሔር የተለያለዩ ናቸው:- ዘኍ. 23÷19፤ ኢሳ. 31÷3፤ ሕዝ. 28÷2፤ ሆሴዕ 11÷9፤ ማቴ. 19÷26፤ ዮሐ. 10÷33፤ ሐሥ. 12÷22፤ 1ቆሮ. 14÷2::
4. ሙሴ "እንደ እግዚአብሔር" ወይም "በእግዚአብሔር ፋንታ" ነበር እንጂ እግዚአብሔር አልነበረም:- ዘፀ. 4÷16፤ 7÷1::
5. አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች፣ ሕዝቅኤል 32÷21 ተዋጊዎችን ወይም ወታደሮችን፣ "ኀያላን አማልክት" ("mighty gods") ብለዋቸዋል:: ነገር ግን ዐውዱን ስንመለከት እንዲህ ዐይነቱ ስያሜ የተሰጣቸው እግዚአብሔርን በማያውቁ አረማውያን/አሕዛብ መንግሥታት እንጂ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ወይም በእስራኤላውያን አልነበረም፤ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:- ሕዝ. 28÷2:9::
6. በኦሪት ዘፀአት ወንጀል የሠራ ሰው የሚቆመው በእግዚአብሔር ፊት እንጂ በዳኞች ፊት አይደለም:: አንዳንድ ትርጉሞች በተሳሳተ መንገድ ዳኞቹን እግዚአብሔር (በዕብራይስጡ ኤሎሂም) በማለት በተሳሳተ መንገድ ተርጉመዋቸዋል:- ዘፀ. 22÷8-9:28 ከ ዘዳ. 19÷17 ጋር ያነጻጽሯል::
7. በመዝሙር 82 ላይ አማልክት (በዕብራይስጡ ኤሎሂም) የሚለው ቃል ምናልባት ቅን ያልሆነ ፍርድ የሚበይኑትን የእስራኤል ዳኞች የሚያመለክት እንጂ፣ ሰዎች አማልክት ናቸው ማለቱ አይደለም፤ ኢየሱስ በዮሐንስ 10÷34-36 ይህን ክፍል ጠቅሶ መናገሩ ይህንኑ እውነት የሚያስረግጥ ነው::

ሀ) እነዚህን ዳኞች/ፈራጆች ኤሎሂም ያላቸው አሳፍ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም መዝ. 82÷1:6::

ለ) አሳፍ በቊጥር 6 ላይ "እናንተ አማልክት ብትሆኑም...እንደ ማንኛውም ሰው ትሞታላችሁ" ሳይሆን፣ "እኔም እናንተ አማልክት ናችሁ፤ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ **አልሁ**:: ነገር ግን እንደ ማንኛውም ሰው ትሞታላችሁ፤ እንደ ማንኛውም ገዢ ትወድቃላችሁ" ነው ያለው::

ሐ) ስለዚህ ዘማሪው አሳፍ እነዚህን ዐመፀኛ ፈራጆች ያላቸው "አማልክት ናችሁ (gods)" ሳይሆን፣ "የልዑል እግዚአብሔር ልጆች ናችሁ" (ቊ. 6) ነው ያላቸው::

መ) ስለዚህ መዝሙር 82÷1 ፈራጆቹን **ኤሎሂም** ያላቸው በምፀት[36] ምልክ ነው፡፡ የተሰጣቸውን ኀላፊነት በትክክል የተወጡ ሰዎች አይደሉም (ከላይ በቁጥር 5 ላይ የተጻፈውን ይመለከቷል)፡፡ ኀላፊነታቸውን በትክክል ስላልተወጡም አሳፍ በምፀት መልክ **ኤሎሂም** ወይም አማልክት (gods) ናችሁ፤ ነገር ግን ትሞታላችሁ፤ በእውነተኛውም ኤሎሂም ፍርድ ሥር ትወድቃላችሁ ይላቸዋል (ቁጥር 1-2:7-8)፡፡

ሠ) ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በዮሐንስ 10÷34-36 ላይ መዝሙር 82÷1 ጠቅሶ መናገሩ ይህን ትንተና የሚጻረር አይደለም፡፡

ረ) "መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና" ማለት "መጽሐፉ ያለአንዳች ተፈጻሚነት እንዲሁ በከንቱ አይቀርም" ማለት ነው (ዋቢ ይሆኑ ዘንድ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ዮሐንስ 7÷23፤ ማቴዎስ 5÷17)፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ እያለ ያለው ነገር፣ ለብሉይ ኪዳኑ ፈራጆች በምፀት መልክ የተሰጠው ነገር ለእኔ በቀጥታ ይውላል ማለቱ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ መፈጸም ያቃታቸውን ነገር እርሱ ፈጽሞታል እንዲሁም ሆኖታልና (አስረጅ ይሆን ዘንድ በአዳምና በኢየሱስ መካከል የተካሄደውን ንጽጽር በሮሜ 5÷12-21፤ እንዲሁም 1ቆሮንቶስ 15÷21-22:45 ይመለከቷል፤ ይህም ንጽጽር በብሉያትና በሐዲሳት መካከል ሰብአውያንንና ክርስቶስን ያወዳደረ ንጽጽር ነው)፡፡

ሰ) በርካታ የእንግሊዝኛ ቅጆች "የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው" ብለው ሳይሆን፣ "የእግዚአብሔር ቃል የመጣባቸውን አማልክት ካላቸው" ብለው ነው የተረጐሙት "those against whom the word of God came"፡፡ ይህ የሚያሳየን ቃሉ "ለአማልክት" ተብዬዎቹ የፍርድ ቃል እንደ ሆነ ነው፡፡ ይህም አማልክቱ በትክክል አማልክት ናቸው ማለት ሳይሆን፣ ሐሰተኞች አማልክት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ሸ) በአጠቃላይ እነዚህ ክፉ ሰዎች፣ በተፈጥሮአቸው፣ "እግዚአብሔርን የሚመስሉ" ወይም "መለኮት የሆኑ" ሰዎች አይደሉም፡፡ ስለዚህ ኤሎሂም (አማልክት) የሚለው ቃል በቀጥታ ሳይሆን፣ በተምሳሌታዊ አገላለጽ (as figurative) መተርጐም አለበት፡፡

ቀ) ሰዎች አማልክት (gods) ቢባሉ እንኳ (ቃለ እግዚአብሔር አይላቸውም)፣ ሰዎች አማልክት መባላቸው ኢየሱስ አምላክ ከመባሉ ጋር የሚነጻጸር አይደለም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ከፍጥረተ ዓለም በፊት አምላክ ነበርና (ዮሐንስ 1÷1)፡፡

## ሸ. መላእክት አማልክት ናቸውን?

1. ቃለ እግዚአብሔር አንድም ቦታ ላይ መላእክትን አማልክት ናቸው አይልም፡፡
2. አጋንንት አማልክት አይደሉም፡፡ በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ 1ቆሮ. 10÷20፤ ገላትያ 4÷8 አማልክት "ኀያላን መናፍስት" መባላቸው መላእክትን አማልክት ናቸው እንድንል አያሰኘንም፡፡ "ኀያላን መናፍስት" ማለት አማልክት ማለት አይደለምና፡፡
3. ስለዚህ ሰይጣን ሐሰተኛ አምላክ ነው 2ቆሮ. 4÷4፡፡

[36] አንድን ቃል ቀጥተኛ ከሆነው ትርጒሙ ውጪ ተቃራኒ በሆነ መንገድ በመጠቀም ሐሳብን መግለጥ ምፀት (irony) ይባላል፡፡ የሽሙጥ፣ የአግቦ፣ የአሽሙር ወይም የሽርደዳ ንግግር ማለት ነው፡፡

4. መዝሙር 8÷5 መላእክት አማልክት እንደ ሆኑ አያስተምርም::

ሀ) ዕብራውያን 2÷7 ከመዝሙር 8÷5 በቀጥታ የተጠቀሰ ሳይሆን ሐሳቡ ነው የተወሰደው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል መዝሙር 68÷18 ከኤፌሶን 4÷8 ጋር ያነጻጽሩ):: በመዝሙር 8÷5 መሠረት ኤሎሂም ማለት አምላክ ማለት እንጂ፣ መላእክት ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም መዝሙር 8÷3-8 የዘፍጥረት 1÷1:8:16:26-28 ተነጻጻሪ ነውና:: ዘማሪው በክፍሉ ዐውድ የሰው ልጅ በፍጥረተ ዓለም ውስጥ እጅግ ከፍተኛውን ስፍራ የያዘ መሆኑን የሚያስተምር ሲሆን፣ በአንጻሩ የዕብራውያን መልእክት ግን፣ ኢየሱስ ሰው በመሆን (ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በዚህች ምድር ላይ መገለጡ) ዝቅተኛውን ስፍራ መውሰዱን ያሳያል:: ስለዚህ የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ መዝሙርን ሲያጣቅስ፣ መላእክት አማልክት ናቸው በሚል መንፈስ አይደለም::

ለ) ምንም እንኳ ዕብራውያን 2÷7 መላእክትን አማልክት ቢልም "gods" ከዕብራውያን 1-2 ዐውድ ላይ ያሉት መላእክት፣ ትክክል ባልሆነ ሁኔታ ራሳቸውን ከክርስቶስ በላይ ያደረጉ ናቸው:: ዕብራውያን 1÷6 ከመዝሙር 97÷7 የተጠቀሰ ሲሆን፣ ይህ የመዝሙር ክፍል ስለ ሐሰተኛ አማልክት የሚናገር ነው:: ስለዚህ ዕብራውያን 1÷6 እና ቈላስይስ 2÷16 አማልክትን ማምለክ ስሕተት እንደ ሆነ የሚገልጹ ክፍሎች ናቸው::

5. ሌሎችም የመዝሙር ክፍሎች መላእክትን እንደ አማልክት ወይም እንደ "አማልክት ልጆች" የሚገልጹ ከሆነ፣ እየገለጿቸው ያለው እንደ ሐሰተኛ አማልክት ነው:: ለምሳሌ:- መዝሙር 29÷1፤ 86÷8-10፤ 89÷6፤ 95÷3፤ 96÷4-5፤ 97÷7-9:: የሰብዐ ሊቃናት ትርጒም[37] እነዚህ ሐሰተኛ አማልክት "መላእክት" እንደ ሆኑ ይገልጻል:- መዝሙር 135÷5፤ 136÷2፤ 138÷1፤ እንዲሁም ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ ዘፀአት 15÷11፤ 18÷11፤ ዘዳግም 10÷17፤ 1ዜና 16÷25፤ 2ዜና 2÷5::

6. መላእክት አማልክት ቢባሉም እንኳ፣ (እስካሁን ያየናቸው ማስረጃዎች እንዳልሆኑ የሚያመለክቱ ናቸው) ይህ ጉዳይ ከኢየሱስ አምላክነት ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ መልአክ አይደለም፤ ነገር ግን መላእክት ፈጣሪያቸው፣ ጌታቸውና አምላካቸው አድርገው የሚሰግዱለት የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዕብራውያን 1÷1-13)::

**ማጠቃለያ:-** አንድ እውነተኛ አምላክ ወይም እግዚአብሔር ብቻ ካለ፣ የተቀሩት አማልክት ግን ሐሰተኞች ናቸው ማለት ነው:: ሰዎችም ሆኑ መላእክት አማልክት አይደሉም፤ አማልክት ሊሆኑም አይችሉም:: እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም:: ቃለ እግዚአብሔር በተደጋጋሚና በግልጥ የሚነግረን ይህን እውነት ከሆነ፣ አንድ አምላክ ብቻ አለ ብለን እንድንደመድም ያደርገናል::

---

[37] በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ላይ ከምድረ ፍልስጥኤም/ከፓለስቲና ውጪ ለሚኖሩ የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ አይሁድ እንዲያገለግል ታስቦ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተተረጐመው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅጅ የሰብዐ ሊቃናት ትርጒም (Septuagint) በመባል ይታወቃል (የሰብዐ ሊቃናተ ትርጒም በዕብራውያን ቀኖና ውስጥ ያልታቀፉ አንዳንድ መጻሕፍትንም መያዙን ልብ ይሏል):: ሰብቱዋጄንት የሚለው የእንግሊዝኛ ስያሜ የመጣው ሰብቱዋጄንታ (septuaginta) ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን፣ ትርጒሙም "ሰባ" ነው:: ይህ ስያሜ መጻሕፍትን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የመለሱት ተርጓምያን በአይሁድ ሊቀ ካህናት የተሾሙ ሰባ ወይም ሰባ ሁለት ሊቃውንት ናቸው የሚል እምነት ስላለ ነው:: የሰብዐ ሊቃናት ትርጒም የሚለው ነባር የአማርኛ ስያሜ የተወሰደው ከዚሁ የላቲን ስያሜ ነው:: የሰብዐ ሊቃናት ትርጒም በአኅጽሮት (LXX) ተብሎ ይጻፋል::

## II. ይህ አንዱ አምላክ በብሉይ ኪዳን ያህዌ በሚል ስም ይታወቅ ነበር::

ሀ. በርካታ የብሉይ ኪዳን ንባባት ያህዌ/ጆሆቫ ኤሎሂም ወይም ኤል ተብሎ እንደሚጠራ ያስረዳሉ፣ ዘዳግም 4÷35:39፤ መዝሙር 100÷3 ወዘተ::

ለ. በርካታ የብሉይ ኪዳን ንባባት ያህዌ/ጆሆቫ በተገናኝ/ጣምራ ስሞች "ያህዌ እግዚአብሔር" (ያህዌ ኤሎሂም) ተብሎ እንደሚጠራ ያስተምራሉ፣ ዘፍጥረት 2÷3፤ 9÷26፤ 24÷3፤ ዘፀአት 3÷15-18፤ 4÷4፤ 2ሳሙኤል 7÷22:25 ወዘተ::

ሐ. አንድ እግዚአብሔር/ያህዌ ብቻ አለ፣ ዘዳግም 6÷4፤ ማርቆስ 12÷29::

መ. ማጠቃለያ:- ያህዌ እውነተኛ አምላክ፣ ብቸኛ ኤል ወይም ኤሎሂም ነው::

## III. እግዚአብሔር ፍጹም ልዩና የሰዎች አእምሮ ከሚረዳው በላይ ምጡቅ ነው::

ሀ. አንድ አምላክ ብቻ ካለ አንድነቱ ልዩ ያደርገዋል፣ I. ሀ. ይመለከቷል::

ለ. እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም I. ለ. ይመለከቷል::

ሐ. የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ሊረዳ አይችልም 1ቆሮንቶስ 8÷2-3

መ. እግዚአብሔርን ልንረዳው የምንችለው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በገለጠልን መጠን ብቻ ነው፣ (ማቴዎስ 11÷25-27፤ ዮሐንስ 1÷18)::

ሠ. ተምሳሌታዊ አገላለጾች እግዚአብሔርን ለመግለጥ የሚያገለግሉ ናቸው፣ ሕዝቄል 1÷26-28፤ ራእይ 1÷13-16::

ረ. እግዚአብሔር ከዓለማት ሁሉ በላይ ምጡቅ (transcendent) እንዲሁም ከዓለማት ፍጹም የተለየ ነው፤ ይኸውም አናጺ ከሚሠራው ወንበር እንደሚለይ::

1. ከዓለማት ይለያል:- ኢሳይያስ 40÷22፤ ሐዋርያት ሥራ 17÷24::
2. ከዓለማት ጋር ተነጻጽሮአል:- መዝሙር 102÷25-27፤ 1ዮሐንስ 2÷15-17::
3. የዓለማት ፈጣሪ ነው:- ዘፍጥረት 1÷1፤ መዝሙር 33÷6፤ 102÷25፤ ኢሳይያስ 42÷5፤ 44÷24፤ ዮሐንስ 1÷3፤ ሮሜ 11÷36፤ ዕብራውያን 1÷2፤ 11÷3::

## IV. እግዚአብሔር አንድ አካል ነውን?

ሀ. እግዚአብሔር በመለኮቱ አንድ ነው (ከላይ በተራ ቁጥር I ላይ የተጠቀሰውን ይመለከቷል):: አንድ ያህዌ፣ አንድ ጌታ፣ (ከላይ በተራ ቁጥር II ላይ የተጠቀሰውን ይመለከቷል) አንድ መንፈስ ብቻ ነው ያለው፣ (ዮሐንስ 4÷24)::

**ለ. ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር "አንድ አካል" ብቻ ነው አይልም**

1. የኪንግ ጀምስ ትርጒም በዕብራውያን 1÷3 ላይ ስለእግዚአብሔር "አካል" ("person") ይናገራል፤ አካል ተብሎ የተተረጐመው ***ሐይፖስታሲስ*** የሚለው የግሪክ ቃል ነው፤ በዚያው በኪንግ ጀምስ ትርጒም ቃሉ በዕብራውያን 11÷1 እንዲሁም 1÷3 ላይ ቃሉ "ልይቀኅስ" ("substance") ተብሎ ነው የተተረጐመው፤ ይህም አብን የሚያመለክት ነው።

2. በገላትያ 3÷20 ላይ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ቃል ኪዳን አንደኛውን ወገን ወክሏል፤ ይህ ማለት ግን አንድ አካል ነው ማለት አይደለም።

3. በኪንግ ጀምስ ትርጒም ኢዮብ 13÷8 ላይ ስለእግዚአብሔር "አካል" ("person") ይናገራል፣ ነገር ግን የዕብራይስጡ ቅጅ "የእርሱ ፊት/ፊቱ" ይላል።

**ሐ. ለእግዚአብሔር የነጠላም ሆነ የበዙ ቊጥር ተውላጠ ስም ገብቶአል**

1. መጽሐፍ ቅዱስ ከ7 ሺህ ጊዜ በላይ እግዚአብሔርን በነጠላ ቊጥር ተውላጠ ስም (እኔ፣ እርሱ ወዘተ) እያለ ጠቅሷል። ይህም ትክክል ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የራሱ ማንነት ያለው አምላክ ነው፤ ነገር ግን በነጠላ ቊጥር ተውላጠ ስም መጠቀሱ እግዚአብሔር ሦስት አካላት እንዳለው ከሚያስተምሩት የቃለ እግዚአብሔር ምንባቦች ጋር የሚጣረስ አይደለም፤ ምክንያቱም እነዚህ አካላት እርስ በርሳቸው የሚለያዩ/ልይዩ (separate) አይደሉምና።

2. ቢያንስ በሦስት ቦታዎች ላይ፣ እግዚአብሔር ራሱ የብዙ ቊጥር ተውላጠ ስሞችን ተጠቅሟል (ዘፍጥረት 1÷26፤ 3÷22፤ 11÷7)።

ሀ) በኢሳይያስ 6÷8 ላይ የብዙ ቊጥር ተውላጠ ስም እግዚአብሔርንና መላእክትን ሊያሳይ ይችላል፤ ነገር ግን የዘፍጥረት መጽሐፍ ከዚህ የተለየ ነው። በዘፍጥረት 1÷26 ላይ "በመልካችን" የሚለው ቃል፣ በ1÷27 ላይ "በእግዚአብሔር መልክ" ተብሎ ተብራርቶአል፤ እንዲሁም በ 3÷22 ላይ፣ "ከእኛ እንደ አንዱ" የሚለው ሐረግ በ3÷5 ላይ "እንደ እግዚአብሔር" እንደ ሆነ ተገልጾአል።

ለ) "ሥነ ጽሑፋዊ ብዙነት" ("literary plural")[38] የሚያመለክት ነው የሚለው ትንተና የሚያስኬድ አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እየተናገረ እንጂ እየጻፈ አይደለም። በጽሑፍም ቢሆን፣ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ባሉ ጽሑፎች ውስጥ ይህ ጒዳይ በውል አይስተዋልም።

ሐ) "ሆንታ ብዙነት" ("plural of deliberation")[39] የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ "ደኅና ነን") የሚለውም ትንተና ብዙ የሚያስኬድ አይደለም፤ ይህ ጒዳይ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልጥ ተጠቅሶ አንመለከትም፤ ይህም ጒዳይ ዘፍጥረት 3÷22 ("ከእኛ እንደ አንዱ") የሚለውን የሚያብራራ አይደለም።

---

[38] አንድ ሰው ጽሑፍ ሲጽፍ ራሱን ብዙ ቊጥር አድርጎ ሲያቀርብ፣ "ሥነ ጽሑፋዊ ብዙነት" ("literary plural") ይባላል። በተለይ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ፣ ጸሓፍያን ራሳቸውን በብዙ ቊጥር መግለጻቸው የተለመደ ነው።

[39] በንግግር ውስጥ አንድ ሰው ሆነ ብሎ ራሱን በብዙ ቊጥር ሲያቀርብ "ሆንታ ብዙነት" ("plural of deliberation") ይባላል። ለምሳሌ "እንደምን ነህ" ሲባል፣ "ደኅና ነን" ብሎ መልስ እንደሚሰጠው ማለት ነው።

*መ*) *"የሙሉነት ብዙነት"* ("plural of amplitude" or of "fullness")[40] **የሚያመለክት ነው** (ይህ ጉዳይ ምናልባት እግዚአብሔር የሚለውን የነጠላ ቁጥር ስም ኤሎሂም የሚለውን የብዙ ቁጥር ስም ሊያብራራ ይችል ይሆናል) የሚለውም ትንተና ትክክል አይመስልም፤ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ በብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም ላይ እውን ሊሆን ያለመቻሉ ብቻ ሳይሆን፣ ዘፍጥረት 3÷22 የማብራራት ዐቅም አይኖረውም::

*ሠ*) *"የግርማዊነት ብዙነት"* "plural of majesty"[41] የሚያመለክት ነው የሚለው ጉዳይ ከ1ነገሥት 12÷9፤ 2ዜና 10÷9 በተለይም ከዕዝራ 4÷18 አንጻር ሲታይ ሊያስኼድ ይችላል ነገር ግን በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፤ እንዲሁም ዘፍጥረት 3÷22 ማብራራት አይችልም፤ በተለይ ደግሞ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ የቀረበበት ግልጽ ቦታ የለም[42]::

[40] *"የሙሉነት ብዙነት"* ("plural of amplitude" or of "fullness") የእግዚአብሔርን ፍጹም ምሉዕነት ለማመልከት ሲባል በንግግርም ሆነ በጽሑፍ እግዚአብሔርን ብዙ ቁጥር አድርጎ ማቅረብን ይመለከታል::

[41] *"የግርማዊነት ብዙነት"* "plural of majesty" የሚባለው ደግሞ፣ ነገሥታት ራሳቸውን በብዙ ቁጥር የመግለጻቸውን ጉዳይ የሚያመለክት ነው:: ለምሳሌ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ራሳቸውን፣ "እኛ" ሲሉ ይገልጹ እንደ ነበር ልብ ይ[illegible]ብሉያትም ሆነ ሐዲሳት በተጻፉበት ዘመን ነገሥታት ራሳቸውን በዚህ መልኩ ሲ[illegible]ቡ አልታየም:: አንዳንድ ሰዎች ወይም ድርጅቶች በሙግታቸው ውስጥ ከላይ ያየናቸውን ክፍሎች በተመለከተ፣ "የግርዊነት ብዜት" ነው ሲሉ ይታያል:: ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱስን በተጻፈበት መቼት/ዘመን ውስጥ ያለማንበብን ችግር የሚያሳይ ነው:: በተለይ በዕብራይስጥ ቋንቋ ይህ ጉዳይ ፍጹም ባዕድ ነው::

[42] ግርማዊ ብዙነት በተመለከተ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ስመ ጥር በሚባሉት የእንግሊዝኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች ላይ ይመለከቷል::

**መ. እግዚአብሔር ከሰው አስተሳሰብ የተለየ (የመጠቀ) መሆኑ (ከላይ በተራ ቁጥር III ላይ የተጠቀሰውን ይመለከቷል) አንዱ መለኮት ሦስት አካላት አሉት እንድንል ሊያደርገን ይችላል::**

## V. የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር ነው

**ሀ. ግልጽ በሆኑ ዐረፍተ ነገሮች:- ዮሐንስ** 17÷3፤ **1ቆሮንቶስ** 8÷6 **ወዘተ::**

**ለ. "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት" የሚለው አነጋገር 2ቆሮንቶስ** 1÷3፤ **ኤፌ.** 1÷3፤ **1ጴጥሮስ** 1÷3::

## VI. ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው

**ሀ. ግልጽ በሆኑ ዐረፍተ ነገሮች**

1. **ኢሳይያስ 9÷6::** በዚህ ዐውድ ኢየሱስ ክርስቶስ ኀያል አምላክ እንደ ተባለው ሁሉ፣ እግዚአብሔር አብም ኀያል አምላክ ተብሎአል 10÷21:: ይህን ክፍል "ኀያል ጀግና" ("mighty hero") ብሎ መተርጐም ስሕተት ነው:: ይህን ክፍል ከሕዝቅል 32÷21 አንጻር መመልከት ስሕተት ነው:: ምክንያቱም (ሀ) ይህ ክፍል ከ10÷21 ጋር በተመሳሳይ ዐውድ ውስጥ የሚገኝ አይደለም:: (ለ) ሕዝቅኤል 32÷21 የሚናገረው ስለ ሐሰተኛ አማልክት ነው፤ ከላይ ተራ ቁጥር I.ሰ.5. ይመለከቷል::

2. **ዮሐንስ 1፥1።** *አንዳንዶች ይህን ክፍል፣* "a god" ብለው ተርጒመውታል፤ ይህ የተሳሳተ አተረጓጐም ነው። አንድ እግዚአብሔር ካለ፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ነገር ግን "a god" ብሎ መተርጐም ስሕተት ነው። ሌሎች ክፍሎች ***ቴዎስ*** የሚለውን የግሪክ ቃል፣ በዚህ ቦታ እንዳለው ዐይነት የሰዋስው አወቃቀር እግዚአብሔር ተብሎ "God" ተተርጒሞአል፣ ለምሳሌ ማርቆስ 12፥27፤ ሉቃስ 20፥38፤ ዮሐንስ 8፥54፤ ፊልጵስዩስ 2፥13፤ ዕብራውያን 11፥16። በግሪክ ሰዋስው ***ቴዎስ*** **(እግዚአብሔር)** ከሚለው የግሪክ ቃል ፊት ውሱን[43] መስተአምር መኖርም ሆነ ያለመኖር አንዳችም የትርጒም ልዩነት አያመጣም፦ ማርቆስ 12፥27፤ ሉቃስ 20፥37-38፤ ዮሐንስ 3፥2፤ 13፥3፤ ሮሜ 1፥21፤ 1ተሰሎንቄ 1፥9፤ ዕብራውያን 9፥14፤ 1ጴጥሮስ 4፥10-11።

3. **ዮሐንስ 1፥18።** እጅግ ጥንታዊና ተአማኒነት ያላቸው የግሪክ ቅጆች "ልዩ አምላክ" ይሉታል። አብዛኛውን ጊዜ ***ሞኖጌኔስ*** የሚለው የግሪክ ቃል የተተረጐመው "አንድያ ልጅ" ተብሎ ነው። መተርጐም የነበረበት ግን "አንድ ዐይነት ባሕርይ ያለው" "one of a kind" ወይም "ልዩ" "unique" ተብሎ ነበር። አንድያ ልጅ ተብሎ ቢተረጐምም፣ የተወለደ አምላክ የሚል ትርጒም አይኖረውም።

4. **ዮሐንስ 20፥28።** ይህ ክፍል የነጠላ ቊጥርን ቢያሳይም፣ የብዙ ቊጥር በማሳየት ("አምላካችን") ከዚህ ክፍል ጋር ተመሳሳይ የሆነ የሰዋስው አወቃቀር ያለውን የራእይ 4፥11 ክፍል ከዮሐንስ 20፥28 ጋር ያነጻጽሩ። እንዲሁም መዝሙር 35፥23 ይመለከቷል። ኢየሱስ ለቶማስ የመለሰውን መልስ ስንመለከት፣ ቶማስ እንደዚያ በማለቱ ስሕተት እንዳልነበረ እንረዳለን። በዮሐንስ 20፥17 ላይ አብ የኢየሱስ አምላክ ተብሎአል (ሰው በመሆኑ ምክንያት)፣ ነገር ግን ቶማስ በዚያው ምዕራፍ ላይ አምላኬ ማለቱ ቊጥር 17 ላይ በታየበት መልኩ እንዳይታይ የሚያደርገው ምክንያት ምንድን ነው? አብ፣ ወልድ ሰው በመሆኑ ምክንያት፣ የወልድ አምላኩ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ወልድም የቶማስ አምላኩ ነው፤ ለቶማስ አምላኩ ከሆነ ደግሞ ለእኛ አምላካችን የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም።

5. **የሐዋርያት ሥራ 20፥28።** "በደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ዐረፍተ ነገር እግዚአብሔር በደሙ የዋጃት ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው። የግሪክ አማራጭ ትርጒሞች "የጌታን ቤተ ክርስቲያን" ቢሉም ከመጀመሪያው ትርጒም ብዙም የራቀ አይደለም።

6. **ሮሜ 9፥5።** ይህ ብቸኛው የሰዋስው ትርጒም አይደለም፤ ሌሎች አማራጭ ትርጒሞችም ሊኖሩት ይችላል፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደው ቡራኬ፣ ይህንን ትርጒም እንድንከተል የሚያደርገን ነው፤ ይህም ክርስቶስ አምላክ እንደ ሆነ ያሳያል።

7. **ቲቶ 2፥13።** ሰዋስዋዊውም ሆነ ዐውዳዊ ትርጒሙ ኢየሱስ አምላክ እንደ ሆነ የሚያመለክት ክፍል ነው። ሻርፐስ በመባል የሚታወቀው የግሪክ የሰዋስው ሕግ (ማለትም ሁለት ስሞች "እና" (ግሪክ "ካይ") በሚለው አያያዥ ቃል ከተጣመሩና በመጀመሪያው ስም ፊት ውስን መስተአምር (the) ኖሮ ሁለተኛው ስም ላይ ውስን መስተአምር ከሌለ፣ ዐረፍተ ነገሩ የሚያወራው ስለአንድ ጒዳይ ብቻ ነው፤ ስለዚህም ሁለቱም ስሞች ወይም ቅጽሎች አንድን ነገር የሚያመለክቱ ናቸው) ኢየሱስ "ታላቅ አምላክ እንዲሁም መድኀኒት" እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው። ከዚህ ዐረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ የሰዋስው አወቃቀር ያላቸውን

[43] እየተናገርሁ ያለሁት የግሪኩን ሰዋስው እንደ ሆነ ልብ ይሏል። ምናልባት በአማርኛ ቋንቋ መስተአምርን ውሱንና ያልተወሰነ ብለን መክፈል አንችል ይሆናል፤ አብዛኛውን ጊዜ ውሱንናትን ስለሚያሳይ። በእንግሊዝኛና መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ (በኮይኔ ግሪክ) መስተአምር ውሱንና ያልተወሰነ ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

በርካታ ክፍሎች ቢኖሩም ለናሙናነት የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል፣ ሉቃስ 20÷37፤ ራእይ 1÷6:: በተጨማሪም ጳውሎስ ዘወትር "መገለጥ" የሚለውን ቃል የሚጠቀምበት ለክርስቶስ ነው፤ ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:- 2ተሰሎንቄ 2÷8፤ 1ጢሞቴዎስ 6÷14፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷10፤ 4÷1:8::

8. **ዕብራውያን 1÷8::** ግሪኩ ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "እግዚአብሔር ዙፋንህ ነው" የሚል ትርጒም አለው:: ቃሉን ቃል በቃል ስንተረጒመው ትርጒም አይሰጥም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በዙፋን ላይ የሚቀመጥ እንጂ እርሱ ራሱ ዙፋን አይደለም:: "እግዚአብሔር ዙፋንህ ነው" የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ እግዚአብሔር የአንድ ንጉሥ የንግሥናው መሠረት ነው የሚል ትርጒም የሚሰጠው ቢሆን እንኳ፣ ክፍሉ ማለትም ዕብራውያን ምዕራፍ 1 ኢየሱስ በመላእክት ላይ ስላለው አመራር የሚናገር ሳይሆን፣ ኢየሱስ ከመላእክት በላይ መሆኑን እንዲያውም አምላክ መሆኑን የሚገልጽ ነው:: ለመላእክት አምላካቸው ስለሆነም ይሰግዱለታል ቊጥር 6::

9. **1ጴጥሮስ 1÷1::** ክፍሉ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን፣ ከቲቶ 2÷13 ጋር ተመሳሳይ የሆነ የሰዋስው አወቃቀር አለው:: ከዚህ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሰዋስው አወቃቀሮችን ከሚከተሉት ክፍሎች ይመልከቱ፣ 2ጴጥሮስ 1÷11፤ 2÷20፤ 3÷2:18::

10. **1ዮሐንስ 5÷20::** "እርሱም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስን ከሆነ፣ "የዘላለም ሕይወት" የሚለውም ሐረግ ክርስቶስን የሚያመለክት ነው (ከ 1÷2 ጋር ያነጻጽሯል):: እርሱም እውነተኛ አምላክ ነው::

**ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ነው::**

1. ሮሜ 10÷9-13 የ"እና" ("for") መደጋገም፣ ክፍሉን እርስ በርሱ የሚያያይዘው ሲሆን፣ በ10÷13 ላይ "ጌታ" የተባለው በ10÷9:12 ላይም ጌታ የተባለው እርሱው ነው::

2. በፊልጵስዩስ 2÷9-11፤ ከዐውደ ምንባቡ እንደምንመለከተው፣ "ከስምም ሁሉ በላይ የሆነው ስም" ቊጥር 11 ላይ የተጠቀሰው "ጌታ" የሚለው ስም ነው፤ ይህም፣ "ከስምም ሁሉ በላይ የሆነ ስም" ያህዌ የሚለው ስም ነው[44]::

3. ዕብራውያን 1÷10፤ በዚህ ክፍል እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ክርስቶስን "ጌታ" እያለ ይጠራዋል:: ይህ ክፍል በቀጥታ የተጠቀሰው/የተወሰደው ከመዝሙር 102÷25 ላይ ነው:: ልመናውን የሚያቀርበው ሰው ልመናውን የሚያቀርበው "ለእግዚአብሔር" ነው:: በክፍሉ አብ ወልድን "ጌታ" ብሎ የሚጠራው ከሆነና ክፍሉን ዐውዱን መሠረት ባደረገ መንገድ የምንተረጒመው

---

[44] በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በአዲስ ኪዳን ንባባት በተጽውዖ ስምና (በመጠሪያ ስምና) በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም ልዩነት የለም:: ለአብነት ያህል ማቴዎስ 28÷19-20 ይመለከቷል:: ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ነው ወይስ "በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም" ነው የሚለውን ጒዳይ በተመለከተ፣ "በተጽውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል ልዩነት አለ" የሚለውን ጒዳይ እንደ መከራከሪያ ነጥብ ሲያነሡት ይስተዋላል:: በብሉያትም ሆነ በሐዲሳት ይህ ዐይነቱ ልዩነት አይታይም:: "በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አስተምህሮ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ "'***የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያኝ አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘኝ***" በሚል ርእስ የጻፈውንና በቅርቡ ለንባብ የሚበቃውን መጽሐፍ ይመለከቷል::

ከሆነ፣ ፍጡራን ክርስቶስን እግዚአብሔር ወይም ጌታ የሚሉት በውክልና ደረጃ ነው ማለት በፍጹም አይቻልም።

4. 1ጴጥሮስ 2÷3-4፤ ይህ ክፍል በቀጥታ የተወሰደው ከመዝሙር 34÷8 ላይ ነው፤ በክፍሉም "ጌታ" የተባለው ያህዌ ነው። ከ1ጴጥሮስ 2÷4-8 ላይ "ጌታ" የተባለው በቁጥር 3 ላይ ኢየሱስ ነው።

5. 1ጴጥሮስ 3÷14-15፤ ይህ ክፍል ደግሞ ኢሳይያስ 8÷12-13 የሚያመለክት ነው። በዚህም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ፣ ቅዱስ የተባለው ያህዌ ነው፤ ይህም ኢየሱስ ያህዌ እንደ ተባለ የሚያሳይ ነው።

6. ኢየሱስ "አንድ ጌታ" ብቻ እንዳለ በተናገረባቸው ንባባት፣ አንድ ጌታ ብቻ እንዳለ፣ ይህም ጌታ ያህዌ እንደ ሆነ ገልጾአል፤ የሚከተሉትን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ንባባት እርስ በርሳቸው ያነጻጽሩ ዘዳግም 6÷4፤ ማርቆስ 12÷29 እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል 1ቆሮንቶስ 8÷6፤ ኤፌሶን 4÷5፤ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያወዳድሩ ሮሜ 10÷12፤ 1ቆሮንቶስ 12÷5።

## ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ ማዕረግ አለው

1. አምላክ ብቻ ያለው/ገንዘቡ ያደረጋቸው የማዕረግ ስሞች

ሀ) መጀመሪያውና መጨረሻው፣ ራእይ 1÷17፤ 22÷13፤ ከሚከተለው ክፍል ጋር ያወዳድሩ ኢሳይያስ 44÷6።

ለ) የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ፣ 1ጢሞቴዎስ 6÷15፤ ራእይ 17÷14፤ 19÷16።

2. የመጨረሻ ግባቸው እግዚአብሔርን የሚያሳዩ የማዕረግ ስሞች

ሀ) አዳኝ፣ ሉቃስ 2÷11፤ ዮሐንስ 4÷42፤ 1ዮሐንስ 4÷14፤ ቲቶ 2÷13:10፤ ወዘተ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያወዳድሩ ኢሳይያስ 43÷11፤ 45÷21-22፤ 1ጢሞቴዎስ 4÷10 ኢየሱስ ክርስቶስ የድኅነት ምንጭ ነው ዕብራውያን 5÷9፤ ዘፀአት 15÷2፤ መዝሙር 118÷14:21።

ለ) እረኛ፣ ዮሐንስ 10÷11፤ ዕብራውያን 13÷20፤ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ መዝሙር 23÷1፤ ኢሳይያስ 40÷11።

ሐ) ዐለት፣ 1ቆሮንቶስ 10÷4፤ ከኢሳይያስ 44÷8 ጋር ያነጻጽሩ።

## መ. ኢየሱስ ክርስቶስ ለአምላክ ብቻ የሚሰጠውን ክብር ተቀብሎአል

1. ክብር፤ ዮሐንስ 5÷23።

2. ፍቅር፤ ማቴዎስ 10÷37።

3. ጸሎት፤ ዮሐንስ 14÷14 (ክፍሉ አከራካሪ ቢሆንም፣ ጸሎትን የሚመልሰው ግን ኢየሱስ ለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም)። በተጨማሪ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል፤ ሐዋርያት ሥራ 1÷24-25፤ 7÷59-60 (ከ ሉቃስ 23÷34:46 ጋር ያወዳድሩ) ሮሜ 10÷12-13፤ 1ቆሮንቶስ 1÷2፤ 2ቆሮንቶስ 12÷8-10 ("ጌታ" የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ከቁጥር 9 ጋር ያወዳድሩ) 2ተሰሎንቄ 2÷16-17 ወዘተ።

4. ስግደት (በግሪኩ ፕሮስኩኖ) ማቴዎስ 28÷17፤ ዕብራውያን 1÷6 (ከመዝሙር 97÷7 ጋር ያወዳድሩ) እንዲሁም ከማቴዎስ 4÷10 ጋር ያወዳድሩ።

5. የተቀደሰ ሃይማኖታዊ አገልግሎት (በግሪኩ ላቲሪዮ) ራእይ 22÷13።

6. ለአምላክ ብቻ የሚቀርብ ምስጋና 2ጢሞቴዎስ 4÷18፤ 2ጴጥሮስ 3÷18፤ ራእይ 1÷5-6፤ 5÷13።

7. እምነት ዮሐንስ 3÷16፤ 14÷1 ወዘተ።

**ሠ. ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ብቻ የሚሠራውን ሥራ ይሠራል።**

1. መፍጠር፣ ዮሐንስ 1÷3፤ 1ቆሮንቶስ 8÷6፤ ቈላስይስ 1÷16-17፤ ዕብራውያን 1÷2፤ ራእይ 3÷14 (“አርኬ” የሚለውን የግሪክ ቃል፣ የተለያዩ ትርጒሞች በተለያየ መንገድ ፈትተውታል፤ የ1954 ትርጒም “መጀመሪያ”፣ 1980 ትርጒም “መገኛ”፣ አዲሱ መደበኛ ትርጒም “ገዥ”። እነዚህ ሁሉ “አርኬ” ለሚለው ለግሪክ ቃል አማራጭ ትርጒሞች ቢሆኑም፣ "ገዥ" የሚለው ቃል ከዐውዱ ጋር የሚቀራረብ ትርጒም ያለው ይመስላል)፤ ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩት “ለእርሱ”ና “በእርሱ” ነው፣ ሮሜ 11÷36፤ ዕብራውያን 2÷10፤ ሐዋርያት ሥራ 17÷28 እንዲሁም ኢሳይያስ 44÷24።

2. ዓለማትን ደግፎ መያዝ፣ ቈላስይስ 1÷17፤ ዕብራውያን 1÷3:11-12።

3. የዘላለምን ሕይወት መስጠት።

    ሀ). በአጠቃላይ ከላይ ሐ.2.ሀ. ይመለከቷል።

    ለ). ኀጢአትን ይቅር ማለት፤ ማቴዎስ 9÷1-8፤ ማርቆስ 2÷1-12፤ ሉቃስ 5÷17-26።

4. አምላካዊ ባሕርያት ሁሉ አሉት፤ ዮሐንስ 5÷17-29 (ፍርድን ጨምሮ ማቴዎስ 25÷31-46፤ 2ቆሮንቶስ 5÷10)።

**ረ. ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ብቻ ገንዘቡ ያደረጋቸው ባሕርያት (ተጋብአዊና አልቦ ተጋብአዊ ባሕርያት[45]) ሁሉ አሉት።**

1. አምላካዊ ባሕርያት ሁሉ አሉት፣ ዮሐንስ 1÷1፤ ፊልጵስዩስ 2÷6፤ ቈላስይስ 1÷15፤ 2÷9፤ ዕብራውያን 1÷3።

2. በራሱ ሕልውና ያለው ነው (Self-existent)፣ ዮሐንስ 5÷26።

3. አይለወጥም:- ዕብራውያን 1÷10-12፣ (ልክ እንደ ያህዌ “YHWH” ማለት ነው) ዕብራውያን 13÷8።

4. ዘላለማዊ ነው:- ዮሐንስ 1÷1፤ 8÷58፤ 17÷5 ቈላስይስ 1÷17፤ ዕብራውያን 1÷2።

5. በሁሉ ቦታ ይገኛል:- ማቴዎስ 18÷20፤ 28÷20፤ ዮሐንስ 3÷13፤ ኤፌሶን 1÷23፤ 4÷10፤ ቈላስይስ 3÷11።

6. ሁሉን ያውቃል:- ዮሐንስ 16÷30፤ 21÷17፤ ከያነጻጽሩ 2÷23-24።

7. ልንረዳው ከምንችለው በላይ ነው፣ ማቴዎስ 11÷25-27።

**ሰ. ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር በሁሉ ነገር እኩል ነው**

---

[45] የእግዚአብሔር ባሕርያት ተጋብአዊ (communicable) እንዲሁም አልቦ ተጋብአዊ (incommunicable) ባሕርያት በሚል በሁለት ዐቢይ ክፍሎች ይከፈላሉ። ተጋብአዊ ባሕርያት የሚባሉት እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጆች በተወሰነ መጠን ያካፈላቸው ባሕርያት ሲሆኑ (ለምሳሌ ዕውቀት) አልቦ ተጋብአዊ ባሕርያት የሚባሉት ደግሞ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያላካፈላቸው (ለምሳሌ በሁሉ ቦታ መገኘት) ባሕርያት ናቸው። ቃሉ **ተጋብአ** ከሚለው የግእዝ ቃል ተወስዶ ይህን ሙያዊ ቃል ቢተካ በሚል የተቀመረ ነው። አንዳንድ ጸሐፍያን ከዚህ ይልቅ፣ **ተግባቦታዊ** እንዲህም **አልቦ ተግባቦታዊ** ባሕርያት የሚሉትን ቃላት ይጠቀማሉ፤ ሊያስኬድ ይችላል።

1. ዮሐንስ 5÷18፣ ምንም እንኳ ዮሐንስ አይሁድ የኢየሱስን አነጋገር በምን መልኩ እንደ ተረዱት ቢዘግብልንም፣ የተረዱት ግን ትክክለኛውን ነገር ነው፤ በቁጥር 17 ላይ ልክ እንደ አባቱ እርሱም ሰንበትን ማክበር እንደማይጠበቅበት ገልጾአል፤ እንዲሁም በ5÷19-29 ላይ አብ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እንደሚሠራ፣ ከዚህም የተነሣ ለአብ የሚሰጠው ክብር ሁሉ ለእርሱም እንደሚገባው ገልጾአል::

2. ፊልጵስዩስ 2÷6፤ ኢየሱስ በዚህች ዓለም ዕውቅናን ለማግኘት ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል የሚያደርገውን ነገር ይዞ መቅረት አልፈለገም፣ ነገር ግን መታወቅ የፈለገው ራሱን ዝቅ በማድረግ እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱ ከፍ እንዲያደርገው ራሱን በመስጠት ነው (ቁጥር 7-11)::

### ሸ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው::

1. በቃለ እግዚአብሔር፣ ልጅ (ወልድ) የሚለው ቃል በቀጥታም ሆነ በተምሳሌታዊ መንገድ አባት ከተባለው ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ ያለው ነው (ለምሳሌ "የእግዚአብሔር ልጅ"፣ "የነጐድጓድ ልጅ"፣ "የዐመፃ ልጅ" የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ማርቆስ 3÷7፤ ኤፌሶን 2÷1)::

2. የሰውን ልጅ በተመለከተ፣ ልጅ የአባቱ ተፈጥሮ/ባሕርይ ያለው ነው (የሰው ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የዳዊት ልጅ ወዘተ)::

3. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መባሉ፣ ልክ እንደ ሰብአውያኑ አነጋገር በእግዚአብሔር የተወለደ ነው ማለት አይደለም::

4. ኢየሱስ "የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ" የተባለው እጅግ በተለየ መንገድ ነው ዮሐንስ 1÷14፤ 3÷16:18፤ 1ዮሐንስ 4÷9)::

5. ቃለ እግዚአብሔር በግልጥ የሚያስተምረን ነገር ወልድ አምላካዊ ተፈጥሮ/ባሕርይ እንዳለው ነው (የወልድ ባሕርይ ልክ እንደ አብ ባሕርይ ነው ማለት ነው:: ከላይ ተራ ቁጥር ረ. ይመለከቷል)::

6. ኢየሱስ በተደጋጋሚ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ማለቱ፣ በአድማጮቹ በአይሁድ ዘንድ፣ ራስን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል በማድረግ እግዚአብሔርን እንደ መሳደብ ነበር ያስቈጠረበት፣ ኢየሱስም ንግግሬን በዚህ መንገድ መረዳታችሁ ስሕተት ነው የሚል ማስተባበያ አላቀረበም፤ ይህም ንግግራቸው ትክክል መሆኑን የሚያመለክት ነው ዮሐንስ 5÷17-23፤ 8÷58-59፤ 10÷30-39፤ 19÷7፤ ማቴዎስ 26÷63-65::

7. ስለዚህ ኢየሱስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው እንጂ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ፍጡር ወይም አገልጋይ አይደለም:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ለእኛ ሲልና ለአባቱ ክብር ሲል ነው ዮሐንስ 13÷13-15፤ 17÷4፤ ፊልጵስዩስ 2÷6-11፤ ዕብራውያን 1÷4-13፤ 3÷1-6፤ 5÷8::

### ቀ. የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የማይቀበሉ ሰዎች አዘውትረው የሚያቀርቧቸው ተቃውሞዎች:-

1. **ምሳሌ 8÷22፤** ክፍሉ ስለክርስቶስ የሚናገር ሳይሆን፣ ሰውኛ በሆነ ዘይቤ ስለጥበብ የሚናገር ቅኔ ነው (ሁሉም የምሳሌ 1-9 ክፍሎች፣ በተለይ ደግሞ 8÷12-21፤ 9÷1-6 ላይ ያሉት ክፍሎች):: ቅኔያዊ በሆነ ሁኔታ/መንገድ እግዚአብሔር ጥበብን ገንዘቡ ያደረገው፣ ፍጥረታትን ከመፍጠሩ በፊት ነው:: በአጠቃላይ ክፍሉ ስለ ጥበብ አስፈላጊነት እንጂ፤ ስለ ክርስቶስ የሚናገር አይደለም:: ክፍሉ ስለ ክርስቶስ የሚናገር ቢሆን ኖሮ፣ ክርስቶስን በሰውኛ ዘይቤ አያቀርበውም፤ እንዲሁም በአንስታይ ጾታ አይገልጸውም ነበር::

2. **ቈላስይስ 1÷15፤** ይህ ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ፍጥረት ነው አይልም:: ነገር ግን አባቱን ወክሎ በዚህ ስለሚገኝ፣ የአባቱ ቀዳማይ ወራሽ ነው (ቊጥር 12-44)፤ ስለዚህ "በኵር" ማለት ወራሽ ማለት ነው (ይህን ጉዳይ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩት፤ ዘፍጥረት 43÷33፤ 48÷14-20 ዘፀአት 4÷22፤ 1ዜና 5÷1-3፤ መዝሙር 89÷27፤ ኤርምያስ 31÷9) ልብ ይበሉ ቊጥሩ ልጁ ፈጣሪ እንደ ሆነ እንጂ፣ ፍጡር መሆኑን አይናገርም (ከላይ በተራ ቊጥር ሠ.1. ላይ ያለውን ይመለከቷል)::

3. **ራእይ 3÷14፤** "መጀመሪያ" የሚለው ቃል እንደ ማዕረግ ሆኖ ሲቀርብ ምንጭ ወይም ጀማሪ የሚል ትርጒም ይወክላል፤ ይህ ደግሞ ፈጣሪነቱን ያሳያል (ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ ራእይ 1÷8፤ 21÷6፤ 22÷13):: በሌላ ስፍራ የኢየሱስን ገዥነት/ፈጣሪነት/የፍጥረት ጀማሪነትን ለማሳየት በዚህ ስፍራ ያለውን ዐይነት የግሪክ ቃል ተጠቅሞአል፤ ቈላስይስ 1÷18 የብዙ ቊጥርን በሚያመለክት መልኩ ደግሞ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል፤ ቈላስይስ፤ 1÷16፤ 2÷10:15 እንዲሁም ሉቃስ 12÷11፤ ሮሜ 8÷38፤ ኤፌሶን 3÷10፤ 6÷12፤ ቲቶ 3÷1፤ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ ሉቃስ 20÷20፤ ይሁዳ 6፤ 1ቆሮንቶስ 15÷24፤ ኤፌሶን 1÷21::

4. **1ቆሮንቶስ 11÷3፤ 15÷28፤** ልጅ ለአባቱ እንደሚገዛ ኢየሱስም ለአባቱ ይገዛል፤ በአምላክነት ግን ከአባቱ ጋር እኩል/ትክክል ነው፤ መገዛት ማነስን አያሳይም፤ ከአብ ጋር ባለው ግንኙነት ራሱን ዝቅ ማድረጉ ማነሱን በፍጹም ሊያሳይ አይችልም[46]::

5. **ዮሐንስ 20÷17፤ ሮሜ 15÷6፤ 1ቆሮንቶስ 15÷24፤ 2ቆሮንቶስ 1÷3፤ ራእይ 1÷6፤ 3÷12፤** ኢየሱስ አባቱን "አምላኬ" ያለበት ምክንያት ኢየሱስ እስካሁን ድረስ አምላክም ሰውም ስለሆነ ነው:: ኢየሱስ አንድም ቦታ ራሱን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመጨመር አብን "አምላካችን" ሲል አንመለከትም፤ ነገር ግን "አምላኬ"ና "አምላካችሁ" ዮሐንስ 20÷17::

6. **ማርቆስ 13÷32፤** ኢየሱስ የዳግም ምጽአቱን ቀን አላውቅም የማለቱ ጉዳይ መብራራት ያለበት፣ ራሱን በትሕትና ዝቅ በማድረግ ሰው በመሆኑ ነው (ፊልጵስዩስ 2÷7):: ኢየሱስ በአምላክነቱ ሁሉን ነገር ያውቃል (ዮሐንስ 16÷30) ከትንሣኤው በኋላ ግን አለማወቁን ጉዳይ ራሱን በጨመረ መልኩ አልተናገረም (ሐዋርያት ሥራ 1÷6-7)::

---

[46] ሁለት ዐይነት ማነስ/መገዛት አለ፤ አንደኛው "ከሥራ ክፍፍል የተነሣ ማነስ" (functional subordination) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ "ከማንነት የተነሣ" (ontological subordination) ማነስ ነው:: በወንድና በሴት፣ በባሪያና በጨዋ፣ በአለቃና በበታች ሠራተኛ ወዘተ መካከል ያለው መገዛት የሥራ ክፍፍልን የሚያሳይ እንጂ፣ በተፈጥሮ አንዱ ከሌላው ይበልጣል ማለት አይደለም:: የሰው ልጅ ለአምላኩ መገዛቱ ግን ከማንነት የተነሣ ማነሱንም ጭምር የሚያሳይ ነው:: ሰው ፍጡር እግዚአብሔር ደግሞ ፈጣሪ ነውና:: ቃለ እግዚአብሔር፣ "ሚስቶች ሆይ ለባሎቻችሁ ተገዙ" (ኤፌሶን 5÷22) ሲል፣ የባሎች የሰውነት ተፈጥሮ ከሴቶች ይበልጣል ማለቱ እንዳልሆነ ሁሉ፣ ወልድም ለአብ ይገዛል ማለት፣ ወልድ ከአብ ያነሰ ነው ማለት አይደለም:: በአስረጅነት ያቀረብኋቸው፣ ክፍሎች ሁሉ "መገዛት" ለሚለው ቃል ተመሳሳይ የግሪክ ቃል የሚጠቀሙ ናቸው::

መጽሐፍ ቅዱስ በሥላሴ አካላት መካከል አንዱ ለአንዱ የመገዛት ነገር እንዳለ በግልጥ ያስተምረናል:: መንፈስ ቅዱስ፣ ለአብና ለወልድ ይገዛል:- (ዮሐንስ 14÷16፤ 14÷26፤ 15÷26፤ 16÷7 በተለይ ደግሞ ዮሐንስ 16:13-14):: ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር አብ ይገዛል (ሉቃስ 22÷42፤ ዮሐንስ 5÷36፤ 20÷21፤ 1ዮሐንስ 4÷14):: በሥላሴ አካላት መካከል፣ "መብለጥና መበላለጥ፣ መቅደምና መቀዳደም የለም" ሲባል፣ ባሕርይን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ብቻ መሆኑን ልብ ይሏል:: ራስን በትሕትና ዝቅ ማድረግ በሥላሴ አካለት መካከል እንዳለ ከቃለ እግዚአብሔር በግልጽ እንማራለን፤ ለምሳሌ:- ፊልጵስዩስ 2÷1-11 ይመለከቷል::

7. **ማርቆስ 10÷17-18፤** ኢየሱስ አምላክ አይደለሁም ማለቱ ሳይሆን፣ ግለሰቡ የዘላለምን ሕይወት እንዲሁ በልግስና/በጸጋ በሚሰጠው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እንዲታመን ለማሳሰብ ነው። ሰውየው ከማን ጋር እየተነጋገረ እንዳለ እንዲገነዘብ እንዲያስተውል ተፈልጎ ሊሆን ይችላል። በዚህ ሐሳብ ክፍሉን ከሙሉ ዐውዱ ጋር ያንብቡ።

8. **ዕብራውያን 5÷14፤** አምላክ የማይፈተን ከሆነ ያዕቆብ 1÷13 ኢየሱስ ለምን ተፈተነ የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፤ ቊም ነገሩ ግን ኢየሱስ ኀጢአትን አላደረገም (ዮሐንስ 5÷19)።

9. **ዮሐንስ 1÷18፤** እግዚአብሔርን ያየ አንድም ሰው ከሌለ፣ ሰዎች ኢየሱስን ለምን አዩት (ለምሳሌ 1ዮሐንስ 1÷1-2) የሚል ጥያቄ ሰዎች ይጠይቃሉ። ኢየሱስ መታየት የቻለው ለኀጢአታችን ሲል ክብሩን ትቶ በመምጣት የእኛን መከራ መሸከም ስላስፈለገ ነው (ፊልጵስዩስ 2÷5-11)። አሁን በክብሩ ያለውን ጌታ ግን ማንም ሊያየው አይችልም 1ጢሞቴዎስ 6÷16።

10. **1ጢሞቴዎስ 1÷17፤** እግዚአብሔር ካልሞተ ኢየሱሰ እንዴት ሊሞት ቻለ? ለምሳሌ ፊልጵስዩስ 2÷8። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም ነው። ሞቶም አልቀረም ራሱን ከሙታን አስነሣ እንጂ (ዮሐንስ 10÷18፤ ሐዋርያት ሥራ 2÷24፤ ዮሐንስ 2÷19-22)።

11. **1ቆሮንቶስ 8÷6፤** በዚህ ስፍራ አብ "እግዚአብሔር" ሲባል ኢየሱስ ግን ለምን "ጌታ" ተባለ፣ የሚል ጥያቄ አንዳንድ ሰዎች ይጠይቃሉ፤ ነገር ግን በዐውዱ ውስጥ "እግዚአብሔር" እና "ጌታ" የሚሉት ቃላት በተለዋዋጭነት ማገልገላቸው አንድ ዐይነት ትርጒም እንደሚወክሉ ያሳያል (በተጨማሪ "እግዚአብሔር" እና "ጌታ" የሚሉት ቃላት በተለዋዋጭነት ካገለገሉባቸው ስፍራዎች ውስጥ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ቊጥር 5 እንዲሁም ሮሜ 14÷3-12)። በተጨማሪ የክፍሉ ዐውድ "ጌታ" በተባለው ኢየሱስ፣ "እግዚአብሔር" ከተባለው አብ በአምላክነቱ ያንሳል የሚል ትምህርት የለውም። ወይም ኢየሱስ እግዚአብሔር አይደለም እንዲሁም አብ ጌታ አይደለም የሚል ትምህርት አያስተምርም (ማቴዎስ 11÷25 ከይሁዳ 4 ጋር ያወዳድሯል)።

12. **1ጢሞቴዎስ 2÷5፤** በዚህ ክፍል ኢየሱስ ከእግዚአብሔር እንደሚለይ እንደሚገልጸው ሁሉ፣ ኢየሱስም በኀጢአት ከወደቁት የሰው ልጆች ይለያል፣ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ማንነት ያለው አምላክ ነው።

13. **ዘዳግም 4÷12፡15-25፤** እስራኤላውያን በኀጢአት በሚወድቁበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር አብ ድምፁን ከመላክ በስተቀር ሰው ሆኖ በመምጣት ሲታደጋቸው አንመለከትም፤ ኢየሱስ፣ ለሰው ልጆች ኀጢአት ሲል ሰው ሆኖ ወደዚህች ምድር መምጣቱ፣ ኢየሱስ አምላክ ነው ከመባሉ አንጻር እንዴት ይታያል የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። በዚያን ጊዜ በሚታይ ሁኔታ ያልተገለጠው እግዚአብሔር ከዚያን ጊዜ በኋላም በሚታይ ሁኔታ አይገለጥም ማለት አይደለም።

14. በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ በአካል እንደሚለይ ይገልጻሉ፤ ለምሳሌ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ፣ በእግዚአብሔር እንደ ተላከ ወዘተ በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት ውስጥ እግዚአብሔር የሚለው መጠሪያ አብን የሚያመለክት ነው።



## VII. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።

**ሀ. እግዚአብሔር ተብሎአል፤ ሐዋርያት ሥራ** 5÷3-4፤2ቆሮንቶስ 3÷17-18፡፡

**ለ. እግዚአብሔር ብቻ ያለው/ገንዘቡ ያደረጋቸው ባሕርያት ሁሉ አሉት፡-**

1. ዘላለማዊ ነው፤ ዕብራውያን 9÷14፡፡

2. በሁሉ ቦታ ይገኛል፤ መዝሙር 139÷7፡፡

3. ሁሉን ያውቃል፤ 1ቆሮንቶስ 2÷10-11፡፡

**ሐ. እግዚአብሔር ብቻ የሚሠራውን ሥራ ይሠራል**

1. ፈጣሪ ነው፤ ዘፍጥረት 1÷2፤ መዝሙር 104÷30፡፡

2. በኢየሱስ ሥጋዌ/ትስብእታዊ ሕይወት፤ ማቴዎስ 1÷18:20፤ ሉቃስ 1÷35፡፡

3. በትንሣኤ፤ ሮሜ 1÷4፤ 8÷11፡፡

4. የዘላለምን ሕይወት መስጠት፤ ሮሜ 8÷1-27፡፡

**መ. አካል አለው**

1. ስም አለው፣ ማቴዎስ 28÷19፤ ምንም እንኳ ግዑዝ ለሆኑም ነገሮች ስም የሚሰጥ ቢሆንም፣ በዚህ ክፍል ላይ አካል ካላቸው ከአብና ከወልድ ጋር እኩል መጠቀሱ አካል እንዳለው ያመለክታል፡፡

2. "አጽናኝ" ነው፡-

ሀ) ሌላ አጽናኝ ነው፣ ዮሐንስ 14÷16፤ ከ1ዮሐንስ 2÷1 ጋር ያወዳድሯል፡፡ በአዲስ ኪዳን ግሪክ፣ አጽናኝ (ግሪክ “ፓራክሊቶስ”) የሚለው ቃል የሚያገለግለው አካል ላለው ነው፡፡

ለ) ለማስተማር በኢየሱስ ስም ይላካል፤ ዮሐንስ 14÷26፡፡

ሐ) በአስፈላጊው ጊዜ በመገኘት ይመሰክራል፤ ዮሐንስ 15÷26-27፡፡

መ) ኢየሱስ በሚልከው ጊዜ በመላክ ስለ ኀጢአት ይወቅሳል፤ ስለራሱ ሳይሆን ስለኢየሱስ በመናገር ኢየሱስን ያከብራል፤ ይህም መንፈስ ቅዱስ ትሑት እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው፤ ዮሐንስ 16÷7-14፡፡

3. መንፈስ ቅዱስ፣ ከርኩሳን መናፍስት ጋር ተነጻጽሮአል፤ ማርቆስ 3÷22-30፤ ማቴዎስ 12÷32፤ 1ጢሞቴዎስ 4÷1፤ 1ዮሐንስ 3÷24-4÷6፡፡

4. ይናገራል፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠቅሶ ይናገራል፤ ዮሐንስ 16÷13፤ ሐዋርያት ሥራ 1÷16፤ 8÷29፤ 10÷19፤ 11÷12፤ 13÷2፤ 16÷6፤ 20÷23፤ 21÷11፤ 28÷25-27፤ 1ጢሞቴዎስ 4÷1፤ ዕብራውያን 3÷7-11፤ 10÷15-17፤ 1ጴጥሮስ 1÷11፤ ራእይ 2÷7:11:17:29፤ 3÷6:13:22፡፡

5. ሰዎች ሊዋሹት ሙከራ አድርገዋል፤ ሐዋርያት ሥራ 5÷3፡፡

6. ውሳኔ ይወስናል/ፍርድን ይሰጣል፤ ሐዋርያት ሥራ 15÷28፡፡

7. ለአማኞች በእግዚአብሔር አብ ፊት ይማልዳል፤ ሮሜ 8÷26፡፡

8. መንፈስ ቅዱስ አካል በሌላቸው ነገሮች የተገለጸው ሌሎች አካል ያላቸው አካላት በተገለጹበት መንገድ ነው፡-

ሀ) መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉ፤ ማቴዎስ 3÷11፤ ሉቃስ 3÷16፤ እንዲሁም ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር ያነጻጸሩ ዘፀአት 3÷2-4፤ ዘዳግም 4÷24፤ 9÷3፤ ዕብራውያን 12÷29።

ለ) መንፈስ ቅዱስ መፍሰሱ፤ ሐዋርያት ሥራ 2÷17:33፤ ከኢሳይያስ 53÷12፤ ፊልጵስዩስ 2÷17፤ 2ጢሞቴዎስ 4÷6 ጋር ያነጻጽሩ።

ሐ) በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፤ ኤፌሶን 5÷18 ወዘተ ከኤፌሶን 3÷17:19፤ 14÷10 ጋር ያነጻጽሩ።



## VIII. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት ናቸው። (አካል ማለት የራሱ ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት ያለው ማለት እንጂ መጨበጥና መዳሰስ እንዳልሆነ ልብ ይሏል)።



### ሀ. ማቴዎስ 28:19

1. የክፍሉ የሰዋስው አወቃቀር በተለይም በዚህ ክፍል ላይ የተጠ ቀሱት ውስን መስተኣምሮች (the) አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት መሆናቸውን ያሳያል። ይህን ዐይነቱን የሰዋስው አወቃቀር ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ፣ ራእይ 1÷17፤ 2÷8:26።

2. አብ የተለየ አካል እንዳለው ውልድም የተለየ አካል አለው፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ አካል የለውም ወይም አብ በኢየሱሰ ውስጥ ያለው መለኮት ነው፤ ኢየሱስ ደግሞ አብ የለበሰው አካል ነው የሚሉ ሰዎች ሁሉ[47]፣ በዚህ ቦታ ላይ የሚገኘው የሰዋስው አወቃቀር ከትምህርታቸው ጋር ይቃረናል (በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስን አካል እንደ ሆነ አድርጎ ነው የሚመለከተው፤ ዐውዱ አለመሆኑን ካላሳየ በስተቀር)።

3. “ስም” የሚለው ነጠላ ቃል አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል መሆናቸውን አያመለክትም። "ስም" የሚለው ነጠላ ቃል የጥቅል ስም እንደ መሆኑ መጠን፣ የብዙ ቍጥር ላላቸው አካላትም ጥቅም ይውላል። አስረጅ እንዲሆን የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመለከቷል፡- ዘፍ 5÷2፤ 11÷14፤ 48÷6፤ 48÷16።

4. ስም የሚለው ቃል የተጸውዖ ስምን ብቻ የሚያመለክት አይደለም፤ ነገር ግን የማዕረግ ስምንም ያመለክታል፣ ለምሳሌ ኢሳይያስ 9÷6፤ ማቴዎስ 1÷23። በመጽሐፍ ቅዱስ አብ፣ ወልድና መንፈስ በተጸውዖ ስምነት የሚገለገሉበት ስም ያህዌ የሚለው ስም ነው።

### ለ. የሐዋርያት ሥራ 2÷38 እንዲሁም ማቴዎስ 28÷19።

1. በሁለቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰነ የጥምቀት ቀመር ሥራ ላይ ውሎ አንመለከትም። እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው በሚያጠምቅበት ጊዜ፣ "በ...ስም አጠምቅሃለሁ" የሚል ነገር ተዘግቦ አንመለከትም።

2. በኢየሱስ ስም የተጠመቁ ሰዎች (የጥምቀት ቀመር ሆኖ አገልግሏል ቢባል እንኳ ማለት ነው)፣ በብሉይ ኪዳን ሥርዐት የኖሩና በሕጉም መሠረት እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡-

[47] ለምሳሌ “የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት።

ሀ) አይሁዶች፤ ሐዋርያት ሥራ 2÷5:38፤ 22÷16።

ለ) ሳምራውያን፤ ሐዋርያት ሥራ 8÷5:12:16።

ሐ) እግዚአብሔርን ይፈሩ የነበሩ አሕዛብ (ሃይማኖታቸውንም ወደ ይሁዲነተ የቀየሩ)፤ ሐዋርያት ሥራ 10÷1-2:22:48።

መ) የመጥመቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት፣ ሐዋርያት ሥራ 19÷1-5። ዮሐንስ፣ አብርሃም አባታችን የሚሉትን ሰዎች ንስሓ እንዲያስገባና ለመሲሑ መንገድ እንዲያመቻች የተላከ ነቢይ ነው። እነዚህ ሰዎች የመጥመቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሆኑ አይሁድ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

ሠ) በቆሮንቶስ የነበሩት የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አይሁዶችና "እግዚአብሔርን ይፈሩ የነበሩ አሕዛብ" ናቸው። ["እግዚአብሔርን ይፈሩ የነበሩ አሕዛብ" የሚለው ሐረግ፣ እምነታቸውን ወደ ይሁዲነት የቀየሩ፣ በትውልድ አሕዛበ የነበሩ ሰዎች መሆናቸውን ልብ ይሏል] ሐዋርያት ሥራ 18÷1-8፤ 1ቆሮንቶስ 1÷13።

## ሐ. እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ ክርስቶስ የተለያዩ አካላት ናቸው

1. የሚከተሉትን ሰላምታዎች ይመለከቷል፤ ሮሜ 1÷7፤ 1ቆሮንቶስ 1÷3፤ 2ቆሮንቶስ 1÷2፤ ገላትያ 1÷3፤ ኤፌሶን 1÷2፤ 6÷23፤ ፊልጵስዩስ 1÷2፤ 1ተሰሎንቄ 1÷1፤ 2ተሰሎንቄ 1÷1:2፤ 1ጢሞ ቴዎስ 1÷1:2፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷2፤ ቲቶ 1÷4፤ ፊልሞና 3፤ ያዕቆብ 1÷1፤ 2ጴጥሮስ 1÷2፤ 2ዮሐንስ 3።
2. አብና ወልድ ሁለት ምስክሮች ናቸው፤ ዮሐንስ 5÷31-32፤ 8÷16-18፤ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ ዘኍልቁ 35÷30፤ ዘዳግም 17÷6፤ 19÷15።
3. አብ ወልድን ልኳል፤ ዮሐንስ 3÷16-17፤ ገላትያ 4÷4፤ 1ዮሐንስ 4÷10፤ ከሚከተሉተ ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ ዮሐንስ 1÷6፤ 17÷18፤ 20÷21።
4. አብና ወልድ እርስ በርሳቸው ይዋደዳሉ፤ ዮሐንስ 3÷35፤ 5÷20፤ 14÷31፤ 15÷9፤ 17÷23-26፤ ከሚከተሉተ ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ ማቴዎስ 3÷17፤ 17÷5፤ 2ጴጥሮስ 1÷17።
5. አብ ለወልድ ይናገራል፤ ወልድም ለአብ ይናገራል፤ ዮሐንስ 11÷41-42፤ 12÷28፤ 17÷1-26 ወዘተ።
6. አብ ወልድን ያውቀዋል፤ ወልድም አብን ያውቀዋል፤ ማቴዎስ 11÷27፤ ሉቃስ 10÷22፤ ዮሐንስ 7÷29፤ 8÷55፤ 10÷15።
7. ኢየሱሰ ጠበቃችን በአብ "ዘንድ" ነው ያለው 1ዮሐንስ 2÷1።

## መ. ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ አይደለም

1. **ኢሳይያስ 9÷6፣** "የዘላለም አባት" ማለት ዘላለማዊ ማለት እንጂ፣ ኢየሱስ አብ ነው ማለት አይደለም። "የዘላለም አባት" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል "አቢአድ" የሚል ሲሆን፣ ትርጒሙም "አቢ" ማለት አባት ማለት ሲሆን፣ "አድ" ማለት ደግሞ፣ ዘላለማዊ ማለት ነው። በተገናኝ የሚነበቡ ይህን መሰል በርካታ ስሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። ለምሳሌ:- "አቢአልቦን" (2 ሳሙኤል 23÷31) ማለት የጥንካሬ አባት ወይም ጠንካራ ማለት ነው። "አቢያሳፍ" (ዘፀአት 6÷24) ማለት ደግሞ የመሰብሰብ አባት ወይም ሰብሳቢ ማለት ነው። "አቢጋኤል" (1ዜና 2÷16) ማለት፣ ከፍ የማለት አባት ወይም ከፍ ያለች ማለት ነው፤ ይህ ስም የሴት ስም እንደ ሆነ ልብ ይሏል። በዕብራይስ ቋንቋ "አባት" (በዕብራይስጥ አቢ) የሚለው ቃል ከስም ጋር ሲጫፈር (በተገናኝ

ሲነበብ) ስሙን የሚየደምቅ ወይም የሚየጸና ነው:: ለምሳሌ:- "የውሸት አባት" ማለት ቀንደኛ ውሸታም እንደ ማለት::

2. **ዮሐንስ 10÷30::**

   ሀ) ኢየሱስ፣ "እኔ አብ ነኝ" ወይም "አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው" አላለም::

   ለ) የብዙ ቊጥር የሚያመለክተው የመጀመሪያ መደብ ተውላጠ ስም "ነን" ("we are")፣ (በግሪኩ "እስሜን") የሚለው ቃል፣ አብና ወልድ የተለያዩ መሆናቸውን ያሳያል::

   ሐ) "አንድ" ተብሎ የተተረጐመው የአማርኛ ቃል በግሪኩ ሂን የሚል ሲሆን፣ ቃሉም የግዑዝ ጾታን የሚያመለክት ነው:: ይህም አብና ወልድ ተመሳሳይ ባሕርይ እንዳላቸው የሚያመለክት እንጂ፣ አንድ አካል መሆናቸውን የሚያስተምር አይደለም:: ይህን ክፍል ከዮሐንስ 17÷21-23 ጋር ያነጻጽሩት::

3. **ዮሐንስ 5÷43፣** ኢየሱስ በአባቱ በአብ ስም መጣ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ነው ማለት አይደለም:: አንዳንዶች በራሳቸው ስምና ሥልጣን ይመጣሉ፤ ኢየሱሰ ግን እንዲህ አይደለም፤ እርሱ የመጣው በአባቱ ስምና ሥልጣን ነው::

4. **ዮሐንስ 8÷19፤ 16÷3፣** በርግጥ ኢየሱስን አለማወቅ ማለት አብን አለማወቅ ማለት ነው:: ነገር ግን ኢየሱስ በክፍሉ ውስጥ፣ "አባቴ" ተብሎ የተጠቀሰው ነው ማለት አይደለም::

5. **ዮሐንስ 14÷6-11::**

   ሀ) አብና ወልድ አንድ ዐይነት ባሕርይ እንጂ፣ አንድ አካል ያላቸው አይደሉም::

   ለ) ኢየሱስ፣ "እኔ በአብ እንዳለሁ" አለ እንጂ፣ "እኔ አብ ነኝ" አላለም::

   ሐ) "አብ በእኔ እንዳለ" የሚለው ሐረግ ኢየሱስ አብ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው:: ይህን ክፍል ከዮሐንስ 14÷20፤ 17÷21-23 ጋር ያወዳድሩ::

6. **ዮሐንስ 14÷18፣** በጥንቱ የዕብራውያን ባህል፣ የበኵር ልጅ ወላጆቹ ሲሞቱ፣ ታናናሾቹን የመጠበቅ/የማስተዳደር ኀላፊነት አለበት፤ በዚህም መንገድ የዚህ ቤተ ሰብ ልጆች የሙት ልጆች እንዳይባሉ ያደርጋቸዋል፤ ይህ ማለት ግን የበኵር ልጁ የልጆቹ አባት ሆነ ማለት አይደለም::

7. **ቈላስይስ 2÷9፣** ይህ ክፍል ኢየሱስ አብ ነው ወይም ኢየሱስ አብ ያደረበት ሥጋ ነው የሚል ትምህርት የለውም:: "ቲዎቴቶስ" የሚለው የግሪክ ቃል፣ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን/የአምላክ ባሕርይ እንዳለው ከዚህም የተነሣ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ የሚያስተምር እንጂ፣ ኢየሱስና አብ አንድ አካል እንዳላቸው የሚያስተምር አይደለም:: "ቲዎቴቶስ" የሚለው የግሪክ ቃል፣ ኢየሱስ አብ ነው የሚል መልእክት የለውም:: ኢየሱስ ውስጥ አብ መኖሩ (ዮሐንስ 10÷38፤ 14÷10:11፤ 17÷21) ኢየሱስን ከአብ ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ እንዳለው የሚያሳይ እንጂ፣ ኢየሱስና አብ አንድ አካል እንዳላቸው የሚያስተምር አይደለም::

8. አብና ወልድ በተመሳሳይ ሥራዎች ውስጥ በኅብረት ሠርተዋል:: ይኸውም ኢየሱስን ከሙታን መካከል በማስነሣት (ገላትያ 1÷1፤ ዮሐንስ 2÷19-22) ለሙታን ሕይወትን በመስጠት (ዮሐንስ 5÷21፤

6÷39-40:44:54¿ 1ቆሮንቶስ 6÷14) ጸሎትን በመመለስ (ዮሐንስ 5÷21፣ 6÷39-40:44:54፣ 1ቆሮንቶስ 6÷14) መንፈስ ቅዱስን በመላክ (ዮሐንስ 14÷16፣ 15÷26፣ 16÷7) ሰዎችን ወደ ኢየሱስ በማምጣት (ዮሐንስ 6÷44፣ 12÷32) ወዘተ:: አብና ወልድ አንድ ዐይነት ሥራ በኅብረት መሥራታቸው አብ አምላክ እንደ ሆነ ሁሉ ወልድም አምላክ መሆኑን የሚያመለክት እንጂ፣ ኢየሱስ አብ መሆኑን የሚያስተምር አይደለም::

**ሠ. ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚህች ምድር ከመምጣቱ በፊት እንዲሁም ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት ነበር:: ይህ፣ ኢየሱስ ከአብ የተለየ ማንነት እንዳለው የሚያስተምር ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ልሔም ከመወለዱም በፊት የነበረ መሆኑን የሚያስተምር ነው:: ይህ፣ እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ለዘላለም ዓለም አብሮ መኖሩን የሚያመለክት ነው:: ይህም አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ያሳያል::**

1. ኢየሱስ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው::

2. ኢየሱስ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው፣ ከላይ VI.ሠ.1 ይመለከቷል::

3. ኢየሱስ ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት (ከፍጥረት ዓለም አስቀድሞ)፣ ከአብ ጋር "አብሮ" ነበር ("ፕሮስ" ወይመ "ፓራ" የሚለው የግሪኩ ቃል በአማርኛ ቅጆች ላይ "ዘንድ" ተብሎ ነው የተተረጐመው)፤ ዮሐንስ 1÷1፤ 17÷5፤ 1ዮሐንስ 2÷1::

4. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ከእርሱ ቀድሞ ከተወለደው ከመጥመቁ ዮሐንስ በፊት ነበር፣ ዮሐንስ 1÷15 ከዮሐንስ 1÷14-18: 29-34 ጋር ያወዳድሯል::

5. ኢየሱስ፣ ከሰማይ የመጣ፣ ከአብ የተላከ፣ ወደ ሰማይ የወጣ፣ ወደ አባቱ የተመለሰ ነው፤ ዮሐንስ 3÷13:31፤ 6÷33:38:41:46:51:56-58:62፤ 8÷23:42፤ 13÷3፤ 16÷27-28፤ ከሐዋርያት ሥራ 1÷10-11 ጋር ያወዳድሯል፤ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከመላኩ ጋር ያወዳድሯል ዮሐንስ 16:5-7፤ 1ጴጥሮስ 1÷12::

6. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መሆኑ መጠን (ዮሐንስ 8÷54-56)፣ ከአብርሃም በፊት እንደ ነበረ ተናግሮአል ዮሐንስ 8÷58::

7. ኢየሱስ ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት (ከፍጥረት ዓለም አስቀድሞ)፣ እንደ ነበረ ተናግሮአል ቈላስይስ 1÷17፤ ከ1÷12-20 ጋር ያወዳድሯል::

8. እስካሁን ያልናቸው እግዚአብሔር ነገሮችን አስቀድሞ ከማወቁ ጋር የሚቃረኑ አይደሉም:: እግዚአብሔር ነገሮች ከመፈጠራቸው በፊት ያውቃቸዋል ማለት፣ ከመፈጠራቸው በፊት ህልውና ነበራቸው ማለት አይደለም::

   ሀ) ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት እኛ ሁላችን በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ነበርን፤ ነገር ግን የዮሐንስ 1÷1፤ እንዲሁም 17÷5 ክፍሎች ስለ ክርስቶስ የሚያስተምሩት ትምህርት እንደዚያ አይደለም::

   ለ) ሁሉ ነገር በእርሱ ከተፈጠረ፣ እርሱ ከፍጥረት በፊት ነበረ ማለት ነው::

9. ኢየሱስ "ዛሬ ወለድሁህ" መባሉ፣ ኢየሱስ ልጅ የተባለው ፍጥረታት በተፈጠሩበት ቀን ነው ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም ይህ ክፍል የሚናገረው በትንሣኤ ቀን ስላለው ክብር ነውና

(ሐዋርያት ሥራ 13÷33፤ ዕብራውያን 1÷3-5፤ 5÷5፤ ከመዝሙር 2÷7፤ ጋር ያወዳድሯል፤ እንዲሁም ከሮሜ 1÷4 ጋር)።

### ሬ. ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ አይደለም

1. መንፈስ ቅዱስ፣ "ሌላ አጽናኝ ነው" ዮሐንስ 14÷16፤ ከ1ዮሐንስ 2÷1 ጋር ያወዳድሯል።

2. ኢየሱስ፣ መንፈስ ቅዱስን ልኮታል ዮሐንስ 15÷26፤ 16÷7።

3. መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን እንደሚያከብር መናገሩ ለወልድ ራሱን ዝቅ ("humility") ማድረጉን ያሳያል ዮሐንስ 16÷13-14።

4. ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸው (ወልድ የራሱ አካል እንዳለው ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም የራሱ አካል እንዳለው) በማቴዎስ 28÷19 ላይ ተገልጾአል።

5. መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ወርዶበታል ሉቃስ 3÷22።

6. ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ነውን?

ሀ) 2ቆሮንቶስ 3÷17፣ በዚህ ክፍል ኢየሱስ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ጌታ ተብሎአል፤ ይህም መንፈስ ቅዱስ አምላክ ወይም ያህዌ መሆኑን ያሳያል። (ቊጥር 16 በአንዳንድ ቅጆች ቊጥር 17 ከዘፀአት 34÷34 የተጠቀሰ ነው) ሐዋርያት ሥራ 28÷25-27 ከኢሳይያስ 6÷8-10 ጋር ያነጻጽሯል።

ለ) 1ቆሮንቶስ 15÷45፣ ኢየሱስ "ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ" መባሉ፣ በበዓለ ኀምሳ ቀን የወረደው መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት አይደለም። "ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ" ማለት እግዚአብሔር እንደ መሆኑ መጠን መንፈስ መሆኑን የሚያሳይ እንዲሁም በከበረ የትንሣኤ አካል ከሙታን መነሣቱን የሚያመለክት ነው። ምንም እንኳ ሦስት መንፈስ ባይኖርም፣ ሦስቱም የሥላሴ አካላት መንፈስ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ግን መንፈስ በመባል ይጠራል።

ሐ) ሮሜ 8÷27:34፣ ሁለቱ አካላት ስለ እኛ መማለዳቸው ሁለት አማላጅ[48] እንዳለን የሚያመለክት ነው እንጂ ኢየሱስ

[48] "ማለደ" የሚለው ቃል ብዙ ትርጒም ሊወክል ይችላል። ለምሳሌ 1) "ማለደ" ማለት ማልዶ ተነሣ (በጧት ተነሣ) ማለት ሊሆን ይችላል። በዚህ ትርጒም መሠረት "ማላጅ" ማለት በጧት መነሣት የሚወድ ሰው ማለት ነው። 2) "ማለደ" ማለት ለመነ፣ ደጅ ጠና የሚል ትርጒም ሊወክል ይችላል። በዚህ ትርጒም መሠረት ደግሞ፣ "ምልጃ" ማለት ልመና ወይም ደጅ ጥናት ማለት ነው። 3) "አማለደ" ማለት ደግሞ፣ በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ወገኖች መካከል የተፈጠረን ቅራኔ፣ ጠብ ወዘተ እንዲወገድ አስታረቀ ወይም ሸመገለ ማለት ነው። የሚለመነው ሰው ለማኙን ይቅርታ እንዲያደርግለት ወይም የሚፈልገውን ጒዳይ እንዲፈጽምለት በለማኙ ስም ተማጸነ ማለት ነው።

ማለደ/አማለደ የሚለው ቃል በነገረ መለኮት በተለይም ክርስቶስን በተመለከተ ያለውን ትርጒም ደግሞ በአጭሩ እንቃኝ። በብሉይ ኪዳን ሦስት ዐይነት አገልግሎቶች ነበሩ። እነርሱም **ነቢይነት፣ ክህነትና ንጉሥነት** ናቸው። ነቢያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕዝቡ የሚያስታውቁ ሲሆን (ነቢይ እግዚአብሔርን ወክሎ ለሕዝቡ ይናገራል፤ በዚህም የእግዚአበሔር አፍ ይሰኛል)፣ ካህናት ደግሞ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት፣ ጸሎትና ምስጋና ያቀርባሉ (ካህን ሕዝቡን ወክሎ ለእግዚአብሔር ይናገራል፤ በዚህም የሕዝብ አፍ ይባላል)፣ ንጉሥ ደግሞ የእግዚአብሔር ወኪል በመሆን ሕዝቡን ያስተዳድራል።

ኢየሱስ እነዚህን የአገልግሎቶች አገልግሏል። እንደ **ነቢይ** እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ሐሳብ/ፈቃድ አስታውቆናል። እንደ **ካህን** ለኀጢአታችን ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቅርቧል። እንደ **ንጉሥ** ደግሞ፣ በዓለማት ላይና በቤተ ክርስቲያን ላይ ይገዛል/ያስተዳድራል።

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ስለሆነ የሚከተሉትን ሦስተ ዐበይት አገልግሎቶች ሰጥቶአል/በመስጠት ላይም ይገኛል:: **1)** ለኀጢአታችን ፍጹም የሆነ መሥዋዕት አቅርቦአል (ዕብራውያን 4÷14፣ 9÷24፣ 10÷4፣ 9÷26፣ 7÷27:24-28፣ 10÷1-2:10:12:14፣ 13÷12):: **2)** ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበናል (ዕብራውያን 9÷1-7:24፣ 6÷19-20፣ 10÷19-22):: **3)** ዘወትር ስለእኛ **ይማልዳል**:: በሮሜ 8÷34 እንዲሁም በዕብራውያን 7÷25 መሠረት **ማለደ** በግሪኩ “**ኢንቲኑክሃይ**” የሚለው ቃል፣ ኢየሱስ ለሰው ልጆች በተወሰኑ (specific) ርእስ ጉዳዮች ላይ ልመና አቀረበ የሚለውን ትርጒም ወክሎ ቀርቧል:: አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ምድር በነበረበት ጊዜ ብቻ ነው የምልጃ አገልግሎት ያገለገለው፣ ከዕርገቱ በኋላ ይህን አገልግሎት አላገለገለም ወይም እርሱ ተማላጅ እንጂ አማላጅ አይደለም ይላሉ:: ምናልባት ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ሊመጣ የቻለው፣ ኢየሱስ አማላጅ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት መቅረቡ ከአብ ያሳንሰዋል ከሚለው ፍርሃት የመነጨ ሊሆን ይችላል:: ድምዳሜው ግን ስሕተት ነው:: ከማንነት የተነሣ ማነስና (ontological subordination) ከሥራ ክፍፍል የተነሣ ማነስ (functional subordination) የሚሉት የነገረ መለኮት ትምህርቶችን ልብ ልንላቸው ይገባል:: ኢየሱስ ክርስቶስ በማንነቱ ከአብ ጋር በሁሉ ነገር እኩል ሲሆን፣ በሥራ ክፍፍል ግን ለሰው ልጆች ኀጢአት ራሱን ለአብ ዝቅ አድርጎ ሲያቀርብ ይታያል:: በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕርገቱ በኋላ የማማለድ ሥራውን እንደ ሠራ ቃለ እግዚአብሔር በግልጥ ያስተምረናል:: ለምሳሌ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕርገቱ በኋላ ይህን የምልጃ አገልግሎት እንዳገለገለ ከሮሜ 8÷34 መመልከት ይቻላል:: ክፍሉ “የሚማልደው” በግሪኩ “**ኢንቲኑክሃዬ**” እንጂ፣ “የሚማለደው” አይልም:: መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ይማልዳል ስንልም በግሪኩ “**ኢንቲኑክሃዬ**” የሚለውን ቃል በሚወክል መልኩ ነው::

መላእክትም ሆኑ ቅዱሳን ሰማዕታት ለሰው ልጆች ይማልዳሉ (በሁለተኛውም ሆነ በሦስተኛው ትርጒሙ) የሚለው ትምህርት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳችም ድጋፍ ያለው አይመስለኝም:: አንዳንድ ሰዎች ለሙግታቸው መሠረት አድርገው የሚያቀርቡት የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ነው:: ይህም ቢሆን ብዙ የሚያከራክር ቢሆንም፣ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ለታሪክ ሳይሆን ለቃለ እግዚአብሔር ነው:: ከቃለ እግዚአብሔር ጋር በሚጣጣም መልኩ ታሪክን ማጣቀስ ወይም ቃለ እግዚአብሔር አፍታቶ ያልነገረንን ነገር አጥርቶ ለማየት ታሪክን ወይም ደግሞ ትውፊትን ዋቢ አድርጎ ማቅረብ ተገቢ ነው:: በታሪክ መሠዊያ ላይ ቃለ



መንፈስ ቅዱስ መሆኑን የሚያስተምር አይደለም (ዮሐንስ 14÷16፣ ሮሜ 8÷26፣ 1ዮሐንስ 2÷1)::

መ) ዮሐንስ 14÷18፣ እዚህ ላይ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እንደሚገለጥላቸው የሚያሳይ እንጂ፣ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት የሚያሳይ አይደለም፤ ይህን ክፍል ከዮሐንስ 14÷19 ጋር ያወዳድሯል::

ሠ) ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ በተመሳሳይ ሥራ ላይ ተካፋይ ሆነዋል፤ ይኸውም ኢየሱስን ከሙታን በማስነሣት (ዮሐንስ 2÷19-19-22፣ ሮሜ 8÷9-11)፣ ሙታንን ከሙታን በማስነሣት (ዮሐንስ 5÷21፣ 6÷39-40:44:54፣ ሮሜ 8÷9-11)፣ በአማኞች ውስጥ በማደር (ዮሐንስ 14÷16፣ 2ቆሮንቶስ 13÷5፣ ቈላስይስ 1÷27)፣ ለአማኞች በመማለድ (ሮሜ 8÷26፣ ዕብራውያን 7÷25)፣ አማኞችን በመቀደስ (ኤፌሶን 5÷26፣ 1ጴጥሮስ 1÷2) ወዘተ:: እነዚህ ሥራዎች ሁለቱም አካላት እግዚአብሔር መሆናቸውን የሚያሳይ እንጂ፣ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አይደለም::

እግዚአብሔርን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ግን የወንጌል አገልጋይ አያሰኝም:: በታሪክ የሚደግፍ ነገር ቢገኝ እንኳ ማለቴ እንጂ፣ ታሪክ የመላእክትንና የቅዱሳን ሰማዕታትን አማላጅነት ያስተምራል የሚል አቋም ስላለኝ አይደለም::

አንዳንድ ጸሓፍት መምህራን **የምልጃንና** (intercession ወይም Intermediate) **የወጆን** (redemption) አስተምህሮ ሲያቀላቅሉት ስለሚታይ አንባብያን ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርባቸዋል:: ምልጃ ማለት “በተወሰኑ (specific) ርእስ ጉዳዮች ላይ ስለ አማኞች በአብ ፊት ልመናን ማቅረብ” የሚል ትርጒም ሲኖረው፣ ወጆ ማለት ደግሞ “ከኀጢአትና ከሰይጣን ባርነት ዕዳን በመክፈል ዐርነት/ነጻ ማውጣትን” ይመለከታል:: የወጆን አስተምህሮ ለማብራራት ተዘውትሮ የሚቀርበውን ታሪካዊ ማብራሪያ ልብ ይሏል፤ ይኸውም የጥንት ባሮችን ዐርነት/ነጻ ለማውጣት ይከፈል የነበረውን ዋጋ (ransom) ማለቱ ነው::

**ሰ. አብ መንፈስ ቅዱስ አይደለም**

1. አብ መንፈስ ቅዱስን ልኮታል ዮሐንስ 14፥15፤ 15፥26።

2. መንፈስ ቅዱስ ወደ አብ ለአማኞች ይማልዳል ሮሜ 8፥26-27።

3. አብና መንፈስ ቅዱስ ሁለት የተለያዩ አካላት መሆናቸው በማቴዎስ 28፥19 ላይ ተገልጾአል።

4. አብ መንፈስ ቅዱስ ነውን?

   ሀ) ማቴዎስ 1፥18፤ ሉቃስ 1፥35፣ አንዳንዶች ከእነዚህ ክፍሎች በመነሣት መንፈስ ቅዱስ፣ ለወልድ ሥጋዊ አባት ነው ይላሉ፤ ይህ ግን ኢየሱስ በሰብአዊ ሁኔታ በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች መካከል በሚካሄድ የግብረሥጋ ግንኙነት አይደለም።

   ለ) አብና መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ ሥራዎች ውስጥ በኅብረት ሠርተዋል፤ ይኸውም በኢየሱሰ ትንሣኤ (ገላትያ 1፥1፤ ሮሜ 8፥11) ኢየሱስን በማጽናናት (2ቆሮንቶስ 1፥3-4፤ ዮሐንስ 14፥26) ኢየሱስን በመቀደስ (ይሁዳ 1፤ 1ጴጥሮስ 1፥2) ወዘተ። ይህ የሚያሳየን ሁለቱ አካላት በኅብረት መሥራታቸውን እንጂ፣ ሁለቱ አካላት አንድ መሆናቸውን አይደለም።

## IX. ማጠቃለያ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ያስተምራል?

**ሀ. ቃለ እግዚአብሔር ስለ ትምህርተ ሥላሴ ያስተምራል።**

1. አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ ወይም እግዚአብሔር አንድ ብቻ።

2. አብ እግዚአብሔር ነው።

3. ወልድ እግዚአብሔር ነው።

4. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።

5. አብ የራሱ አካል አለው፤ ወልድ የራሱ አካል አለው፤ መንፈስ ቅዱስም የራሱ አካል አለው።

**ለ. አዲስ ኪዳን በተደጋጋሚነት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ይላል (እግዚአብሔር፣ ክርስቶስ፣ መንፈስ ቅዱስ)** ማቴዎስ 28፥19፤ 2ቆሮንቶስ 13፥14፤ **እንዲሁም ሉቃስ** 1፥35፤ 3፥21-22፤ 4፥1-12፤ **ዮሐንስ** 4፥10-25፤ 7፥37-39፤ 14፥16፤ 20፥21-22፤ **ሐዋርያት ሥራ** 1፥4-8፤ 2፥33:38-39፤ 5፥3-4:9:30-32፤ 7፥55-56፤ 10፥36-38:44-48፤ 11፥15-18፤ 15፥8-11፤ 20፥38፤ 28፥25-31፤ **ሮሜ** 1፥1-4፤ 5፥5-10፤ 8፥2-4:9-11:14-17፤ **1ቆሮንቶስ** 6፥11፤ 12፥4-6:11-12:18፤ **2ቆሮንቶስ** 1፥19-22፤ 3፥6-8:14-18፤ **ገላትያ** 3፥8-14፤ 4፥4-7፤ **ኤፌሶን** 1፥3-17፤ 2፥18:21-22፤ 3፥14-19፤ 4፥4-6:29-32፤ 5፥18-20፤ **ፊልጵስዩስ** 3፥3፤ **1ተሰሎንቄ** 1፥3-6፤ **2ተሰሎንቄ** 2፥13-14፤ **ቲቶ** 3፥4-6፤ **ዕብራውያን** 2፥3-4፤ 9፥14፤ 10፥28-31፤ **1ጴጥሮስ** 1፥2፤ **1ዮሐንስ** 3፥21-24፤ 4፥13-14፤ **ይሁዳ** 20-21፤ **ራእይ** 2፥18:27-29።

**ሐ. ከዚህ የምንማረው ቃለ እግዚአብሔር ስለሥላሴ እንደሚያስተምር ነው።**

## X. አስተምህሮተ ሥላሴ በእምነት አስተምህሮ ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?

ሀ. **ሉዓላዊነት፣** ከሥላሴ አካላት የምንማረው፣ እግዚአብሔር የፈጠረን ፍቅራችንን ለሌሎች እንድናካፍል አድርጎ ነው (ሐዋርያት ሥራ 17÷25፤ ዮሐንስ 17÷21-26)::

ለ. **ምስጢር፤** በዚህ ምድር ሥላሴን የሚመስል አንዳችም ነገር የለም፤ ይህም እግዚአብሔር በአካባቢያችን ካሉም ሆነ ከምናስባቸው ነገሮች ሁሉ በላይ መሆኑን የሚያስተምረን ነው ሮሜ 11÷33-36፤ ኢሳይያስ 40÷18::

ሐ. **ድኅነት፤** ድኅነታችንን አስቀድሞ ያቀደው፣ ሊያድነን ወደ እኛ የመጣው፣ በእኛ መካከል ያደረው እንዲሁም ድኅነታችንን የፈጸመው 1ጴጥሮስ 1÷2፤ ኤፌሶን 1÷3-18 ወዘተ ሥላሴ ነው::

መ. **ጸሎት፤** በወልድ በኩል ወደ አብ እንጸልያለን፣ በመንፈስም ወደ ወልድ በቀጥታ መጸለይ እንችላለን ዮሐንስ 14÷13-14፤ ኤፌሶን 2÷18 ወዘተ::

ሠ. **አምልኮ፤** አብና ወልድን በመንፈስ እናመልካለን ዮሐንስ 4÷23-24፤ ፊልጵስዩስ 3÷3፤ ዕብራውያን 1÷8 ወዘተ::

ረ. **ፍቅር፤** በሥላሴ አካላት መካከል ያለው ፍቅር፣ እርስ በርሳችን ላለን ፍቅር መሠረት ነው ዮሐንስ 17÷26::

ሰ. **አንድነት፤** የሥላሴ አካላት ኅብረት የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ማእከል ነው ዮሐንስ 17÷21-23::

ሸ. **ትሕትና፤** የሥላሴ አካላት አንዱ የሌላውን ለማክበር ያላቸው ፍላጎት፣ እኛም ከራሳችን ይልቅ የሌሎችን ፍሎጎት እንድንፈልግ ያደርገናል ፊልጵስዩስ 2÷5-11፤ ዮሐንስ 16÷13-14::

ቀ. **ልጅነት፤** በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማካይነት ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር ኅብረት ሲኖረን፣ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን፤ ይኸውም እግዚአብሔር የማደጎ ልጆቹ ያደርገናል ዮሐንስ 1÷12-23፤ ሮሜ 8÷14-17::

በ. **እውነት፤** እግዚአብሔርን ከልብ የሚወዱና በእውነት ሊያመለኩት የሚፈልጉ ሰዎች፣ እግዚአብሔር እውነት እንደ ሆነ ሊያውቁ ይገባል፤ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እውነት ነው ዮሐንስ 4÷24፤ 14÷6:17፤ 15÷26፤ 16÷13::

# አባሪ 1



## እነማን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰገዱ?

| እነማን ለኢየሱስ ሰገዱ? | የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ |
|---|---|
| መላእክት | ዕብራውያን 1÷6 |

| | |
|---|---|
| **ደቀ መዛሙርት** | **ማቴዎስ** 14÷33፤ **ማቴዎስ** 28÷9፤ **ማቴዎስ** 28÷17፤ **ሉቃስ** 24÷52 |
| **ሰብአ ሰገል** | **ማቴዎስ** 2÷2፤ **ማቴዎስ** 2÷11 |
| **ለምጻሙ ሰው** | **ማቴዎስ** 8÷2 |
| **የሮማው መኰንን** | **ማቴዎስ** 9÷17-18 |
| **ከነናዊቷ ሴት** | **ማቴዎስ** 15÷25 |
| **የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከነልጆችዋ** | **ማቴዎስ** 20÷20 |
| **ዐይነ ስውሩ ሰው** | **ዮሐንስ** 9÷38 |

**እግዚአብሔር አምላክ እርሱን ብቻ እንድናመልከው ትእዛዝ ሰጥቶናል** (**ዘዳግም** 6÷13)፡፡ **ኢየሱስም ይህን እውነት ስለሚያውቀው ነው በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ ይህን ክፍል ለሰይጣን የጠቀሰለት** (**ማቴዎስ** 4÷10)፡፡ **እውነቱ ይህ ከሆነ እነዚህ ሰዎችም ሆኑ መላእክት ለኢየሱስ በሚሰግዱለት ጊዜ፣ ይህንንስ አታድርጉ ሲል ያልገሠጻቸው ለምንድን ነው? እንዲያውም አብ ራሱ መላእክቱ ለኢየሱስ እንዲሰግዱ ሲያዛቸው እንመለከታለን** (**ዕብራውያን** 1÷6)፡፡ **ይህም ኢየሱስ ከአብ ጋር ትክክል ዕሪና ያለው መሆኑን ያስረዳል፡፡**

**አብና ወልድ በሃያ አራቱ ሽማግሌዎች እኩል ስግደት ሲቀርብላቸው ከራእየ ዮሐንስ እናነባለን** (**ራእይ** 4÷11)፡፡ **ኢየሱስ ክርስቶስ "ኀይልና ባለ ጠግነት፣ ጥበብም፣ ብርታትም ክብርም፣ ምስጋናም፣ በረከትም ሊቀበል ይገባዋል"** (**ራእይ** 5÷12)፡፡ **በሰማይም ሆነ በምድር የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ፣ ይህን መሰሉን ምስጋናና አምልኮ ለአብ እንደሚያቀርቡ ሁሉ ለወልድም ያቀርባሉ** (**ራእይ** 5÷13-14)፡፡

**ከላይ በአስረጅነት በቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ "ስግደት" ለሚለው ቃል የተጠቀሙት "ፕርስኩኖ" የሚለውን የግሪክ ቃል መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡**

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ

**"ሰብአ ሰገል፡- የተወለደው የአሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ"** (**ማቴዎስ** 2÷2)፡፡

**"ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፤ ወድቀውም ሰገዱለት፤ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን፣ ከርቤም አቀረቡለት"** (**ማቴዎስ** 2÷11)፡፡

**"እነሆም ለምጻም ቀርቦ፡- ጌታ ሆይ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ ሰገደለት"** (**ማቴዎስ** 8÷2)፡፡

**"ይህንም ሲነግራቸው አንድ መኮንን መጥቶ፡- ልጄ አሁን ሞተች ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት በሕይወትም ትኖራለች እያለ ሰገደለት"** (**ማቴዎስ** 9÷18)፡፡

**"በታንኳዪቱም የነበሩት፡- በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት"** (**ማቴዎስ** 14÷33)፡፡

**"እርስዋ ግን መጥታ፡- ጌታ ሆይ እርዳኝ እያለች ሰገደችለት"** (**ማቴዎስ** 15÷25)፡፡

**"በዚያን ጊዜ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆችዋ ጋር እየሰገደችና አንድ ነገር እየለመነች ወደ እርሱ ቀረበች"** (**ማቴዎስ** 20÷20)፡፡

**"እነሆም ኢየሱስ አገኛቸውና፡- ደስ ይበላችሁ አላቸው፡፡ እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት"** (**ማቴዎስ** 28÷9)፡፡

“ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ” (ማቴዎስ 28÷17)፡፡

“እነርሱም ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ” (ሉቃስ 24÷52)፡፡

“እርሱም፡- ጌታ ሆይ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም” (ዮሐንስ 9÷38)፡፡

“ዐጕል ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ የሚወድ ማንም ሰው እንዳያደናቅፋችሁ ተጠንቀቁ፡፡ እንደዚህ ያለ ሰው ስላየው ራእይ ከመጠን በላይ ራሱን እየካበ በሥጋዊ አእምሮው ከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ ይታበያል” (ዮሐንስ 2÷18 አዲሱ መደበኛ ትርጕም)፡፡

“ደግሞም በኵርን ወደ ዓለም ሲያገባ፡- የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ” (ዕብራውያን 1÷6)፡፡

“የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ፤ በታላቅ ድምፅም፡- የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት፤ ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውሃንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት አለ” (ራእይ 14÷7)፡፡

4÷9 “እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ፣

4÷10[49] ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፡-

4÷11 ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤ ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና፤ ተፈጥረውማልና፤ ክብር ውዳሴ ኀይልም ልትቀበል ይገባሃል፤ እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ” (ራእይ 4÷9-11)፡፡

5÷11 “አየሁም በዙፋኑም፣ በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ ቍጥራቸውም እእላፋት ጊዜ እእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበረ፤

5÷12 በታላቅም ድምፅ፡- የታረደው በግ ኀይልና ባለጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዎል አሉ፡፡

5÷13 በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ፡- በረከትና ክብር ምስጋናም ኀይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ፡፡

5÷14 አራቱም እንስሶች[50]፡- አሜን አሉ፤ ሽማግሌዎቹም ወድቀው ሰገዱ” (ራእይ 5÷11-14)፡፡

# አባሪ 2

[49] ግእዙ ዕሥራ ወአርባእቱ ካህናተ ሰማይ ይላቸዋል፡፡

[50] ግእዙ አርባእቱ እንስሳ ይላቸዋል፡፡



# ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው

| አምላካዊ ባሕርያት | እግዚአብሔር አብ | እግዚአብሔር ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) |
|---|---|---|
| ሁሉን መቻል (ከሃሊ ኵሉ) | 1ዜና 29÷11 (ያህዌ) | ፊልጵስዩስ 3÷20-21 |
| ሁሉን ማወቅ | 1ዮሐንስ 3÷20 | ቈላስይስ 2÷2-3 |
| በሁሉ ቦታ መገኘት (ከሳቴ ኵሉ) | ምሳሌ 15÷3 (ያህዌ) | 2ቆሮንቶስ 2÷14 |
| የሰንበት ጌታ | ዘፍጥረት 2÷3 | ማቴዎስ 12÷8 |
| እኔ ነኝ | ዘፀአት 3÷14 (ያህዌ) | ዮሐንስ 8÷58 |
| ፈጣሪ (ገባሬ ኵሉ) | ኢሳይያስ 44÷24 (ያህዌ) | ዮሐንስ 1÷3 |
| አዳኝ | ኢሳይያስ 43÷11፤ 45÷21 (ያህዌ) | ሐዋርያት ሥራ 4÷12 |
| በሕያዋንና በሙታን መፍረድ | ኢሳይያስ 3÷13, 14 (ያህዌ) | 2ቆሮንቶስ 5÷10 |
| በበጎችና በፍየሎች ላይ መፍረድ | ሕዝቅኤል 34÷17 (ያህዌ) | ማቴዎስ 25÷31-33 |
| ነቢያትን መላክ | ኤርምያስ 7÷25 (ያህዌ) | ማቴዎስ 23÷34 |
| ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ማስነሣት | ሐዋርያት ሥራ 4:10 (ያህዌ) | ዮሐንስ 10:17-18 |
| በክብር መምጣት | ኢሳይያስ 40÷5 (ያህዌ) | ማቴዎስ 24÷30 |
| አባትነት | ኢሳይያስ 63÷16 (ያህዌ) | ኢሳይያስ 9÷6 |
| አልፋና ዖሜጋ (የመጀመሪያውና የመጨረሻው) | ኢሳይያስ 44÷6 (ያህዌ) | ራእይ 1÷17 |
| የድነት ዐለት | 2ሳሙኤል 22÷32 (ያህዌ) | 1ቆሮንቶስ 10÷4 |
| የመሰናከያ ዐለት | ኢሳይያስ 8÷13-15 (ያህዌ) | 1ጴጥሮስ 2÷8 |
| መንገድ እንዲዘጋጅለት የተነገረለት | ኢሳይያስ 40÷3 (ያህዌ) | ማቴዎስ 3÷3 |
| ዘላለማዊ | ዘፍጥረት 21÷33 (ያህዌ) | ሚክያስ 5÷2 |
| የሕይወት ውሃ ምንጭ | ኤርምያስ 17÷13 (ያህዌ) | ዮሐንስ 4÷10-14 |
| ሙታንን ማስነሣት | ሐዋርያት ሥራ 26÷8 | ዮሐንስ 6÷40 |
| ለሰው ልጆች የሥራቸውን መክፈል | ኢሳይያስ 40÷10 (ያህዌ) | ማቴዎስ 16÷27 |
| የፍጹም ክብርና የፍጹም ኀይል ባለቤት | 1ዜና 29÷11 (ያህዌ) | ማቴዎስ 28÷18 |
| ለሰው ልጆች ክብርና ኀይል መስጠት | መዝሙር 68÷35 | ሉቃስ 9÷1 |
| ኀጢአትን ይቅር ማለት | 2ዜና 7÷14 (ያህዌ) | ማቴዎስ 9÷6 |
| መንፈስ ቅዱስን መላክ | ዮሐንስ 14÷16 | ዮሐንስ 16÷7 |
| ከስም ሁሉ በላይ ስም ያለው | ነህምያ 9÷5 (ያህዌ) | ፊልጵስዩስ 2÷9 |
| ስግደት የሚገባው | ዘፀአት 34÷14 (ያህዌ) | ራእይ 5÷12-13 |
| መልካም እረኛ | ዘፍጥረት 48÷15 | ዮሐንስ 10÷14 |
| የጠፉትን የእስራኤል ልጆች የሚፈልግ | ሕዝቅኤል 34÷11 (ያህዌ) | ማቴዎስ 15÷24 |
| የጌቶች ጌታ | ዘዳግም 10÷17 (ያህዌ) | ራእይ 17÷14 |
| ጕልበት ሁሉ የሚንበረከክለት | ኢሳይያስ 45÷22-23 (ያህዌ) | ፊልጵስዩስ 2÷10 |
| የዳዊት ሥር | ኤርምያስ 23÷5-6 (ያህዌ) | ኤርምያስ 33÷15 |
| ብቻውን ቅዱስ የሆነ | 1ሳሙኤል 2÷2 (ያህዌ) | ሐዋርያት ሥራ 3÷14 |
| በደሙ ከኀጢአታችን ያነጻን | ሐዋርያት ሥራ 20÷28 | 1ዮሐንስ 1÷7 |
| ዓለማትን ገንዘቡ ያደረገ | ምሳሌ 16÷4 (ያህዌ) | ቈላስይስ 1÷16 |
| ከሁሉ በላይ የሆነ | ነህምያ 9÷6 (ያህዌ) | ሮሜ 9÷5 |
| የማይለወጥ | መዝሙር 102÷24-27 | ዕብራውያን 1÷8-12 |
| የሰው ልጆች ብርሃን | መዝሙር 27÷1 (ያህዌ) | ዮሐንስ 8÷12 |
| መንገድ | መዝሙር 16÷11(ያህዌ) | ዮሐንስ 14÷6 |
| መላእክትን ገንዘቡ ያደረገ | መዝሙር 103÷20 (ያህዌ) | 2ተሰሎንቄ 1÷7 |
| ለሰው ልጆች ዕረፍትን የሚሰጥ | ዘፀአት 33÷14 (ያህዌ) | ማቴዎስ 11÷28 |
| የዘላለምን ሕይወት የሚሰጥ | ምሳሌ 19÷23 (ያህዌ) | ዮሐንስ 3÷36 |
| ሙሽራ | ኢሳይያስ 54÷5 (ያህዌ) | 2ቆሮንቶስ 11:2 |
| ልብንና ኵላሊትን የሚመረምር | ኤርምያስ 17÷10 (ያህዌ) | ራእይ 2÷23 |

# አባሪ 3

## የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ከዕብራውያን ምዕራፍ 1

| ዕብራውያን ምዕራፍ 1 | ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች |
|---|---|
| 1. እግዚአብሔር አብ እንደሚናገረው ይናገራል (ቍጥር 1-2)፡፡ | ዮሐንስ 1÷1:14፤ 8÷43-47 |
| 2. የእግዚአብሔር አብ የሆነው ሁሉ የእርሱም ነው (ቍጥር 2)፡፡ | ማቴዎስ 11÷27፤ ቈላስይስ 1÷16 |
| 3. እግዚአብሔር አብ የሆነውን ሁሉ እርሱም ነው (ቍጥር 3)፡፡ | ዮሐንስ 1÷1፤ 14÷9፤ ቈላስይስ 1÷15 |
| 4. እግዚአብሔር አብ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እርሱም ይሠራል (ቍጥር 3)፡፡ | ዮሐንስ 5÷19፤ ቈላስይስ 1÷17 |
| 5. እግዚአብሔር አብ ያለው ክብር ሁሉ እርሱም አለው (ቍጥር 6)፡፡ | ማቴዎስ 28÷17፤ ዮሐንስ 5÷23 |
| 6. ለእግዚአብሔር አብ ያለው ማዕረግ ሁሉ ለእርሱም አለው (ቍጥር 8:10)፡፡ | ኢሳይያስ 9÷6፤ ዮሐንስ 1÷1፤ 20÷28፤ ሮሜ 10÷9-13፤ ፊልጵስዩስ 2÷9-11፤ ቲቶ 2÷3-14፤ 2 ጴጥሮስ 1÷1:11 |
| 7. እግዚአብሔር አብ ገዢ እንደሆነ ሁሉ እርሱም ገዢ ነው (ቍጥር 8-9)፡፡ | ሉቃስ 1÷33፤ ኤፌሶን 1÷21 |
| 8. እግዚአብሔር አብ የሠራቸውን ሥራዎች ሁሉ እርሱም ሠርቶአል (ቍጥር 10)፡፡ | መዝሙር 102÷25-27፤ ኢሳይያስ 44÷24፤ ዮሐንስ 1÷3፤ ቈላስይስ 1÷16 |
| 9. እግዚአብሔር አብ መመኪያ የሆነውን ያህል እርሱም መመኪያ ነው (ቍጥር 11- | ዮሐንስ 14÷1፤ ዕብራውያን 13÷8 |





| | |
|---|---|
| 12)፡፡ | |
| 10. እግዚአብሔር አብ ከፍ ያለውን ያህል እርሱም ከፍ ብሏል (ቍጥር 13)፡፡ | ማቴዎስ 28÷18፤ ኤፌሶን 1÷20-22፤ ፊልጵስዩስ 2÷9-11 |

# አባሪ 4

## ሥነ አፈታትን አስመልክቶ ተዘውትረው የሚታዩ ችግሮች

ከዚህ በታች በአጭሩ ለመመልከት የምንሞክረው፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ እንዳንተረጕም/እንዳንረዳ ሊጠቅሙን የሚችሉትን ነጥቦች ነው፡፡ እነዚህ ነጥቦች ቃለ እግዚአብሔርን በግልዎ ሲያጠኑም ሆነ፣ በአንድ ርእሰ ጕዳይ ላይ ከሌላ ሰው ጋር ሲወያዩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅዎ እንዲሁም መመሪያዎቹን መከተልዎ መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ እንዳይረዱ፣ የተረዱ ሰዎችንም እንዲያስተካክሉ ይጠቅሞታል፡፡

### 1. የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዳይደርሱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ

#### ሀ. በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ብሏልን?

**አስረጅ:-** መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ከወንዶች ያንሳሉ አይልም፡፡ 1ጢሞቴዎስ 6÷10 ገንዘብ የኀጢአት ሥር ነው አይልም፡፡ የኀጢአት ሥር የሆነው ገንዘብን **"መውደድ"** ነው፡፡ ወንጌላት ኢየሱስ ክርስቶስ በግድግዳው "ውስጥ" ወይም በተዘጋ ቤት "ውስጥ" ዐለፎ ገባ አይሉንም (ለምሳሌ:- ዮሐንስ 20÷19:26)፡፡

#### ለ. ክፍሉ በትክክል ተተርጕሞአልን?

**አስረጅ:-** ምናልባት ሉቃስ 2÷1-2 መተርጐም የነበረበት፣ "ይህም ቄሬኔዎስ በሶርያ ገዥ በነበረበት ጊዜ የተደረገ የመጀመሪያው የሕዝብ ቈጠራ ነበር"

[አዲሱ መደመኛ ትርጉም የጥናት ጽሑፍ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ማብራሪያ እንዲሁም የተለያዩ የሉቃስ ወንጌል አንድምታዎች ክፍሉን በተመለከተ የሰጡትን አስተያየት ይመለከቷል]፡፡ ዮሐንስ 1÷1 "…ቃልም ትንሽ አምላክ ነበር (a god)" ተብሎ መተርጐም በፍጹም የለበትም[51]፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ስንተረጉም ታማኝ መሆን የሚጠበቅብን ለቃሉ እንጂ፣ ለአስተምህሮአችን አይደለም፡፡

**ሐ. ምናልባት ክፍሉ በጥንት ዘመን ሲባዛ በተሳሳተ መንገድ ተገልብጦ (miscopied) ይሆንን?**

**አስረጅ፡-** 2ሳሙኤል 10÷18፤ 1ዜና 19÷18 ላይ በ700 እና በ7,000 መካከል ያለው ልዩነት፣ በጥንት ጊዜ ክፍሉ ሲገለበጥ የተፈጠረ ስሕተት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ዐይነቱ የግልበጣ ችግር በወል የሚስተዋለው በእንዲህ ዐይነቱ ጊዜ ነው፡፡

**መ. ይህ ክፍል የእናት ቋንቋው/የበኵረ ጽሑፉ ክፍል ነውን?**

**አስረጅ፡-** በማርቆስ 16÷12 ላይ ኢየሱስ፣ "በሌላ መልክ ተገለጠ" የሚለው ክፍል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሣኤ አካሉ ብቻ እንደ ገተለጠ ከሚገልጹት የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች ጋር የሚቃረን ነው፡፡ አብዛኞቹ ሊቃውንት እንደሚስማሙበት [በዚህ ክፍል የሚገኘው የዐረፍተ ነገር አሰካክ፣ የቃላት አመራረጥ፣ ከነገረ መለኮት ይዘት ከተቀሩት ክፍሎች ጋር ያለመጣጣማቸው እንዲሁም ጥንታዊና ተአማኒነት ባላቸው የጥንት ቅጆች ውስጥ ይህ ክፍል አለመገኘቱ] የማርቆስ 16÷9-20 ያለው ክፍል፣ የማርቆስ ወንጌል አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ የአዲሱ በደበኛ ትርጉም እንዲሁም የ1980 ትርጉም የጥናት ጽሑፍ/የግርጌ ማስታወሻ (ማርቆስ 16÷9-20) ላይ ይመልከቱ፡፡ ልክ እንደዚሁ ሁሉ ክርስቲያኖችም አጠራጣሪ በሆኑ ክፍሎች ላይ አስተምህሮአቸውን መመሥረት የለባቸውም፤ ለምሳሌ ትምህርተ ሥላሴን 1ዮሐንስ 5÷7 ባሉ ክፍሎች ላይ መሠረት ማድረግ ስሕተት ነው፡፡

**ሠ. ክፍሉን በትክክል ተረድተነዋልን?**

**አስረጅ፡-** በማቴዎስ 12÷40 ኢየሱስ ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ ለ72 ሰዓት እንደ ቆየ የሚናገር ይመስላል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ወንጌላት ኢየሱስ ክርስቶስ ዐርብ ሞቶ እሁድ ጧት ከሙታን እንደ ተነሣ ይነግሩናል (ማቴዎስ 27÷62-63፤ 16÷21፤ 17÷23፤ 20÷19፤ 28:1፤ ማርቆስ 15÷42፤ 16÷1፤ 8÷31፤ 9÷31፤ 10÷34፤ 14÷58፤ 15÷29፤ ሉቃስ 9÷22፤ 18÷33፤ 24÷7:46፤ 13÷32፤ 24÷21፤ ዮሐንስ 2÷19-20)፡፡ "ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት" የሚለው፣ የሦስት ቀንን ክፍሎች ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውል የዕብራውያን ፈሊጣዊ አነጋገር ነው አስቴር 4÷16፤ 5÷1፡፡ ይህን በትክክል ያልተረዳ ሰው እነዚህ ክፍሎች ሊገቡት አይችልም፡፡

**ረ. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ መረጃዎች በትክክል ተብራርተዋልን?**

**አስረጅ፡-** አንዳንድ ሊቃውንት የግብፃውያን የቀን አቈጣጠር ትክክል ነው የሚለውን ጉዳይ ታሳቢ አድርገው የፀአቱ (እስራኤላውያን ከምድረ ግብፅ የወጡበት) ታሪክ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩ ተከሥቶአል በሚልበት ጊዜ የተካሄደ አይደለም ባዮች ናቸው፡፡ የሚያስደንቀው ጉዳይ ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቀባይነት ያገኙ ንድፍ ሐሳቦች፣ የፀአቱ ታሪክ የተካሄደው ቀድሞ ከሚገመተው ከ600 ዓመት ቀደም ብሎ እንደ ሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህ ደግሞ የግብፃውያኑ የቀን አቈጣጠርና በመጽሐፍ ቅዱስ ተዘግቦ የሚገኘው የፀአቱ ታሪክ አንድ መሆኑ ነው፡፡

**ሰ. የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ ከሰዎች የአስተሳሰብ አድማስ በላይ የመሆኑ ጉዳይ ግምት ውስጥ ገብቶአልን?**

**አስረጅ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ የበላይ ገዥ መሆኑን፣ በአንጻሩ ደግሞ ሰዎች በሚሠሯቸው ሠናይም ሆነ እኩይ ሥራዎች ተጠያቂዎች መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ እነዚህ ነገሮች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስላሉ፤ ነገር ግን ይህን ጉዳይ መረዳት የምንችለው፣ የእግዚአብሔርን ምጡቅነት ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ብቻ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ እግዚአብሔር አለ ብሎን፣ እንደ አብ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር ነው የሚለው ጉዳይ ሊጨበጥልን የሚችለው የእግዚአብሔርን ምጡቅነት ታሳቢ ስናደርግ ነው፡፡

## 2. ተዘውትረው የሚታዩ የአፈታት ስሕተቶች

[51] የአዲስ ዓለሚቱ ትርጉም (New World Translation) በመባል የሚጠራው የይሖዋ ምስክሮች የመጽሐፍ ቅዱስ "ትርጉም" ክፍሉን በዚህ መልክ ነው የተረጐመው፡፡

**ሀ. እውነታን፣ ከትእዛዝ ወይም ከፍላጎት ወይም ደግሞ ከተስፋ ጋር ማቀያየጥ፡፡**

**አስረጅ፡-** የይሖዋ ምስክሮችም ሆኑ ሞርሞኖች ዮሐንስ 17÷21-23 በመጥቀስ እውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን ኅብረቷ ጠንካራ ሊሆን ይገባል ይላሉ፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ አማኞች ኅብረት ይኖራቸው ዘንድ ጸለየ እንጂ፣ ኅብረታቸው ተከናውኖአል/ተፈጽሞአል አላለም፡፡

**ለ. ታሪካዊ ክሥተቶችን ከእውነታው አላቄ መተርጐም፡፡**

**አስረጅ፡-** የይሖዋ ምስክሮች በሐዋርያት ሥራ 15 ላይ ያለውን የኢየሩሳሌሙን ጉባኤ በመጥቀስ ድርጅታቸውን ከሚመሩት የአመራር አካላት ጋር ያመሳስሉታል፤ ነገር የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ የተካሄደው በሐዋርያቱ ነው፤ ሐዋርያቱ ዛሬ እስከ ሌሉ ደረስ አንዳችም ጉባኤ በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ ሊመስል አይችልም[52] (የይሖዋ ምስክሮችም በመካከላቸው ሐዋርያ እንደ ሌለ ይቀበላሉ)፡፡

**ሐ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ቃል በቃል እንደ ተጠቀሱ አድርጎ ማሰብ፡፡**

**አስረጅ፡-** አንዳንድ ሰዎች ዕብራውያን 2÷7 እንዲሁም መዝሙር 8÷5 በመጥቀስ መላእክት አማልክት ተብለዋል ይላሉ፡፡

**መ. ክፍሉ የሚገኝበትን ሥነ ጽሑፋዊ ይዘት በግምት ውስጥ አለማስገባት፡፡**

**አስረጅ፡-** የይሖዋ ምስክሮች ምሳሌ 8÷22 ጥበብን በሰውኛ ዘይቤ በሚገልጽበት ዐውድ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ይህን ክፍል በቀጥታ በመተርጐም ይህ ጥቅስ የሚናገረው ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ስለ መፈጠሩ ነው ይላሉ፤ ይህ የክፍሉን ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ማዕከል ያደረገ አፈታት አይደለም፡፡

**ሠ. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የማይገኘውን ጉዳይ ወይም ክፍልፍሎሽ በቃሉ ውስጥ ጨምሮ ማንበብ፡፡**

**አስረጅ፡-** "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አማኞች በተጽውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል ልዩነት አለ ይላሉ፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ዐይነቱ ክፍልፍል የለም፡፡ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል፡- ዘፀአት 34÷14፤ ኢሳይያስ 7÷14፤ 9÷6፤ ማቴዎስ 1÷23፤ ራእይ 19÷13፡፡

**ረ. የግርጌ ማጣቀሻ አንድን ክፍል ከሌላው ክፍል ጋር በማጣቀሻነት ጠቅሷል ማለት ክፍሎቹ ተደጋጋፊ ናቸው ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ እንኳን የግርጌ ማጣቀሻዎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፍና በቍጥር የተከፋፈለው በቅርብ ጊዜ ነው፡፡ ይኸውም ለጥናት እንዲያመች፡፡**

**አስረጅ፡-** "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ማቴዎስ 28÷19 እና የሐዋርያት ሥራ 2÷38 እርስ በርስ በማጣቀስ ኢየሱስ ክርስቶስ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት ስሕተት ነው፡፡

## 3. ክፍሉን በረጋ መንፈስ በመመርመር ሊከሠቱ የሚችሉትን ስሕተቶች ያርሙ

**ሀ. ክፍሉንና ክፍሉ የሚገኝበትን ዐውድ ወይም ዐረፍተ ነገር በሙሉ ያንብቡ ወይም ሌላ ሰው እንዲያነብልዎ ያድርጉ፡፡**

**አስረጅ፡-** የይሖዋ ምስክሮች አብዛኛውን ጊዜ የ1ቆሮንቶስ 15÷50 የመጀመሪያ ክፍል ብቻ ይጠቅሳሉ፤ ነገር ግን ለትምህርታቸው ማስደገፊያ

[52] አንዳንድ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት፣ ዛሬም ሐዋርያት አሉ የሚል አስተምህሮ አላቸው፡፡ እንዲያውም ሰዎችን "ሐዋርያ" በማለት ይጠራሉ፡፡ የዚህ መልእክት አቅራቢ "ሕይወት" መጽሔት ቁጥር 45፣ 46 እና 47 ላይ "በውኑ ሐዋርያት አሉን?" በሚል ርእስ በተከታታይ ባቀረበው ጽሑፍ፣ ዛሬ በእነዚህ ቤተ ክርስቲያናት በስፋት የሚታየው "የሐዋርያት" አስተምህሮ በጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ውስጥ ፍጹም ባይተዋር ነው ሲል ሞግቶአል፡፡

ይሆናል በሚል ለሚጠቅሱት የመጀመሪያው ክፍል፣ የክፍሉ ሁለተኛው ክፍል ሙሉ ለሙሉ ያፈርሰዋል፡፡

**ለ. የመጠቀሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ጋር መሠረታዊ ልዩነት አለው ወይስ የለወም የሚለውን ጒዳይ ለማጣራት አንድን ክፍል በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች ይመልከቱ፡፡**

**አስረጅ፡-** የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ፍጡር ነው ለማለት ራእይ 3÷14 ከ1954 ትርጒም ይጠቅሳሉ፤ ነገር ግን ክፍሉ በ1980 እንዲሁም በአዲሱ መደበኛ ትርጒም ከ1954 ትርጒም የተለየ ሀሳብ እንዳለው እናያለን፡፡ የ ትርጒምም ቢሆን እነሱ የሚሉትን ዐይነት ትምህርት እንደሌለው ልብ ይሏል፡፡

**ሐ. ከክፍሉ በፊትና በኋላ ያሉትን ክፍሎች በደንብ ይመልከቱ (የሚያነቡት የምዕራፉን የመጀመሪያ ቊጥር ቢሆን እንኳ)፡፡ ይህን ማድረጎ ችግሩን ሊፈታው ወይም ደግሞ ክፍሉን በተሳሳተ መንገድ እንዴት ተተረጐመ የሚለውን ጒዳይ እንዲያውቁ ያደርጎታል፡፡ ይህ መሠረታዊ ጒዳይ ስለሆነ ቢያንስ ሦስት አስረጆችን እናቅርብ፤**

(1) የይሖዋ ምስክሮች ሉቃስ 12÷32 ሲጠቅሱልዎ ቊጥር 31 ያንብቡላቸው፡፡

(2) የይሖዋ ምስክሮች ዮሐንስ 2÷19 የሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያንን ነው ባዮች ናቸው ቊጥር 22 ያንብቡላቸው፡፡

(3) የይሖዋ ምስክሮች 1ዮሐንስ 4÷1 ላይ ያለውን ክፍል በተሳሳተ ምንገድ መተርጐማቸውን 3÷24 ገሐድ ያወጣዋል፡፡

**ሠ. ክፍሉን ወይም ርእሰ ጒዳዩን በዚህ መልኩ ለምን እንዳብራሩት ወይም ሊረዱ እንደ ቻሉ ይጠይቋቸው፡፡ ይህን ጥያቄዎን ለማብራራት የሚሄዱበት መንገድ ወይም ሙግት የተሳሳተ እንደ ሆነ ሊረዱ ይችላሉ፡፡**

**ረ. በውይይቱ ጣልቃ ደግመው ደጋግመው "አይደለም እንዴ?" ወዘተ በማለት የሚጠይቅዎትን ጥያቄ አይመልሱ፡፡ ብዙውን ጊዜ መናፍቃን እንዲህ የሚያደርጉት እርስዎን ለማሳሳት ብለው ነው፡፡ እነርሱ በክፍሉ ወይም**





**በርእሰ ነገሩ ላይ ማብራሪያቸውን ከጨረሱ በኋላ፣ እርስዎ የራስዎን ማብራሪያ ይስጡ፡፡ የክፍሉን ትምህርት በትክክል ያልተረዱት ከሆነ ወይም የእርስዎ መሠረተ እምነት በርእሰ ጒዳዩ ላይ ምን እንደሚል በሚገባ የማያውቁ ከሆነ፣ በግልጽነት ክፍሉን ወይም ርእሰ ጒዳዩን በሚገባ እንደማያውቁት ነገር ግን በሌላ ጊዜ አጥንተው በመምጣት ማስረዳት እንደሚችሉ ይግለጹ፡፡**

## በጸሓፊው የተዘጋጁ ሌሎች መጻሕፍት

- ዐበይት መናፍቃን
- የሥነ ምግባር መርሖ
- ውርጃን ሕጋዊ እናደርጋለንን?
- የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና ትምህርተ ሥላሴ
- የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን
- የአዲሲቱ ዓለም ትርጒም ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ነውን?
- እግዚአብሔርን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 101 ጥያቄዎች
- መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 102 ጥያቄዎች
- ትክክልና ስሕተትን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 103 ጥያቄዎች

**እንዲሁም ሌሎች**

## በጸሓፊው እየተዘጋጁ ያሉ መጻሕፍት

- **የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ መሠረት**
- "'የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን' አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

- እኵይ፡- የነገረ መለኮትና የፍልስፍና ትንታኔ
- በውኑ እግዚአብሔር አለን? ፍልስፍናዊ ጥናት (ትርጉም)
- የፍልስፍናና የነገረ መለኮት መዝገበ ቃላት
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ ምንባባት
- መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት
- ጥያቄዎቻችሁና መልሶቻቸው
- የሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮች
- የትንሣኤው ማኅበረሰብ
- የብሉይ ኪዳን መክፈቻ
- የሐዲስ ኪዳን መክፈቻ
- የሃይማኖት ፍልስፍና
- የፖለቲካ ፍልስፍና
- ዐቃቤ ክርስትና
- ሥነ አመክንዮ
- ነገረ ክርስቶስ



## ገለጻ

ሥላሴን ለማሳየት በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጠቀምንበት ይህ ምልክት
"ትሪክዊትራ ይባላል" (The Triquetra)፡፡

ትሪንክዊትራ እጅግ ጥንታዊ የሆነና የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥላሴን ለማሳየት ትጠቀምበት የነበረ ምልክት ነው፡፡ እኩል መጠን ያላቸው ሦስቱ ቀስቶች እንዲሁም የማዕከሉ ሦስት ማዕዘን ሥላሴን የሚገልጽ ሲሆን፣ የቀስት ቅርጽ እንዲኖራቸው የተፈለገበት ምክንያት ደግሞ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ዘላለማውያን መሆናቸውን ለማሳየት ነው፡፡ እርስ በርስ መቈላለፋቸው ደግሞ፣ በሥላሴ አካላት መካከል መከፋፈል እንደሌለ ለመግለጽ ታስቦ ነው፡፡ ይህ ሥዕላዊ ገለጻ ከጥንታዊነቱ አንጻር የተጠቀምንበት እንጂ፣ ትምህርተ ሥላሴን ይወክላል በሚል እንዳልሆነ ልብ ይኋል፡፡